የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

ጀኖ ፡ ሽልዩም ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡
ሰጋ ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ጎ . ም ።

Vol. II No. 1
Summer 1965

በዚህ ፡ እትም ።

IN THIS ISSUE

ጎዳር ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱፯ ፡ ዓ. ም. ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ከኤክስቴንሽን ፡ ክፍል ፡ ለመዝመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ተመርቀው ፡ ለወጡት ፡ ተማሪዎች ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ።

የሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚያበቃችሁን ፡ ትምህርታችሁን ፡ ጨርሳችሁ ፡ ዛሬ ፡ የተመረቃችሁትን ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያላችሁ ፡ እንላችኋለን ። እናንተም ፡ ብዙ ፡ ዕንቅፋት ፡ ተራምዳችሁ ፡ እዚህ ፡ የደረሳችሁት ፡ ተማሪዎችና ፡ ሥራውን ፡ አቀነባብረው ፡ እዚህ ፡ ያደረሷችሁ ፡ መምህራንም ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያላችሁ ፡ መባል ፡ የሚገባቸው ፡ ናቸው ።

ሕግን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀለኛ ፡ የንግድና ፡ ሌሎችም ፡ ሕጎች ፡ እንደዚሁም ፡ በፖርላማ ፡ ተመክሮ ፡ በመንግሥት ፡ የሚታወጁትን ፡ ዐዋጆች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውላቸው ፡ ሰው ፡ ካላገኙ ፡ ከንቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ሆነው ፡ ይቀራሉ ። አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ውስጥ ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ የሚያኰራ ፡ ሕግ ፡ አላት ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ያስደስታልም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ መሻሻል ፡ መጠን ፡ የሕግ ፡ ባለሞያዎች ፡ በትምህርታቸውና ፡ በሥራቸው ፡ የሠለጠኑና ፡ የተጠናቀቁ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። የሕግ ፡ መሻሻል ፡ ያገር ፡ መሻሻል ፡ የተያያዘና ፡ የተግመረ ፡ ነው ።

በዳኝነት ፡ እውነትን ፡ መፈለግ ፡ ለሥራም ፡ ምርጥ ፡ ሰው ፡ መፈለግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። የሚመረጠውም ፡ ሕግን ፡ ከተማሩና ፡ ከራሳቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ከሚያበልጡ ፡ መካከል ፡ ነው ። ጠበቃም ፡ በውነት ፡ ከሠራ ፡ ዳኛ ፡ ነው ።

ትምህርታችሁን ፡ በምትማሩበት ፡ ጊዜ ፡ እያጋጠመን ፡ እተማሪ ፡ ቤታችሁ ፡ እንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደር ስን ፡ ተመልከተናል ። ካሁን ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፤ ሰው ፡ ከሕያንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ቢማር ፡ የበለጠ ፡ ነው ። በኋላም ፡ በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ ቢማር ፡ ፈቃድን ፡ የሚያበሪታና ፡ ፈቃድ ፡ እያሽነፈው ፡ ትምህርትን ፡ ለማጠራቀም ፡ የሚቻል ፡ መሆኑም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተናገርነው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ፤ አሁን ፡ እደረሳችሁበት ፡ ላይ ፡ በርትታችሁ ፡ በመማራችሁ ፡ የተናገርነው ፡ ሁሉ ፡ እድንጋይ ፡ ላይ ፡ እንደተዘራ ፡ አይቁጠርም ። እለምለም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በቅሎ ፡ አፍርቷል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ይሽም ፡ ግና ፡ ወደፊት ፡ እንዲሰፋፋ ፡ ተስፋችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ። እናንተም ፡ የዛሬ ፡ ተመራቂዎች ፡ ይህን ፡ በመገንዘብ ፡ የገጠማችሁን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ አልፋችሁ ፡ ለዚህ ፡ ደረጃ ፡ በመድረሳችሁ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ሌሎችም ፡ የናንተን ፡ እርምጃ ፡ ተከትለው ፡ ትምህርታቸውንና ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለማሻሻል ፡ መሞከራቸው ፡ የሚያስመሰግናቸው ፡ ነው ።

ሌሎችም ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ እንዲከተሉ ፡ ተስፋ ፡ የምናደርግበት ፡ ነው ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ የተቀበሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ እጥፍ ፡ ሊሆን ፡ መቻሉን ፡ በናስብ ፡ መንፈሳችን ፡ የሚረካው ፡ ወደፊት ፡ የሚመጣውን ፡ የበለጠ ፡ በብዛት ፡ እንዲገኝ ፡ ያደርገዋል ፡ በማለት ፡ ነው ። ዛሬም ፡ በመካከላችሁ ፡ ዳኞችና ፡ የሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ በመገኘታቸው ፡ ላገልግሎታቸው ፡ ትጋት ፡ ያሳየናል ።

ትምህርት ፡ በሰው ፡ ዕድሜ ፡ ውስጥ ፡ የማያቋርጥ ፡ ገቢያ ፡ ነው ። ጋብቻ ፡ ሥራ ፡ መያዝ ፡ ጉጀ ፡ መውጣት ፡ በዕድሜ ፡ መቁየት ፡ እነዚህ ፡ የትምህርትን ፡ ገቢያ ፡ ሊያጸርጡት ፡ ወይም ፡ እንደማይታለፍ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሊቁጠሩ ፡ አይገባም ።

ለዚህም ፡ እናንተ ፡ ራሳችሁ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ። በትምህርት ፡ ራሳችሁን ፡ በማሻሻል ፡ ለሳስጉዳዩ ፡ የምታቀርቡትን ፡ አገልግሎት ፡ ከማሻሻላችሁም ፡ በላይ ፡ አገራችሁን ፡ በጠቅላላው ፡ አሻሽላችኋል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። እናንት ፡ እንደዚህ ፡ ለማሻሻል ፡ ስትበረቱ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ ትምህርት ፡ እንዲገበዩ ፡ የሰበሰብናቸውን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ለትምህርታቸው ፡ ያጠነከራቸዋል ። ልጆቹም ፡ ተምረው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እባቶቻቸውን ፡ ሊንቅፍ ፡ ቸው ፡ እይችሉም ፤ አባቶችም ፡ የትምህርት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ተምረዋልና ፡ ይልቁንም ፡ ሲያከብሩ ፡ ዋቸው ፡ ይችላሉ ።

ይህም ፡ የደረሳችሁበት ፡ ደረጃ ፡ እንደየሥራችሁ ፡ በቂ ፡ ታዋቂነት ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ። እናንተን ፡ በሞያ ችሁ ፡ ሌላውም ፡ ሁሉ ፡ በየሞያው ፡ ራሱን ፡ የማሻሻል ፡ የትምህርት ፡ መንፈስ ፡ ሲያድርበት ፤ እገሌጋይነቱ ፡ የተሻሻለ ፡ ራሱንና ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ለመጥቀም ፡ የሚችል ፡ ዜጋ ፡ ይሆናል ። እግዚአብሔር ፡ ወደፊት ፡ እናንተንም ፡ ያበርታችሁ ፡ ሌላውንም ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ያሰብንበትን ፡ እንዲበረታታ ፡ ያድርገው ።

HIS IMPERIAL MAJESTY'S
Remarks to the First Graduating Class of the
EXTENSION PROGRAM at the FACULTY OF LAW
HAILE SELLASSIE I UNIVERSITY
November 24, 1964

We are indeed pleased to congratulate this class who have today received Certificates in law from the University — and to the teachers who have made your accomplishment possible by planning, organizing and carrying out of this pioneer project.

You may rightly take great pride in your accomplishment, just as We do.

The administration of justice, in a modern state, demands well trained qualified persons at every level. The introduction of the codes and the revised Constitution of Ethiopia, as well as other legislation continuously coming from Parliament and the Government, has dramatically changed Ethiopia's legal system. The law of the Empire is now modern, complex and scientific in the sense that it has been prepared by experts after careful study. The administration of the law of the Empire increasingly demands highly trained persons.

In a real sense the development of the nation depends upon the development of our legal institutions.

The proper administration of justice requires a research for truth, therefore, the judicial function requires highly selected men. Judges shall be chosen from among those who studied law, and who sacrifice their personal interests to their duties.

An advocate who discharges his duty honestly is a judge. So the need for persons trained in law is obvious.

Thus We are pleased to learn that others are following hard upon the footsteps of this class. We are pleased to know that soon the number of Ethiopian lawyers holding a university degree in law will be virtually doubled.

We are especially pleased to see that so many judges and other civil servants and advocates are taking time to continue their education even as they continue to perform their regular daily duties.

Education is an ongoing task. The obligation to improve oneself does not cease simply because one has a regular job. This is certainly true for those who work in the administration of law and in legal counselling. We would urge that these persons must do all they can to improve, continuously, their professional capacities through further study.

Members of this graduating class: by sacrificing your time you have advanced yourselves and the nation.

We are confident that the qualification you have earned today will be recognized within the legal profession. We believe it should. We believe, too, that the professional attainment to be achieved by other students now studying law in other programs of the Law School must be recognized.

Ethiopia needs a modern legal profession just as she needs the modern legal system she is building. The one cannot exist without the other.

You — all of you who are taking University training in law — are helping in the task of building a profession.

I congratulate you. I congratulate this class: take pride in what you have done by serving with continuing zeal and loyalty the Law of Our Empire.

Complete text as reported in the Ethiopian Herald, November 25, 1964. ed

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ መሻሻል ፡ ጠቃሚ ፡ ደረጃ ፡ መሆኑን ፡ በመገ መት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ ግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔትን ፡ መቋቋም ፡ መሠረቱ ። መጽ ሔቱ ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀጥልና ፡ ተግባሩን ፡ እንዲያስፋፋ ፡ ፍላጎት ፡ ያደረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የመጽሔቱ ፡ ጠባቂና ፡ ደጋፊ ፡ እንዲሆኑ ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጅ ፡ ቦርድ ፡ ጋበዘ ። በማብዣውም ፡ መሠረት ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተዘርዝሮ ፡ የሚገኙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ፡ ሆነዋል ።

ክቡር ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ በሻሕ ፡ በላይነህ ፡
የተከበሩ ፡ ብላታ ፡ ማትያስ ፡ ህለተ፡ወርቅ፡
የተከበሩ ፡ አቶ፡ሐጐስ፡ተወልደ ፡ መድንን
የተከበሩ ፡ ብላታ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ፡
የተከበሩ ፡ ዶክተር ፡ ዊልያም ፡ ቡሐጂያር ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሐ ፡ አወቀ ፡

ክቡር ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡
ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ አስፍሃ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ ማሞ ፡ ታደሰ ፡
ክቡር ፡ ኰ/ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ ሰዩም ፡ ሐረጉት ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ አሰፋ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ብርሃን ፡ መስቀ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ ከተማ ፡ አበበ ፡
የተከበሩ ፡ የመ/አ ፡ ግርማ ፡ ወ/ጊዮርጊስ ፡

አቶ ፡ ለማ ፡ ወልደ ፡ ሰማያት ፡
አቶ ፡ ለገሠ ፡ አበበ ፡
ዶክተር ፡ ማርቼሎ ፡ ሎምባርዲ ፡
ሚስተር ፡ ሲቲፕን ፡ ሎውንስቲን ፡
ሚስተር ፡ ኤን ፡ ሐማዊ ፡
ሚስተር ፡ ጄ ፡ ሐማዊ ፡
አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ መዊኤል ፡ መብራቱ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ተሰማ ፡

አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ በሪሁን ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ሚካኤል ፡ ፋሲል ፡
አቶ ፡ ማሀሙድ ፡ ኑርሁ ፡ ሳይን ፡
ሴ/ኰ፡ ምህረት ፡ ገብረሰላም ፡
ሚስተር ፡ ኬኔት ፡ አር ፡ ሬደን ፡
ዶክተር ፡ ሳባ ፡ ህባቹ ፡
ሚስተር ፡ አራኪል ፡ ሳካድጅያን ፡
ሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ኤ ፡ ሴድለር ፡
ስኮት ፡ እና ፡ ስኮት ፡ የሕግ ፡ ጠበቆች ፡
አቶ ፡ ቀንዓ ፡ ጉማ ፡

አቶ ፡ በለጠ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ በላቸው ፡ አሥራት ፡
አቶ ፡ በላይ ፡ መንግሻ ፡
ወይዘሮ ፡ በልዩ ፡ ወርቅ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
ሚስተር ፡ ሪስል ፡ በርማን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡
ደጃዝማች ፡ በቀለ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ናዲ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ገብረአምላክ ፡
አቶ ፡ ቡልቻ ፡ ደመቅሳ ፡
ሌ/ኮ፡ ብርሃን ፡ ወልደየስ ፡
አቶ ፡ ብርሃኔ ፡ ክፍለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገሠሠ ፡
አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ ምትኩ ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ ደገፋ ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ ጐሹ ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡
ባላምባራስ ፡ ተሰማ ፡ ወንድምነህ ፡
ፊታውራሪ ፡ ተስፋ ፡ ማርያም ፡ ስብሀት ፡
አቶ ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ ኢያሱ ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዱባለ ፡
ባላምባራስ ፡ ተሾመ ፡ ገታው ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
ቀኛዝማች ፡ ተገኘ ፡ ሐበሺ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ሚስተር ፡ ማይክል ፡ ቶፒንግ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አውላቸው ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ሽንቁጤ ፡
ካፕቴን ፡ ኃይሉ ፡ አርሰዴ ፡
አቶ ፡ ነብየ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ይፍሩ ፡
ቀኛዝማች ፡ ኑረዲን ፡ ዘይን ፡
አቶ ፡ ንርአዮ ፡ ኢማይያስ ፡
ሌ/ኮ፡ አህመድ ፡ አሚኑ ፡
ሼክ ፡ አህመድ ፡ አስማን ፡
አቶ ፡ አለ ፡ አም ፡ ስበርሃቱ ፡
አቶ ፡ አመዴ ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ደግፌ ፡
አቶ ፡ አማኑኤል ፡ ዐምደ ፡ ሚካኤል ፡
ሚስስ ፡ ማሪካ ፡ አርቫኒቶፖሎ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ መታፈሪያ ፡
አቶ ፡ አስፍሃ ፡ ካሣዬ ፡
አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ አባተ ፡ ወንድምአገኘሁ ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አደራ ፡ ፍራንሷ ፡
አቶ ፡ አድማሴ ፡ ገሠሠ ፡
አቶ ፡ አድነው ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ አድነው ፡ ኪዳኔ ፡
አቶ ፡ አጽብሀ ፡ ሩንታ ፡

አቶ ፡ ኢያሱ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያት ፡
ዶክተር ፡ ኢዮብ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡
ደጃዝማች ፡ ኢድሪስ ፡ ለጃም ፡
ዶክተር ፡ ሞሪስ ፡ ጂ ፡ ኤሊዮን ፡
አቶ ፡ እሸቴ ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ እንዳለ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ እንዳለ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ከልል ፡
አቶ ፡ ክበደ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡
ዶክተር ፡ ስታንሊ ፡ ኪርኮር ፡
ሚስተር ፡ ማይክል ፡ ኬንድሪድ ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ወ/ማርያም ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ስዩም ፡
አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ ውቤ ፡ ወልደየስ ፡
ሚስተር ፡ ፍራንክ ፡ ዲ ፡ ዊንስተን ፡
አቶ ፡ ዋቅጅራ ፡ ቦንሣ ፡
አቶ ፡ የሸዋ ፡ ወርቅ ፡ ኃይሉ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ ኃይሉ ፡
ሌ/ኮ ፡ ደማ ፡ ዘንማ ፡ እማዜር ፡
አቶ ፡ ደስታ ፡ ገብሩ ፡
ሚስተር ፡ ጂ ፡ ኤን ፡ ደባስ ፡
ባላምባራስ ፡ ገመዳ ፡ ኡርጌሣ ፡
ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ሐና ፡ ቅጣው ፡
ባሻ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘዑሉ ፡
አቶ ፡ ገብረየሱስ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ክብረት ፡
ዶክተር ፡ ፊ ፡ ግሪቨን ፡
አቶ ፡ ጎይቶም ፡ በይን ፡
አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ ተፈሪ ፡
ሚስተር ፡ ስታንሊ ፡ ፊሸር ፡
ሚስተር ፡ ዶናልድ ፡ ኢ ፡ ፓራዲስ ፡
ሚስተር ፡ ጀምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖል ፡
ዶክተር ፡ ጃክስ ፡ ፒ ፡ ኤም ፡ ቫንደርሊንደን ፡

የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነትን ፡ ለመሆን ፡ የሚመኝ ፡ ሰው ፡ በሚከተለው ፡ አድራሻ ፡ ቢያስታውቀን ፡ መልካም ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በኩል ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

PATRONS OF THE JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

The Journal of Ethiopian Law was inaugurated by His Imperial Majesty Haile Sellassie I in the summer of 1964 as an important step in the development of Ethiopia's legal system. Subsequently, the Board of Editors of the Journal has invited those who are interested in the continuation and expansion of the Law Journal's activities to express their support by becoming Patrons of the Journal. The following persons have become Patrons of the Journal of Ethiopian Law:

H.E. Afenegus Kitaw Yitateku
Hon. Ato Bashahe Belayeneh
Hon. Blatta Matias Hiletwork
Hon. Ato Hagos Tewolde Medhin
Hon. Blatta Haile Wolde Kidan
Hon. Dr. William Buhagiar
Hon. Ato Negussie Fitawake
H.E. Tsehafi Taezaz Aklilu Habte Wolde
H.E. Bitwoded Asfeha Woldemicael
H.E. Ato Mammo Tadesse
H.E. Col. Leghesse Wolde Hanna
H.E. Ato Seyoum Haregot
H.E. Ato Assefa Gebre Mariam
H.E. Deja. Berhane Meskel Wolde Sellassie
H.E. Ato Ketemma Abebe
Hon. Lt. Girma Wolde Giorgis

Ato Abate Wondemagegnehu
Ato Aberra Jembere
Ato Adarra François
Ato Adenew Haile Michael
Ato Adenew Kidane
Ato Admasse Gessesse
Dr. Maurice J. Aelion
Lt. Col. Ahmed Aminu
Sheik Ahmed Osman
Ato Aklilu Atlabatchew
Ato Aklilu Bete Mariam
Ato Ali M. S. Berhatu
Ato Amanuel Amdemichael
Ato Amare Degefe
Ato Amede Lemma
Mrs. Marica Arvanitopoulo
Ato Asfeha Kahsai
Ato Assefa Liban
Ato Assefa Metaferia
Ato Atsheba Fanta
Dejazmatch Bekele Beyene
Ato Bekele Demissie
Ato Bekele Gebre Amelak
Ato Bekele Habte Michael
Ato Bekele Nadi
Ato Bekele Tesfaye
Ato Belatchew Asrat
Ato Belay Mengesha
Ato Belete Wolde Sellassie
Woz. Beleyu Work Gebre Meskel
Ato Berhane Kefle Mariam
Lt. Col. Berhane Woldeyes
Mr. Russell Berman
Ato Bulcha Demeksa
Lt. Col. Dama Zeng Egzer
Mr. G. N. Debbas

Ato Desta Gebru
Ato Endale Wolde Micael
Ato Endale Mengesha
Ato Eshete Berhane
Ato Eyassu Gebre Hawariat
Dr. Eyob Gebrecristos
Mr. Stanley Z. Fisher
Ato Gebreyesus Haile Mariam
Kegn. Geta Gebre Hanna Kitaw
Bashai Gebre Meskel Zeilo
Balambarass Gemeda Urgessa
Ato Getachew Asfaw
Ato Getachew Kibret
Ato Goytom Beyen
Dr. Philippe Graven
Dr. Saba Habachy
Ato Haile Leoul Habte Giorgis
Ato Haile Sellassie Awulatchew
Capt. Hailu Arsede
Ato Hailu Shenqute
Mr. G. Hamawi
Mr. N. Hamawi
Dejazmatch Idris Lejam
Ato Kanaa Guma
Ato Kassa Beyene
Ato Kebede Gebre Mariam
Ato Kebede Kelel
Mr. Michael Kindred
Dr. Stanley Kirkor
Ato Legesse Abebe
Ato Lemma Wolde Semayat
Dr. Marcello Lombardi
Mr. Steven Lowenstein
Ato Makonnen Tessema
Lt. Col. Meherete Gebre Selam
Ato Mengesha Wolde Amanuel
Ato Mesfin Berhe
Ato Mesfin Fanta
Ato Mewail Mebratu
Ato Michael Fasil
Ato Muhamud Nurhu Sain
Ato Mulugeta Berihun
Ato Mulugeta Wolde Giorgis
Ato Nabiye Leoul Kifle
Ato Negash Yifru
Ato Negga Tessema
Ato Nirayo Esayas
Kegnazmatch Nuridine Zayenu
Mr. Donald E. Paradis
Mr. James C.N. Paul
Mr. Kenneth R. Redden
Mr. Arakel Sakadjian
Scott and Scott, Attorneys at Law
Mr. Robert A. Sedler
Ato Tadesse Tekle Giorgis
Ato Tefera Degefe
Ato Tefera Metiku
Ato Tefferi Berhane
Ato Tefferi Lemma
Kegnazmatch Tegegne Habesh
Ato Tereffe Gessesse
Fitawrari Tesfa Mariam Sebhat
Ato Tesfa Zion Eyassu
Ato Tesfaye Dubale
Ato Tesfaye Kebede
Ato Teshome Gebre Mariam
Balambarass Teshome Getaw
Ato Teshome Haile Mariam

Ato Tessema Goshu

Balambarass Tessema Wondameneh

Ato Tessema Wolde Yohannes

Mr. Michael Topping

Ato Tsegaye Tefferi

Dr. Jacques P.M. Vanderlinden

Ato Wakgira Bonsa

Mr. Frank D. Winston

Ato Wolde Amanuel Wolde Mariam

Ato Wolde Leoul Seyoum

Ato Woldu Berhe

Ato Woube Woldeyes

Ato Yeshewa Work Hailu

Ato Yilma Hailu

Anyone desiring to become a Patron of the Journal of Ethiopian Law should notify the Journal of Ethiopian Law, The Faculty of Law, Haile Sellassie I University, P. O. Box 1176, Addis Ababa.

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ።

ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ በዓመት ፡ ሹለት ፡ ጊዜ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚዘጋጅ ።

(ጀኖ ፡ የኢት. ሕግ. መ. ተብሎ ፡ ይጠቀስ ።)

የቦርድ ፡ አባሎች ።

አቶ ፡ በላቸው ፡ ዐሥራት ፡ ሰብሳቢ ፤

ዶክተር ፡ ፊሊፕ ፡ ግሪቨን ፡ — አቶ ፡ ንርአዮ ፡ ኢሳይያስ ፡

ዲን ፡ ጂምስ ፡ ሲ. ኤን. ፖል ፡ — ፕሮፌሰር ፡ ኬኔስ ፡ ሬደን ፡

አቶ ፡ ነጋ ፡ ተሰማ ፡ — ሚስተር ፡ ስቲቨን ፡ ሎውንሽተን ።

አዘጋጂዎች ።

ሚስተር ፡ ስቲቨን ፡ ሎውንሽተን ፡
ፕሮፌሰር ፡ ኬኔስ ፡ ሬደን ፡ — የመጽሔቱ ፡ ዋና ፡ አዘጋጆች ።

ሚስተር ፡ ስታንሊ ፡ ዚ. ፊሸር ፡ — የዝግጅቱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ኀላፊ ።

ማይክል ፡ ኪንድርድ ፡ — የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ መግለጫዎች ፡ አዘጋጅ ።

ሚስተር ፡ ኖርማን ፡ ሲንገር ፡ — የማሳተሙ ፡ ተቈጣጣሪና ፡ አዘጋጅ ።

አቢዩ ፡ ገለታ ፡
አሌክሳንድራ ፡ ሐማዊ ፡
ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ከፍሌ ፡
ሰላሙ ፡ በቀስ ፡ — ተባባሪ ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጆች ።

ስለ ፡ ማንኛውም ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ ያላችኹን ፡ ሐሳብና ፡ ጥያቄ ፡ ለመጽሔቱ ፡ ዋና ፡ አዘጋጂዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ የፖስታ ፡ ሣጥን ፡ ቍጥር ፡ 1176 ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ (ኢትዮጵያ ፡) ብላችኹ ፡ ጣፉ ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published twice annually at the Faculty of Law of Haile Selassie I University
In co-operation with the Ministry of Justice
(to be cited as: II J. ETH. L.)

EDITORIAL BOARD

Justice Belatchew Asrat, Chairman

Dr. Philippe Graven

Dean James C.N. Paul

Ato Negga Tessema

Ato Nirayo Esayas

Professor Kenneth Redden

Mr. Steven Lowenstein

EDITORIAL STAFF

Editors
Steven Lowenstein — Kenneth Redden

Editor for Administration
Stanley Z. Fisher

Editor for Court Reports
Michael Kindred

Press Editor
Norman Singer

Associate Editors
Abiyu Geleta
Alexandra Hamawi
Nabiyelul Kifle
Selamu Bekele

Please address correspondence to the Editors, *Journal of Ethiopian Law*, Box 1176, Addis Ababa, Ethiopia

ማውጫ ።

TABLE OF CONTENTS

የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ማውጫ ።

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

TABLE OF CASES REPORTED

Supreme Imperial Court

High Court

መግለጫዎች ።

የሚከተሉት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ጉዳዮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። የዐማርኛው ፡ ፍርድ ፡ መደበኛ ፡ (አፈሻል ፡) ስለኾነ ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ቀድሞ ፡ ይገኛል ። ስለነዚህም ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ዳኞች ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ተወሰኑት ፡ ጉዳዮች ፡ በዐማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ኹለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፡ መጻፋቸውን ፡ ማስተዋል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ አስተያየቶች ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ የተተረጐሙ ፡ አይደሉም ። እያንዳንዱ ፡ ፍርድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ በዳኞች ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ሥረ ፡ ነገሩና ፡ ስለ ፡ መጨረሻው ፡ ውሳኔ ፡ ስምምነት ፡ አለ ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ በሦስት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ስለኾኑ ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ የተሰየው ፡ አስተያየት ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ፍርዱን ፡ ተከታትሎ ፡ በዐማርኛም ፡ በእንግሊዝም ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

REPORTS

The following are twelve cases decided by the Supreme Imperial and the High Courts of Ethiopia. The Amharic judgment is official and always precedes the English. It is important to note that in those cases heard before mixed benches of both Ethiopian and foreign judges, separate opinions are written in Amharic and in English. These opinions are not translations of one another, but are independent judgments based upon common agreement among the judges as to the principles and final outcome of each case. In addition, dissents from the majority decisions are published in three of the cases immediately after the majority opinions in Amharic and in English.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አንደኛ ፡ ችሎት ።

መኰንን ፡ ወልደየስ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፴፭/፻፬ ፡ ዓ. ም ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ — በቸልተኛነት ፡ ስለመበደል —"የሚያ ፡ ተግባር ፡" የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ትርጕም — የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፳፯ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት — የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ዝርዝር ።

የአቶብስ ፡ ነጂ ፡ የኾነው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አውራ ፡ ጕዳናው ፡ በደንብ ፡ በማይታይበት ፡ ወቅት ፡ ከፈቱ ፡ ያለውን ፡ መኪና ፡ አቀድማለኹ ፡ ሲል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይመጣ ፡ የነበረውን ፡ መኪና ፡ ገጭቶ ፡ በተገጭው ፡ መኪና ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ በመግደሉ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፳፯ ፡ (፪) መሠረት ፡ በከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ ሰው ፡ ገድለኻል ፡ ብሎ ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ ፈረደ በት ። ስለዚህም ፡ ይግባኙ ፡ ቀረበ ።

ውሳኔ ፤ - ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የፈረደው ፡ ጸደቀ ።

፩ ፤ አውራ ፡ ጕዳናው ፡ በደንብ ፡ በማይታይበት ፡ ወቅት ፡ መኪናን ፡ መቅደም ፡ የቸልተኛነት ፡ ጠባይ ፡ ነው ።

፪ ፤ የአንድ ፡ ሰው ፡ ለጊዜው ፡ ከነመላ ፡ አካላቸው ፡ በሱ ፡ ሥር ፡ የሚገኙን ፡ ሰዎች ፡ በተለየ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲጠብቅ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሲኾን ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፳፯ ፡ (፪) መሠረት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ "ሕይወትን ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚያ ፡ ተግባር ፡" ይኖረዋል ። ሐኪሞች ፡ ነርሶች ፡ የአውሮፕላን ፡ ነጂዎች ፡ እና ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የተ ሽከርካሪ ፡ ነጂዎች ፡ የሚያ ፡ ተግባር ፡ ያላቸው ፡ ምሳሌ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ባለሚያ ፡ በእንቀጽ ፡ ፭፻፳፯ ፡ ፪) ፍች ፡ መሠረት ፡ "ልዩ ፡" ተግባር ፡ የሚኖረው ፡ በሱ ፡ ዐላፊነት ፡ ለሚገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ነሕዝብ ፡ የሚያገለግል ፡ የተሽከርካሪ ፡ ነጂ ፡ በተሽከርካሪው ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ዐላፊ ፡ እንደኾነ ።

፬ ፤ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ክሱ ፡ የሚጠነክርበትን ፡ ምክንያት ፡ ካልዘረዘረ ፡ ስንኩል ፡ ነው ።

ግንቦት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፱፪ ፡ ዓ. ም ። ዳኞች ፤- አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ታደሰ ፡ ሙንባሻ ፡ ዶክተር ፡ ዊሊያም ፡ ቦሐጅያ ር ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ። ይህ ፡ ይግባኝ ፡ በከፍ ተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፸፬/፻፫ ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ ጥር ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፱፬ ፡ ዓ. ም. የከሳሹ ፡ በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰበት ፡ አን ቀጽ ፡ ፭፻፳፯ ፡ (፪) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የወሰነውን ፡ ውሳ ኔና ፡ በዐምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ እንዲቀጣ ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ የቀ ረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተከሰሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፯ ፡ የተመለከተውን ፡ በቸልተኛነት ፡ የሰው ፡ መግደል ፡ ወን ጀል ፡ ሠርቶአል ፡ በማለት ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ኹኖ ፡ ተገኝቶ ፡ የዐምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ የተፈረደበት ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፯ ፡

ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤና ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ አስተዋይነት ፡ እንዲያደርግ ፡ የሚያ ፡ ተግባሩ ፡ የሚያስገድደውን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ ቀርቶአልና ፡ ቅጣቱ ፡ ሊከብድበት ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ነው ። ይግባኙም ፡ የቀረበው ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ የተባለበትም ፡ ምክንያት ፡ (ሀ) ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የፈረደበት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሳያገኝ ፡ ነው ፤ (ለ) ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የተከሰሰው ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፳፭ ፡ ዅኖ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶአል ፡ ሲል ፡ ጥፋተኛ ፡ ስላደረገው ፡ በሕግ ፡ በሆል ፡ ተሳስቶአል ፤ (ሐ) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተገቢነቱ ፡ እንደይገባኝ ፡ ባዩ ፡ ባለ ፡ መኪና ፡ ነጂ ፡ ላይ ፡ ሳይ ዅን ፡ የሚያ ፡ ሥራቸውን ፡ በቸልተኝነት ፡ በሚሠሩ ፡ ሐኪሞችና ፡ ነርሶች ፡ በሌሎቹም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሚያ ፡ ሥራ ፡ በአላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ነው ።

መዝገቡ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበለት ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ ያረጋገጠው ፡ ዅነታ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አውቶቡስ ፡ ነጅ ፡ መኾኑን ፡ ነሐሴ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ቍጥር ፡ 6135 ፡ የኾነውን ፡ አውቶቡስ ፡ ይነዳ ፡ እንደነበረና ፡ ከወዲስ ፡ አበባ ፡ ፭፻፳፭ ፡ ኪሎሜትር ፡ ርቀት ፡ ቀሊቲ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ገደማ ፡ ሲኾን ፡ ከወደፊቱ ፡ ከሚመጣው ፡ ቍጥሩ ፡ 9956 ፡ ከኾነ ፡ ቮልስዋገን ፡ አውቶሞቢል ፡ ጋራ ፡ እንደተጋጨና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ቮልስዋገኑ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ መሞታቸውን ፡ በአውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ያልደረሰባቸው ፡ መኾኑን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አውቶቡሱን ፡ ከሌላ ፡ አውቶቡስ ፡ ኋላ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ይነዳ ፡ ስለነበር ፡ በዐቢራው ፡ ምክንያት ፡ መንገዱ ፡ በቅጡ ፡ የማይታይ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከፊት ፡ ፊቱ ፡ የሚኼደውን ፡ አውቶቡስ ፡ ለመቅደም ፡ ሲሞክር ፡ ከመንገዱ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ በሆል ፡ ማድላቱንና ፡ አውቶቡሱ ፡ ቀጥታውን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ከሚመጣው ፡ ቮልስዋገን ፡ መኪና ፡ ጋራ ፡ መጋጨቱን ፡ ነው ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያቀረበው ፡ ክርክር ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መንገዱን ፡ ዐቢራ ፡ ሸፍኖት ፡ ለዐይን ፡ በትክክል ፡ በማይታይበት ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ የሚኼደውን ፡ አውቶቡስ ፡ እቀድማለኹ ፡ ብሎ ፡ አውቶቡሱን ፡ ከቮልስዋገን ፡ መኪና ፡ ጋራ ፡ በማጋጨቱ ፡ በቮልስዋገኑ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ የሞቱት ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ቸልተኝነት ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ነው ።

በዚህ ፡ በይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ውሳኔ ፡ በሰጠበት ፡ ነገር ፡ ግልጽ ፡ የኾነ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቦለታል ። የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ጠበቃ ፡ እንዳቀረቡት ፡ ክርክር ፡ ምስክሮቹ ፡ የመሰከሩት ፡ ቃል ፡ ተቃራኒ ፡ የለበትም ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ በሚነሣው ፡ ዐቢራ ፡ መንገዱ ፡ ተሸፍኖ ፡ በደንብ ፡ ለማየት ፡ በማይቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ከወደፊት ፡ የሚጣውን ፡ መኪና ፡ ሳያይና ፡ ሳይ፟ለከት ፡ ከፊት ፡ የሚኼደውን ፡ መኪና ፡ ለመቅደም ፡ የሚሽቀዳደም ፡ መኪና ፡ ነጅ ፡ ቸልተኛና ፡ ጥፋተኛ ፡ መኾኑ ፡ እያጠራጥርም ፤ ስለዚህ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ጥፋት ፡ በኾነ ፡ የቸልተኝነት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የወሰ ነው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ።

የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ጠበቃ ፡ በአቀረቡት ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የተከሰሰው ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፭ ፡ በተመለከተው ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላው ፡ ሲኾን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፭ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) በተመለከተው ፡ ቅጣትን ፡ በሚያ ከብደው ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ያደረገው ፡ አሳማቢ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል ። ይህን ፡ በመሰለው ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚያ ፡ ተግባሩ ፡ የሚያስገድደው ፡

ልዩ ፣ ጥንቃቄ ፣ ማጉደሉን ፣ በክሱ ፣ ጽሑፍ ፣ ውስጥ ፣ ገልጦ ፣ መጣፍ ፣ አስፈላጊ ፣ ነበር። በቍጥር ፣ ፭፻፳፯ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩) እና ፣ (፪) የተመለከተው ፣ በጠቅላላው ፣ ጥፋት ፣ በኾነ ፣ ቸልተኝነት፡ሰውን ፣ ስለመግደል ፣ ወንጀል ፣ ቢኾንም ፣ በንኡስ ፣ ቍ. (፪) የተመለከተው ፣ የወንጀል ፣ አሠራር ፣ ጥፋተኛ ፣ ኹኖ ፣ የተገኘውን ፣ ሰው ፣ ቅጣት ፣ ያከብድበታል ። ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ክስ ፣ ሲያቀርብ ፣ ተከሳሹ ፣ የተከሰሰበትን ፣ ወንጀል ፣ ደኅና ፣ አድርጎ ፣ እንዲያውቀውና ፣ ለመከላከል ፣ እንዲችል ፣ ይኸው ፣ ኹነታው ፣ ተገልጾ ፣ በክሱ ፣ ጽሑፍ ፣ ውስጥ ፣ መጣፍ ፣ ነበረበት ። በክሱ ፣ ውስጥ ፣ ይህ ፣ ኹኔታ ፣ ተገልጾ ፣ ስላልተጣፈ ፣ የክሱ ፣ ጽሑፍ ፣ ጒድለት ፣ ያለበት ፣ መስሎ ፣ ታይቷል ። ነገር ፣ ግን ፣ የክሱ ፣ ጽሑፍ ፣ ጒድለት ፣ ቢኖርበትም ፣ በዚህ ፣ ነገር ፣ ወደፊት ፣ በሚገለጠው ፣ ምክንያት ፣ ትክክለኛና ፣ ሕግን ፣ የተከተለ ፣ ፍርድ ፣ እንዳይሰጥ ፣ አያግድም ።

የይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ጠበቃ ፣ የአቀረቡት ፣ ኹለተኛው ፣ ክርክርና ፣ የይግባኝ ፣ ምክንያት ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፭ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፪) የተመለከተው ፣ ተገቢነት ፣ ጥንቃቄ ፣ በማጉደልና ፣ በቸልተኝነት ፣ በሚሠሩ ፣ ሐኪሞችና ፣ ነርሶች ፣ ላይ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የአውቶቡስ ፣ ነጂ ፣ በኾነው ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ ተገቢነት ፣ የለውም ፣ በማለት ፣ ነው ። ጥፋት ፣ ባለበት ፣ ቸልተኝነት ፣ የሰው ፣ መግደል ፣ ወንጀል ፣ የሠራ ፣ ሰው ፣ ወንጀሉን ፣ ያደረገው ፣ የሰውን ፣ ሕይወት ፣ ከሞት ፣ አደጋ ፣ ለማዳን ፣ የሚያ ፣ ተግባሩ ፣ የሚያስገድደውን ፣ ጥንቃቄ ፣ በማጉደል ፣ የኾነ ፣ እንደኾነ ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፭ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፪) የተመለከተው ፣ ሕግ ፣ ቅጣቱን ፣ ያከብድበታል ። በዚህ ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፭ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፪) የተመለከተውን ፣ ሕግ ፣ ሲያነቡት ፣ ሕይወትን ፣ ከሞት ፣ አደጋ ፣ ለማዳን ፣ ልዩ ፣ ጥንቃቄ ፣ እንዲያደርጉ ፣ የሚያ ፣ ሥራቸው ፣ ያስገድዳቸዋል ፣ የተባሉት ፣ ሰዎች ፣ ሐኪሞችና ፣ ነርሶች ፣ መኾናቸው ፣ በሐሳብ ፣ ትዝ ፣ ቢልም ፣ በተባለው ፣ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ የተመለከተው ፣ ዐላፊነት ፣ በሐኪሞችና ፣ በነርሶች ፣ ብቻ ፣ የተወሰነ ፣ አይደለም ። “የሚያ ፣ ተግባር ፡” የሚለው ፣ አነጋገር ፣ ሰፊ ፣ ስለኾነ ፣ በሥራቸው ፣ ምክንያት ፣ ለሌሎች ፣ ሰዎች ፣ ጥንቃቄ ፣ ማድረግ ፣ ለሚገባቸው ፣ ሰዎች ፣ ኹሉ ፣ ተገቢነት ፣ አለው ። “የሚያ ፣ ተግባር ፡”የሚለው ፣ ቃል ፣ በአውሮፕላን ፣ ነጂዎችና ፣ በአውቶቡስ ፣ ነጅዎች ፣ በሌሎችም ፣ ለሕዝብ ፣ የሚያገለግሉ ፣ ተሽከርካሪዎች ፣ ነጅዎች ፣ ላይ፣ ተገቢነት፡ አለው። ነገር ፣ ግን ፣ እንደዚህ ፣ ያሉት ፣ ሰዎች ፣ ልዩ ፣ ጥንቃቄ ፣ ማድረግ ፣ የሚገባቸው ፣ በየትም ፣ ቦታ ፣ ለሚገኘውም ፣ ሰው ፣ ኹሉ ፣ ሳይኾን ፣ በሚያ ፣ ሥራቸው ፣ ምክንያት ፣ ግንኙነት ፣ ላላቸው ፣ ሰዎች ፣ ነው ። ማለት ፣ አውሮፕላን ፣ ነጅዎች ፣ በአውሮፕላን ፣ ለሚጓዙት ፣ መንገደኞች ፣ አውቶቡስ ፣ ነጂዎች ፣ በአውቶቡስ ፣ ውስጥ ፣ ለሚጓዙ ፣ መንገደኞች ፣ ነው ። እነዚህ ፣ የሚያ ፣ ሥራ ፣ ያላቸው ፣ ሰዎች ፣ ለማንኛውም ፣ ለእገረኛ ፣ መንገደኛ ፣ ልዩ ፣ ጥንቃቄ ፣ ለማድረግ ፣ ግዴታና ፣ ዐላፊነት ፣ የለባቸውም ።

እነዚህ ፣ የሚያ ፣ ሥራ ፣ ያላቸው ፣ ሰዎች ፣ ለእገረኞች ፣ መንገደኞች ፣ ወይም ፣ ከአውሮፕላኑና ፣ ከአውቶቡሱ ፣ ውጭ ፣ ለሚገኙት ፣ የሚያደርጉት ፣ ጥንቃቄ ፣ ማንኛውም ፣ ሰው ፣ እንደሚያደርገው ፣ ያለ ፣ ተራ ፣ ጥንቃቄ ፣ ነው ። እንዲሁም ፣ በዚህ ፣ በእኹኑ ፣ ነገር ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በሚያ ፣ ሥራው ፣ ምክንያት ፣ በፓልስዋገኑ ፣ መኪና ፣ ለነበሩት ፣ ሰዎች ፣ በሚያ ፣ ሥራው ፣ ልዩ ፣ ጥንቃቄ ፣ ለማድረግ ፣ በሕግ ፣ ግዴታ ፣ የለበትም ። ስለዚህ ፣ በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ጥፋተኛ ፣ መኾን ፣ የሚገባው ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፯፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩) በተመለከተው ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ስለኾነ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ደንብ ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፭ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩) የተመለከተውን ፣ ወንጀል ፣ በመሥራት ፣ ብቻ ፣ ጥፋተኛ ፣ ነው ። በቅጣቱ ፣ በኩል ፣ ይህ ፣ የይግባኝ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ እንደተመለከተው ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ የሠራው ፣ የቸልተኝነት ፣ ወንጀል ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ የቸልተኝነት ፣ ወንጀል ፣ ስለኾነና ፣ ከባድ ፣ የሞት ፣ አደጋ ፣ ስላስከተለ ፣ በዚሁ ፣ በቍጥር ፣ ፭፻፳፭ ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፭) በተመለከተው ፣ በከፍተኛው ፣ ቅጣት ፣ መቀጣት ፣

ስለሚገባው ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ በቍጥር ፣ ፩፻፳፮ ፣ በንኡስ ፣ ቍ. (፩)በተመለከ
ተው ፣ መሠረት ፣ በሦስት ፣ ዓመት ፣ እስራት ፣ መቀጣት ፣ አለበት ። በጠቅላላው ፣ ከዚህ ፣
በላይ ፣ እንደተዘረዘረው ፣ ይግባኙን ፣ ተቀብለን ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ጥፋተኛ ፣ ኹኖ ፣ የተገ
ኘበትን ፣ ከባድ ፣ ቅጣት ፣ የሚወስነውን ፣ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፪) ወደ ፣ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩)
በመለወጥና ፣ የእስራቱን ፣ ቅጣት ፣ በንኡስ ፣ ቍጥር ፣ በተመለከተው ፣ መሠረት ፣ ከዐ
ምስት ፣ ዓመት ፣ እስራት ፣ ወደ ፣ ሦስት ፣ ዓመት ፣ እስራት ፣ በመለወጥ ፣ ከፍተኛው ፣
ፍርድ ፣ ቤት ፣ የፈረደውን ፣ ፍርድ ፣ አሻሽለን ፣ ፈርደናል ።

ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ፍርዱ ፣ መሻሻሉን ፣ እንዲያውቀው ፣ ይጣፍለት ። ይህ ፣
ፍርድ ፣ ዛሬ ፣ ግንቦት ፣ ፯ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፸፬ ፣ ዓ. ም. በጠቅላይ ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ፍርድ ፣
ቤት ፣ በግልጽ ፣ ችሎት ፣ ተሰጠ ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 1 A

MAKONNEN WOLDEYES v. THE PUBLIC PROSECUTOR

Criminal Appeal No. 335/54 E.C.

Penal law - - Negligent homicide - - "Special professional duty" construed - - Art. 526 P. C. Criminal Procedure - - Contents of Charge.

On appeal from a judgment of the High Court convicting appellant, a bus driver, for aggravated negligent homicide under Art. 526 (2) when he overtook another vehicle without proper visibility, causing a collision in which three persons in an oncoming automobile were killed.

Held: Conviction and sentence revised, since no aggravation was charged or proved.

1. It is negligent conduct to overtake another vehicle without proper visibility.

2. A person has a "professional duty to safeguard life" under Art. 526 (2) P.C. when his job requires special care to safeguard persons whose physical integrity is temporarily under his care; doctors, nurses, pilots of airplanes, and drivers of public vehicles are examples of persons with such a professional duty.

3. A professional owes a "special" duty within the meaning of Art. 526 (2) P.C. only to those for whom he is responsible; the "special" duty owed by a driver of a public vehicle thus extends only to the passengers in the vehicle.

4. A charge under Art. 526 (2) P.C. that does not specify that the defendant is being charged with aggravation is defective.

Guenbot 6, 1952 E.C. (May 13, 1960 G.C.); Justices: Afenegus Taddessa Mengesha, Dr. W. Buhagiar, Ato Taddesse Tekle Giorgis: — The appellant was charged before the High Court with the offence of homicide by negligence, punishable under Article 526 of the Penal Code; he was found guilty, convicted and sentenced to the maximum period of imprisonment of five years under the second paragraph of Article 526, under which the offence of homicide by negligence is aggravated where the homicide is caused by a person who has a special professional duty to safeguard life. This is an appeal from the judgment of the High Court.

The grounds of appeal are (a) that there was no sufficient evidence on which the High Court could convict, (b) that the High Court was wrong in law in convicting the appellant under paragraph (2) of Article 526 when the charge referred only to Article 526, and (c) that the second paragraph of Article 526 is not applicable to the appellant (a driver of a bus) but is applicable only to doctors, nurses, etc. who carry out their duties in a negligent way.

The facts as found by the High Court are as follow: the appellant is a bus driver by profession; on Nehasse 11, 1953 E.C., the appellant was driving Bus No. AA 6135 and at the 126th km. on the road from Alaba Kulite to Addis Ababa; at about 15 minutes after midday, he came into collision with a car Volkswagen No. 9956 coming from the opposite direction; and as a result of this collision, the three passengers in the Volkswagen were killed. There were no fatal accidents amongst the passengers in the bus driven

by the appellant. The appellant was driving his bus behind another motor-vehicle, which was some distance in front and which was causing lots of dust rendering visibility very poor. The appellant was trying to overtake the other motor-vehicle, and in doing so, went partly on the wrong side of the road; at this time the Volkswagen, which was on the proper side of the road, collided with the bus driven by the appellant. The allegation of the prosecution is that the appellant was negligent in trying to overtake the other motor-vehicle when the visibility was poor as a result of the dust, and that the cause of death of the three passengers in the Volkswagen is due directly to the appellant's negligence.

In the opinion of this Court, there was sufficient and clear evidence on which the High Court could come to the conclusion it did. There is no contradiction amongst the witnesses, as the appellant submitted. There can be no question that it is very negligent for a driver to try to overtake another car when he has not a proper look-out of on coming traffic due to the dust. The High Court was, therefore, right in finding that the appellant was negligent.

The appellant submitted that the High Court was wrong in convicting the appellant under the provisions of the second paragraph of Article 526 when the charge referred generally to Article 526. It is essential in criminal cases that the accused should know what charge he is asked to meet; in the present case the charge does not allege that the appellant was, at the time of the offence, acting in a special professional capacity. The first and second paragraphs of Article 526 deal with the same offence, that is, homicide by negligence, but the second paragraph contains an aggravating element which subjects the offender to a higher punishment. The accused should know whether the prosecution is charging him with the aggravation and when the prosecution intends to do so, mention thereof should be made in the charge. In this respect, the charge is defective, but for reasons that will be given later, the defective charge has not in the present case led to a miscarriage of justice.

The appellant submitted as another ground of appeal that the second paragraph of Article 526 applies to doctors and nurses who carry out their duties in a negligent manner and does not apply to the appellant, the driver of a bus. The second paragraph of Article 526 provides for a higher punishment where the negligent homicide has been caused by a person who has a special professional duty to safeguard life. On reading this paragraph, the persons who first come to one's mind as having a special professional duty to safeguard life are doctors and nurses; but the said paragraph does not limit the responsibility to doctors and nurses; the word "professional" is used in the wide sense and applies to persons whose job requires special care to safeguard the life of persons whose physical integrity is temporarily under their care. The word "professional" applies to persons like the pilots of an airplane, bus drivers, and drivers of other public vehicles.

The duty of such persons is not, however, towards any person in the world; the duty of such professional persons is specially towards those persons for whom they are responsible, such as passengers in an airplane or passengers in a bus; such professional persons do not owe a special duty towards pedestrians; the duty to pedestrians or other persons not in the public vehicle is a general duty, not a special duty. Thus in the present case the appellant owed a special professional duty to the passengers in his bus, but owed only a general duty towards others outside the bus, such as the persons in the Volkswagen. For these reasons the appellant should have been found guilty of an offence under Article 526 (1) of the Penal Code, and he is hereby convicted under that provision. As to sentence, this Court considers that this is a very serious offence with serious consequences and the maximum punishment under the first paragraph of Article 526 should be inflicted and the appellant is sentenced to simple imprisonment for three years. In this sense, the appeal is allowed, and the judgment of the High Court is varied accordingly.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አሥመራ ፡ ችሎት ።

ኡኒቨርሳል ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኢጀንስ ፡ ትሬዲንግ ፡ ኩባንያ ፡ ሊሚትድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ተክሌ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቅጥር ፡ ፯/፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

ከዉል ፡ ውጭ ፡ የሚደርስ ፡ ጎላፊነት—ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ—ለተጐዳ ፡ ሰው ፡ በቀጥታ ፡ የተፈጠረ ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ—የንግድ ፡ ሕግ ፡ አናቅጽ ፣ ፭፻፹፭ ፡ ፭፻፹፮ ፡ እና ፡ ፭፻፹፰ ።

ያልተገባ ፡ ብልጽግና ፡

ውክለ—የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፪፺ሕ፭፻፳፩ ።

ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ከሳሽ ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ተከሳሹ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ በሌለበት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለከሳሽ ፡ በመፍረዱ ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ።

ውሳኔ ፤- የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ተገለበጠ ።

፩ ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፭ ፡ የሚሰው ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በቀጥታ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ ክሶ ፡ ካሳ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ እይደለም ። ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ከኢንሹራንሱ ፡ በቀጥታ ፡ ካሳ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባውን ፡ ሰው ፡ ከሶ ፡ በሱ ፡ ጥፋት ፡ ጉዳቱን ፡ ያደረሰበት ፡ መኾኑን ፡ በፍርድ ፡ ካረጋገጠ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ጥፋቱን ፡ አምኖ ፡ የጉዳቱን ፡ ካሳ ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ለመክፈል ፡ የተስማማና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውም ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ በንጉሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከሱን ፡ የተክላከለ ፡ ወይም ፡ ስምምነቱን ፡ የተቀበለ ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ ነው ።

፪ ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፯ ፡ (፪) የሚለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በክሱ ፡ ተጠሪ ፡ ኹኖ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ በመከላከል ፡ ለመከራከር ፡ በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ሊዋዋል ፡ መቻሉን ፡ ነው ። ይህም ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ መብት ፡ የሚጠብቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ወገን ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባውን ፡ (ተቀባይን) ፀልፎ ፡ (ዘሎ) በቀጥታ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ ለመክሰስ ፡ ይችላል ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ።

፫ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፪፺ሕ፭፻፳፩ ፡ ለተጐዳ ፡ ሰው ፡ ለጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የሰጠን ፡ በቀጥታ ፡ በመክሰስ ፡ ካሳ ፡ እንዲጠይቅ ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ። ምክንያቱም ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከገባው ፡ ጋራ ፡ ያልተከፈለ ፡ የጋራ ፡ ጎላፊነት ፡ ስለሌለው ፡ ነው ።

፬ ፤ ምንም ፡ ጉዳቱን ፡ ያደረሰው ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ እንዲከፍል ፡ ግድረግ ፡ የግይቻል ፡ ቢኾንና ፡ ይህም ፡ ሰው ፡ ለተጐዳው ፡ ሰው ፡ ካሳ ፡ እንዲከፈል ፡ ምንም ፡ ወይነት ፡ ስምምነት ፡ ያላደረገ ፡ ቢኾን ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ከኢንሹራንሱ ፡ ሰጪ ፡ ያልተገባ ፡ ብልጽግና ፡ ካሳ ፡ ሊጠይቅ ፡ እይችልም ። የዚህ ፡ ወይነቱ ፡ ያልተገባ ፡ ብልጽግና ፡ ካሳ ፡ ክስ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ አድራሹን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሶ ፡ መብቱን ፡ ላያረጋግጥ ፡ በቀጥታ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንዲክስ ፡ ከተራ ቀደለትማ ፡ በኢንሹራንስ ፡ ሰጪውና ፡ በጉዳት ፡ አድራሺው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ማሳጣት ፡ ይኾናል ።

ግንቦት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹፮ ፡ ዓ ፡ ም ። ዳኞች ፤- አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ ዐወቀ ፡ ዶክተር ፡ ጋየታኖ ፡ ላቲለ ፡ ዶክተር ፡ ጃንካርሎ ፡ ፖሌራ ። ለይግባኝ ፡ መነሻ ፡ የኾነው ፡

ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፤- ሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ ኪፐር ፡ እንደ ፡ ኤውሮጳ ፡ አቈጣጠር ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ . ም ፡ ከምሽቱ ፡ ኹለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲኾን ፡ በራስ ፡ ዳምጠው ፡ ጕዳና ፡ የሰዴው ፡ ቍጥር ፡ 62309 ፖሮን ፡ መኪና ፡ እየነዳ ፡ ሲሼድ ፡ መልስ ፡ ሰጭውን ፡ እስክን ፡ ቢስኪሌቱ ፡ ገጭቶት ፡ በቀኝ ፡ እግሩና ፡ እጁ ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ ስላደረሰበት ፡ በሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ስለቀረበበት ፡ በቃ ኘው ፡ ስተሸን ፡ በሰል ፡ መጥሪያ ፡ ቢላክለት ፡ ወደ ፡ አሜሪካን ፡ አገር ፡ መኼዱ ፡ ስለ ታወቀ ፤ ክሱ ፡ ተሻሽሎ ፡ ከሪቻርድ ፡ ጋራ ፡ ስለአደጋ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ያደረገውን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ (የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ) ተከሳሽ ፡ በማድረግ ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ መጥ ሪያ ፡ ደርሶት ፡ ስላልቀረበ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፷፯/፷፪ ፡ በሌለበት ፡ ለመልስ ፡ ሰጪው ፡ የጕዳት ፡ ካሳ ፡ የኢት. ብር ፡ 1620 እንዲከፍል ፡ ስለፈ ረደበት ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ያቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ምክንያት ፡ ባጭሩ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤-

፩ ፤ በመልስ ፡ ሰጪውና ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መካከል ፡ የሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ ስለሌለ ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ስላደረሰው ፡ አደጋ ፡ በጎላፊ ነት ፡ ሊጠየቅ ፡ አይገባውም ፤

፪ ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ስለ ፡ ኪፐር ፡ ሪቻርድ ፡ እንዲከራከርለት ፡ ወይም ፡ ደግሞ፡ እንዲሞግትለት ፡ የሚል ፡ አንዳች ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ አል ሰጠውም ፤

፫ ፤ ከቃኘው ፡ ስተሺን ፡ ለመልስ ፡ ሰጪው ፡ ጠበቃ ፡ በተጻፈለት ፡ ደብዳቤ ፡ ሚስተር ፡ ኪፐር ፡ ሪቻርድ ፡ ባደረሰው ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እንዲከራከርለት ፡ ይገባዋል ፡ ቢልም ፡ በመልስ ፡ ሰጪው ፡ በቀጥታ፡ አደጋ ፡ ያደረሰውን ፡ ሚስተር ፡ ሪቻርድን ፡ ክሶ ፡ ሳያስፈርድ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ እንዲከራከር ፡ የሚያስገድደው ፡ ሕግ ፡ የ ለም ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አስፈላጊ ፡ ኹኖ ፡ ያገኘው ፡ እንደኾነ ፡ በደንበ ኛው ፡ ስም ፡ ኹኖ ፡ ከመልስ ፡ ሰጪው ፡ ጋራ ፡ ይከራከር ፡ እንጂ ፡ በቀ ጥታ ፡ መከሰስ ፡ እንደሌለበት ፡ ራሱ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ያስረዳል ። ይህም ፡ የሚያስረዳው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያን ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ የተሰጠ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ለጠቀሳቸው ፡ የን ግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፮፻፹፭ ፡ ፭፻፹፮ ፡ እና ፡ ፭፻፹፰ ፡ በይግባኝ ፡ ባ ዩና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ለገባው ፡ በሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ መካከል ፡ ስለ ሚመለከተው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚያመለክቱ ፡ እንጂ ፡ መልስ ፡ ሰ ጪው ፡ ከይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ለመጠየቅ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ አያመለክቱም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፺ሕ፭፻፷፭ ፡ መ ልስ ፡ ሰጪው ፡ ቢጠቅስም ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚኾነው ፡ በ ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጪው ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ግንኙነት ፡ ሲኖር ፡ መኾኑን ፡ አላስረዱም ።

በበኩሉ ፡ የመልስ ፡ ሰጪው ፡ ጠበቃ ፡ ያቀረበው ፡ መከላከያ ፡ በዐጭሩ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤-

፩ ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፹፭ ፡ መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ የጥቅሙ ፡ ጠባቂ ፡ ምግዚት ፡ እንደመኾኑ ፡ መጠን ፡ ጕዳት ፡ የ ደረሰበት ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ በሕግ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡

ክስ ፣ ሲያቀርብ ፣ ጉዳት ፣ የደረሰበት ፣ ወገን ፣ ይግባኝ ፣ ባዩን ፣ ለመክሰስ ፣ ይችላል ። ኢንሹራንስ ፣ ገቢው ፣ በሚያደርሰው ፣ ጉዳት ፣ የኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በጎላፊነት ፣ ተጠያቂ ፣ እንደሚኾን ፣ በማንም ፣ ዘንድ ፣ የታወቀ ፣ ነው ፤

፪ ፤ ኢንሹራንስ ፣ ገቢው ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ ወደ ፣ አገራቸው ፣ ስለኼዱ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በእሳቸው ፣ እግር ፣ ተተክቶ ፣ ለቀረበባቸው ፣ ክስ ፣ መልስ ፣ መስጠት ፣ እንደሚገባቸው ፣ ግልጽ ፣ ነው ፤

፫ ፤ በንግድ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፮፻፹፩ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ኢንሹራንስ ፣ አድራጊው ፣ ላደረሰው ፣ ጉዳት ፣ ካሳ ፣ ከመክፈል ፣ ነጻ ፣ የሚኾነው ፣ ተጐጂው ፣ ካሳውን ፣ በስምምነት ፣ ወይም ፣ በፍርድ ፣ እንዲከፍለው ፣ ያልጠየቀ ፣ እንደኾነ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ካሳውን ፣ በስምምነት ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ እንዲከፍለው ፣ በደብዳቤ ፣ ጠይቆት ፣ ስለአልከፈለው ፣ ክስ ፣ አቅርቧል ፤ ይኸውም ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ በቍጥር ፣ ፮፻፹፮ ፣ የተደገፈ ፣ ነው ፤

፬ ፤ መልስ ፣ ሰጪው ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ ያቀረበው ፣ ክስ ፣ ሕጋዊ ፣ ለመኾኑ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቍጥር ፣ ፪፻ሕ፭፻፷፭ ፣ ንኡስ ፣ ቍ ፣ (፩) ፣ (፪) ፣ (፫) የተደገፈ ፣ ነው ፤ ይህም ፣ ቍጥር ፣ ማንም ፣ ሰው ፣ በተንኰልና ፣ በዘዴ ፣ የማይገባውን ፣ ብልጽግና ፣ ከማግኘት ፣ እንዲታገድ ፣ የተደነገገ ፣ ነው ።

በግራ ፣ ቀኙ ፣ በኩል ፣ የቀረበውን ፣ ክርክር ፣ ከመመርመራችን ፣ በፊት ፣ ለቀረበው ፣ ይግባኝ ፣ ሊወሰን ፣ የሚገባው ፣ ጭብጥ ፣ ምን ፣ እንደኾነ ፣ መረዳት ፣ ያስፈልጋል ። ዋናው ፣ ጥያቄ ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ በመልስ ፣ ሰጪው ፣ ቢስከሌትና ፣ በእካሉ ፣ ላይ ፣ ስላደረሰበት ፣ ጉዳት ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ የኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ ሰጪውን ፣ በቀጥታ ፣ ለመክሰስ ፣ የሚችል ፣ መኾን ፣ አለመኾኑን ፣ መወሰን ፣ ነው ።

በይግባኝ ፣ ባዩና ፣ በሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ መካከል ፣ ስለአደጋ ፣ ዋስትና ፣ የኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ የተደረገ ፣ ለመኾኑ ፣ በኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ በኩል ፣ አልተካደም ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ በኢንሹራንስ ፣ ውሉ ፣ መሠረት ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ የመክሰስ ፣ መብት ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ በማስተላለፍ ፣ የወከለው ፣ ለመኾኑ ፣ የቀረበ ፣ ማስረጃ ፣ የለም ።

ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተገለጹትን ፣ ፍሬ ፣ ነገሮች ፣ ካረጋገጥን ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ ስለኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ በመልስ ፣ ሰጪው ፣ የተጠቀሱትን ፣ ቍ ፣ ፮፻፹፭ ፣ ፮፻፹፮ ፣ ፮፻፹፯ ፣ እንመርምር ።

ቍጥር ፣ ፮፻፹፭ ፣ የኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ ጎላፊነት ፣ ሲናገር ፣ "ጉዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ ላይ ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ ወይም ፣ በስምምነት ፣ ጥያቄ ፣ ካላደረገ ፣ በቀር ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በዐላፊነት ፣ አይጠየቅም ፣" በማለት ፣ ይደነግጋል ። ይህም ፣ የሚያስረዳን ፣ እነዚህ ፣ ኹለት ፣ ሕጋዊ ፣ ኹነታዎች ፣ ካልተፈጸሙ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በዐላፊነት ፣ አይጠየቅም ፣ ማለትን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ጉዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ በቀጥታ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ ከሶ ፣ የጉዳቱን ፣ ካሳ ፣ ለመጠየቅ ፣ ይችላል ፣ ማለቱን ፣ አይደለም ። ጉዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ለጉዳቱ ፣ ካሳ ፣ የሚያገኘው ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባውን ፣ ሰው ፣ ከሶ ፣ በሱ ፣ ጥፋት ፣ ጉዳቱን ፣ ያደረሰበት ፣ መኾኑን ፣ በፍርድ ፣ ካረጋገጠ ፣ ወይም ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ ጥፋቱን ፣ አምኖ ፣ የጉዳቱን ፣ ካሳ ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ ለመክፈል ፣ ሲስማማና ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውም ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ መብት ፣ ተተክቶ ፣

በነገሩ ፣ ውስጥ ፣ ነብቶ ፣ ክሱን ፣ የተከላከለ ፣ ሲኾን ፣ ወይም ፣ ስምምነቱን ፣ ሲቀበል ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በዐላፊነት ፣ ሊጠየቅ ፣ ይችላል ። ነገር ፣ ግን ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባውን ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድን ፣ ከሶ ፣ ላደረሰው ፣ ጕዳት ፣ እዋፊ ፣ መኾኑን ፣ አላስረዳም ። እንዲያውም ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ የመከላከሉን ፣ መብት ፣ ለኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በማስተላለፍ ፣ አልዳረገውም ። እነዚህ ፣ ሕጋዊ ፣ ዅነታዎች ፣ ሳይፈጸሙ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በቀጥታ ፣ ጕዳት ፣ ለደረሰበት ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ የጉዳት ፣ ካሳ ፣ ለመክፈል ፣ ዐላፊ ፣ ሊኾን ፣ አይችልም ። መልስ ፣ ሰጪው ፣ ለኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ለጕዳቱ ፣ ካሳ ፣ ጥያቄ ፣ በማቅረብ ፣ ብቻ ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ዐላፊ ፣ መኾን ፣ አለበት ፣ በማለት ፣ ያቀረበው ፣ ክርክር ፣ በሕጉ ፣ መሠረት ፣ ያለው ፣ ዅኖ ፣ አላገኘነውም።

ቍጥር ፣ ፮፻፹፮ ፣ ንኡስ ፣ ቍ ፡ (፪) ስለ ፣ ወንጀል ፣ ነገር ፣ ስለሚናገር ፣ በዚህ ፣ ጕዳይ ፣ ተፈጻሚ ፣ ስላልኾነ ፣ ንኡስ ፣ ቍ ፡ (፩)ን ፣ ብቻ ፣ እንመረምራለን ፤ ስለክስ ፣ አመራር ፣ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩) ሲናገር ፣ ‘‘ጕዳት ፣ የደረሰበት ፣ ወገን ፣ በዐላፊነት ፣ የሚያቀርበውን ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ መሪ ፣ ለመኾን ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ የተዋዋለው ፣ ቃል ፣ ይጸናል ፣’’ በማለት ፣ ይደነግጋል ። ይህም ፣ ማለት ፣ ጕዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ለሚያቀርበው ፣ ክስ ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ ስም ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በክሱ ፣ ተጠሪ ፣ ዅኖ ፣ ለመከራከር ፣ የሚችል ፣ መኾኑን ፣ በኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ ውስጥ ፣ ለመዋዋል ፣ ይችላል ፣ ማለት ፣ ነው ። ይህም ፣ አነጋገር ፣ ቢኾን ፣ የኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ የመከላከል ፣ መብት ፣ የሚጠበቅ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ጕዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ለደረሰበት ፣ ጕዳት ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባውን ፣ ሰው ፣ ዐልፎ ፣ (ዘሎ) በቀጥታ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ ለመክሰስ ፣ ይችላል ፣ ማለቱ ፣ አይደለም ። የዚህ ፣ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ መንፈስ ፣ በተጨማሪ ፣ የሚያስረዳን ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ሰው ፣ሰም ፣ ካልኾነ ፣ በቀር ፣ ለምሳሌ ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ ላይ ፣ ጕዳት ፣ ያደረሰውን ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ በቀጥታ ፣ ለመክሰስ ፣ የማይችል ፣ መኾኑን ፣ ነው ። የኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ ውጤት ፣ ያለው ፣ በቀጥታ ፣ በኢንሹራንስ ፣ ሰጪውና ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ መካከል ፣ ነው ።

ቍጥር ፣ ፮፻፹፮ ፣ ንኡስ ፣ ቍ ፡ (፩) ጕዳት ፣ ለደረሰበት ፣ ሰው ፣ በቀደምትነት ፣ ስለመክፈል ፣ ሲደነግግ ፣ ‘‘ጕዳት ፣ ለደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ በሚከፍለው ፣ ኪሣራ ፣ ሒሳብ ፣ ልክ ፣ ካሳውን ፣ እስኪከፍለው ፣ ድረስ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ኢንሹራንስ ፣ ለገባው ፣ ሰው ፣ ካሳ ፣ አይከፍለውም ፡’’ በማለት ፣ ይገልጻል ። ይህም ፣ ማለት ፣ ጕዳት ፣ ለደረሰበት ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ ወይም ፣ በስምምነት ፣ ኢንሹራንስ ፣ ለገባው ፣ ሰው ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ የሚከፍል ፣ ከኾነ ፣ አስቀድሞ ፣ ለሦስተኛው ፣ ወገን ፣ የጕዳቱን ፣ ካሳ ፣ ሒሳብ ፣ መክፈል ፣ ያለበት ፣ ለመኾኑ ፣ ነው ። የዚሁም ፣ ድንጋጌ ፣ ሕጋዊ ፣ ዐሳብ ፣ እላይ ፣ ስለ ፣ ቍጥር ፣ ፮፻፹፮ ፣ በታተተው ፣ ዐሳብ ፣ መሠረት ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ የጕዳቱን ፣ ካሳ ፣ የሚከፍል ፣ ሲኾን ፣ ሦስተኛው ፣ ወገን ፣ ማግኘት ፣ የሚገባውን ፣ የጕዳት ፣ ካሳ ፣ የቀደምትነት ፣ መብት ፣ ለመጠበቅ ፣ የተደነገገ ፣ ነው ።

በተጨማሪም ፣ የመልስ ፣ ሰጪው ፣ ጠበቃ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርን ፣ ሕግ ፣ ቍ ፡ ፱፻፯ ፩፻፷፩ ፣ ጠቅሷል ። ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፩) በዐግርኛው ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ የተሠረዘና ፣ እርግቱም ፣ በእንግሊዝኛ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በርግት ፣ ክፍል ፣ የተሠረዘ ፣ መኾኑን ፣ መገንዘብ ፣ ይገባ ፣ ነበር ።

ይህ ፣ ቍጥር ፣ ስለመዳረግ ፣ በንኡስ ፣ ቍ ፡ (፩) ሲደነግግ ፣ ‘‘እንድ ፣ ሰው ፣ ከሚወሰነው ፣ ዕዳ ፣ የክፍያውን ፣ ድርሻን ፣ መክፈል ፣ የሚገባው ፣ ሲኾን ፣ ዕዳውን ፣ በውሉ ፣ የከፈለ ፣ እንደኾነ ፣ ከርሱ ፣ ጋራ ፣ ዕዳውን ፣ እንዲከፍሉ ፣ ግዴታ ፣ ባለባቸው ፣ ሰዎች ፣

ላይ ፣ የመጠየቅ ፣ መብት ፣ አለው ፣'' በማለት ፣ ያስረዳል ፤ ንኡስ ፣ ቍጥር ፣ (፪) ደግሞ ፣ ጥያቄውን ፣ ለማቅረብ ፣ በተበደለው ፣ ሰው ፣ መብቶች ፣ እንደገባ ፣ ይቈጠራል ፣ በማለት ፣ ይገልጣል ። ይህም ፣ የሚያስረዳን ፣ ለምሳሌ ፣ ከብዙ ፣ በጥቂቱ ፣ መኪና ፣ ነጂው ፣ ባደረ ሰው ፣ ጉዳት ፣ ከመኪናው ፣ ባለቤትና ፣ ከመኪናው ፣ ነጂ ፣ ለሚጠየቀው ፣ የጉዳት ፣ ካሳ ፣ ወይም ፣ ብዙ ፣ ባለዕዳዎች ፣ በአንድነት ፣ ለዕዳው ፣ ተጠያቂዎች ፣ ሲኾኑ ፣ በገቡበት ፣ ግዴታ ፣ ከነሱ ፣ ውስጥ ፣ እንደኛው ፣ ብቻውን ፣ ዕዳውን ፣ በምሉ ፣ የከፈለ ፣ እንደኾነ ፣ ከርሱ ፣ ጋራ ፣ ዕዳውን ፣ እንዲከፍሉ ፣ ግዴታ ፣ ባለባቸው ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ ለመጠየቅ ፣ መብት ፣ የሚሰጥ ፣ ድንጋጌ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ጉዳት ፣ የደረሰበት ፣ ሥስተኛ ፣ ወገን ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ በቀጥታ ፣ ከሶ ፣ የጉዳት ፣ ካሳውን ፣ ለመቀበል ፣ መብት ፣ አይሰጠውም ። ምክንያቱም ፣ የኢንሹራንሱ ፣ ግዴታ ፣ በኢንሹራንስ ፣ ሰጪውና ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ መካከል ፣ ባለው ፣ ሕጋዊ ፣ ግንኙነት ፣ ብቻ ፣ የተመሠረተ ፣ በመኾኑ ፣ ነው ። ኢን ሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ ከውል ፣ ውጭ ፣ በኾነ ፣ ጎላፊነት ፣ ባደረሰው ፣ ጉዳት ፣ በቀ ጥታ ፣ ተጠያቂ ፣ የሚኾነው ፣ እሱ ፣ ነው ። ግን ፣ ለሚያደርሰው ፣ ጉዳት ፣ የኢንሹራንስ ፣ ዋስትና ፣ ስላለው ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ኹኑታውን ፣ በመመልከት ፣ ቢፈቅድ ፣ ኢንሹ ራንስ ፣ ስለገባው ፣ ሰው ፣ ዅኖ ፣ የጉዳቱን ፣ ካሳ ፣ ጉዳት ፣ ለደረሰበት ፣ ሥስተኛ ፣ ወገን ፣ ይከፍላል ። ለመክፈል ፣ ፈቃደኛ ፣ ካልኾነም ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ በሕግ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ ከሶ ፣ እንዲከፈለው ፣ ያደርጋል ፣ እንጂ ፣ በቀጥታ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ ኢንሹራንስ ፣ ከገባው ፣ ሰው ፣ ጋራ ፣ ያልተከፈለ ፣ የጋራ ፣ ጎላፊነት ፣ እንዳለባቸው ፣ ቈጥሮ ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ (ሥስተኛ ፣ ወገን) ፣ በቀጥታ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪውን ፣ የመክ ሰስ ፣ መብት ፣ የለውም ። እንዲያውም ፣ ለምሳሌ ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ ከኢንሹ ራንስ ፣ ውል ፣ ዅነታ ፣ ውጭ ፣ ላደረሰው ፣ ጉዳት ፣ ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ዐላፊ ፣ የማይ ኾንበት ፣ ዅነታ ፣ ሊኖር ፣ ይችላል ። ስለዚህ ፣ በኢንሹራንስ ፣ ሰጪውና ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ መካከል ፣ እንዲሁም ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰውና ፣ ጉዳት ፣ በደረሰ በት ፣ በ'መልስ ፣ ሰጪው ፣ መካከል ፣ ያለው ፣ ግዴታ ፣ በየደረጃው ፣ በሚረጋገጥ ፣ መብት ፣ የተያያዘ ፣ እንጂ ፣ በኢንሹራንስ ፣ ሰጪውና ፣ ጉዳት ፣ በደረሰበት ፣ በመልስ ፣ ሰጪው ፣ መካከል ፣ በቀጥታ ፣ የተፈጠረ ፣ ሕጋዊ ፣ ግዴታ ፣ የለም ። ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ከመ ልስ ፣ ሰጪው ፣ ጋራ ፣ ስላለው ፣ የመብት ፣ ወይም ፣ የመከላከል ፣ ዋያቄ ፣ ኢንሹራንስ ፣ በገባው ፣ ሰው ፣ መብትን ፣ በመዳረግ ፣ ወይም ፣ በማስተላለፍ ፣ ግዴታ ፣ የተመሠረተ ፣ ነው ። እንዲሁም ፣ ኢንሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ በመልስ ፣ ሰጪው ፣ ላይ ፣ ስላደረሰበት ፣ የጉዳት ፣ ካሳ ፣ የመልስ ፣ ሰጪው ፣ የመጠየቅ ፣ ወይም ፣ የመከላከል ፣ መብት ፣ ኢንሹራ ንስ ፣ ባደረገው ፣ ሰውና ፣ በመልስ ፣ ሰጪው ፣ መካከል ፣ ባለው ፣ ሕጋዊ ፣ ግንኙነት ፣ የተ መሠረተ ፣ መኾኑን ፣ ማወቅ ፣ ያስፈልጋል ። ኢንሹራንስ ፣ የገባው ፣ ሰው ፣ ላደረሰው ፣ ጉዳት ፣ ለሚከፍለው ፣ ካሳ ፣ የኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ የመክፈል ፣ ወይም ፣ ያለመክፈል ፣ ግዴታ ፣ የተመሠረተው ፣ በኹለቱ ፣ መካከል ፣ ባለው ፣ ሕጋዊ ፣ ግንኙነት ፣ መኹኑ ፣ ግልጥ ፣ ነው ።

ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ ስላደረሰው ፣ ጉዳት ፣ የቃኘው ፣ ስተሽን ፣ የሕግ ፣ ክፍል ፣ ለይግ ባኝ ፣ ባዩ ፣ ለኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ የጣፈውንና ፣ ይግባኝ ፣ ባዩም ፣ የመለሳቸው ፣ ደብዳቤ ዎች ፣ በማስረጃነት ፣ ቀርቦልን ፣ ተመልክተናል ። በዚህም ፣ ማስረጃ ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ መልስ ፣ ሰጪውን ፣ የወከለበት ፣ ወይም ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በመልስ ፣ ሰሞው ፣ ላይ ፣ ለደረሰ በት ፣ ጉዳት ፣ ካሳ ፣ ለመክፈል ፣ የተስማማበት ፣ ለመኾኑ ፣ ስለማይገልጽ ፤ እንዲያው ፣ የቃኘው ፣ ስተሽን ፣ የሕግ ፣ ክፍል ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ ከይግባኝ ፣ ባይ ፣ ጋራ ፣ የኢንሹ ራንስ ፣ ውል ፣ ስላለው ፣ መክፈል ፣ እለበት ፣ ብሎ ፣ በመጣፍ ፣ ብቻ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በጎላ ፊነት ፣ የሚጠይቅበት ፣ ምክንያት ፣ ስለሌለ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩና ፣ የቃኘው ፣ ስተሽን ፣ የሕግ ፣

ክፍል ፣ የተጻጸፉት ፣ ደብዳቤ ፣ ለነገሩ ፣ ማስረጃነት ፣ ዋጋ ፣ የሌለው ፣ መኾኑን ፣ ተረድ ተናል ።

ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ ከይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ጋራ ፣ የኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ ቢኖረውም ፣ በመ ልስ ፣ ሰጪው ፣ ላይ ፣ ለደረሰው ፣ ጉዳት ፣ በቀጥታ ፣ ተጠያቂ ፣ የሚኾነው፣ እሱ ፣ ራሱ ፣ ነበር ። ግን ፣ ክስ ፣ ሳይቀርብበት ፣ ወይም ፣ ከይግባኝ፣ ባዩ ፣ ከኢንሹራንስ ፣ ሰጪው ፣ ጋራ ፣ ተስማምቶ ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ የጉዳት ፣ ካሳ፣ እንዲከፍል፣ ሳያደርግ፣ ዝም ፣ ብሎ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ ኼዷል ። ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ዐሳፊነት ፣ የሚጠየቅ ፣ መኾኑን ፣ እያወቀ ፣ ነገሩን ፣ ሳያስወስን ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ ከአገር ፣ ወጥቶ ፣ እንዳይኼድ ፣ ሕጋዊ ፣ እርምጃ ፣ መውሰድ ፣ ሲገባው ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ዝም ፣ ብሎ፣ ሰውየው ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ ከኼደ ፣ በኋላ ፣ ክስ ፣ ቢያቀርብበትና ፣ ኋላም ፣ መጥሪያው ፣ ሊደርሰው ፣ የማይ ችል ፣ መኾኑን ፣ ሲያውቅ ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ በቀጥታ ፣ በይግባኝ፣ ባዩ ፣ ላይ፣ ክስ ፣ ሲያቀርብ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ከመልስ ፣ ሰጪው ፣ ጋራ ፣ ሕጋዊ ፣ ግንኙነት ፣ ወይም፣ ግዴታ ፣ ያለው ፣ መኾኑን ፣ አላስረዳም ። ሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ ስላደረሰው ፣ ጉዳት ፣ የኢንሹራንስ ፣ ዋስ ትና ፣ እያለው ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ ምንም ፣ ሳያደርግለት ፣ በመኼዱ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ (ኢንሹራንስ ፣ ሰጪው) ያልተገባ ፣ ብልጽግና ፣ የሚያገኝ ፣ ቢመስልም ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድን ፣ ከሶ ፣ በፍርድ ፣ መብቱን ፣ ሳያረጋግጥ ፣ በቀጥታ ፣ ይግ ባኝ ፣ ባዩን ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ እንዲከስ ፣ ከተፈቀደለት ፣ በይግባኝ ፣ ባዩና ፣ በሚስተር ፣ ሪቻ ርድ ፣ መካከል ፣ ያለውን ፣ የኢንሹራንስ ፣ ውል ፣ ዋጋ ፣ ማሳጣት ፣ ይኾናል ።

ስለዚህ ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ በቅጥር ፣ ፮፻፹፭ ፣ ፮፻፹፯ ፣ ፮፻፹፰ ፣ እና ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በቅጥር ፣ ፪፺ሺሕ፭፻፷፭ ፣ የተደነገገውና ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተገለጠው ፣ ትችት ፣ መሠረት ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ በቀጥታ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩን ፣ የመክሰስ ፣ መብት ፣ የሌለው ፣ መኾኑን ፣ በመረዳት ፣ የኢንሹራንሱ ፣ ውል ፣ በይግባኝ ፣ ባዩና ፣ በሚስተር ፣ ሪቻርድ ፣ መካከል ፣ ያለውን ፣ ሕጋዊ ፣ ግንኙነት ፣ ብቻ ፣ የሚመለከት ፣ ስለኾነ ፣ ሚስ ተር ፣ ሪቻርድ ፣ በኢንሹራንሱ ፣ ውል ፣ መሠረት ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ የመ ጠየቅ ፣ መብት ፣ ለመልስ ፣ ሰጪው ፣ ያልዳረገው ፣ ወይም ፣ በማስተላለፍ ፣ የውክልና ፣ ሥልጣን ፣ ያልሰጠው ፣ መኾኑን ፣ በመገንዘብ ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ሚስተር ፣ ሪቻርድን ፣ ክሶ ፣ ስላደረሰው ፣ የጉዳት ፣ ካሳ ፣ በፍርድ ፣ ሳያረጋግጥ ፣ በቀጥታ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩን ፣ የመ ጠየቅ ፣ ሕጋዊ ፣ መብት ፣ የሌለው ፣ መኾኑን ፣ ስለተረዳን ፣ የከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በመዝገብ ፣ ቁ ፣ .... የሰጠውን ፣ ፍርድ ፣ ሽረናል ።

ኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ በዚህ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የደረሰባቸውን፣ ወጪ ፣ ይቻሉ፣ ብለናል።

የዚህ ፣ ፍርድ ፣ ግልባጭ ፣ ለፍርድ ፣ አስፈጻሚው ፣ ይተላለፍ ።

ይህ ፣ ፍርድ ፣ ዛሬ ፣ ግንቦት ፣ ፯ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፺፯ ፣ ዓ. ም. ኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ ባሉ በት ፣ ተሰጠ ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Asmara Div.

UNIVERSAL INSURANCE AGENTS TRADING CO. LTD. v. GHEBRE MESKEL TEKLE

Civil Appeal No. 90/56 E. C.

Extra-contractual liability - - Insurer - - Direct liability to injured person - - Arts. 685, 687, *and* 688 *Com. C.*

Unjust enrichment.
Contractual obligation -- Subrogation - - Art. 2161 *Civ. C.*

On appeal from a High Court judgment by default in favour of the plaintiff in a personal injury action brought directly against the insurer of the person who caused the injury.

Held: Judgment reversed.

1. Art. 685 Com. C. does not mean that an injured third party may claim compensation directly from the liability insurer of the person who caused the injury. In order to claim directly from the insurer, the injured third party must, first, establish by court proceedings or admission of the insured person that the injury resulted from the fault of the latter, and second, show that the liability insurer participated in the proceedings on behalf of the insured or has accepted an amicable settlement of the case.

2. Art. 687 (2) Com. C. safeguards the interests of the liability insurer by enabling him to represent the insured and raise defences. This does not entitle the injured third party to by-pass the insured and sue the liability insurer directly.

3. Art. 2161 Civ. C. does not entitle an injured third party to claim compensation directly from the liability insurer, since the latter is not jointly liable with the insured person who caused the injury.

4. Even though the insured person who caused an injury is not subject to service of process by local courts and has done nothing to compensate the victim, the latter has no "unjust enrichment" claim against the liability insurer; to allow such a claim without having judicially established the victim's right against the person who caused the injury would annul the insurance contract between the latter and the liability insurer.

Guenbot 7, 1956 E.C. (May 14, 1964 G.C.); Justices: Ato Negussie Fitawake, Dr. Gayatano Lattila, Dr. Giancarlo Pollera: — The circumstances which gave rise to this appeal, briefly stated, are as follows:

At 8:30 p.m. on September 1, 1962, Mr. Richard Cooper was driving a car, Lic. No. 62309, on Ras Desta Damtew Street, when he collided with the respondent, who was riding a bicycle, thereby injuring him on the right leg and arm. An action was brought against Mr. Cooper, and a summons was issued and sent to the Kagnew Station for service on him; it was learned, however, that he had left for the U.S.A. The complaint was then amended to substitute as defendant the present appellant, an insurance company by which Mr. Cooper was insured against accidents. Summons was issued and served upon the company, the present appellant, but the appellant failed to appear. The High Court, therefore, gave judgment by default, ordering the appellant to pay $1620 compensation to the respondent.

The appeal was lodged against this judgment.

The grounds of appeal submitted by the appellant may be summarized as follows:

1. No legal relationship exists between the appellant and the respondent and, therefore, the appellant can have no responsibility for the accident that has occurred.

2. Appellant has no agreement or authorization to represent Richard Cooper in any litigation.

3. In spite of the advice of the letter from Kagnew Station to the advocate for the appellant that in an action arising from an accident the appellant must represent Richard Cooper, there is no law that requires the appellant to represent him in any litigation unless the respondent has first sued and obtained a judgment against Richard Cooper, the person who caused the injury.

The terms of the contract of insurance are clear that appellant has the right to direct the defence of the insured against the respondent, had it considered this necessary, but that it may not be sued directly. This shows that the provision is to safeguard the interests of the insurance company.

4. And lastly, respondent has referred to Articles 685, 687, and 688 of the Commercial Code. These provisions concern the rights and duties that exist between the appellant and the insured, Mr. Cooper; they do not entitle the respondent to sue the appellant directly. Respondent has also referred to Article 2161 of the Civil Code, but he failed to show the relationship that must exist between the appellant and the respondent before this Article could apply.

The reply submitted by the advocate for the respondent may be summarized as follows:

1. In accordance with Article 687 of the Commercial Code, the appellant is a guardian of the interests of Mr. Cooper, and, therefore, to claim compensation for injury done to him by an insured person, the respondent may sue the appellant; that the insurer is liable for compensation for an injury caused by the beneficiary is known by all.

2. Since Mr. Cooper has gone back to his country, appellant must reply to the complaint brought against it as a substitute for Mr. Cooper.

3. Appellant would be exempted from paying compensation in accordance with Article 685 of the Commercial Code for injury done by an insured person only if the injured person does not claim compensation, either amicably or judicially. Respondent asked appellant amicably to pay him the compensation, but because appellant would not pay, he has brought this action. This is in conformity with Article 688 of the Commercial Code.

ተከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፣ በክርክሩ ፡ ያለውን ፡ ቤት ፡ ከሳሹ ፡ (ቤቱን ፡) እንዲለቁ ፡ ያዘዝኩበት ፡ ምክንያት ፡ ቤቱ ፡ ለነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስለተሰጠ ፡ ነው ፣ ለዚሁም ፡ ይደግፈኛል ፣ ብሎ ፣ ያቀረበው ፡ እንደኛው ፣ ተከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቦ ፡ ስንመለከተው ፡ በዝርዝሩ ፡ ያለውን ፣ ቤት ፣ የያዘ ፡ ቦታ ፡ የተሰጠ ፡ መኾኑንና ፣ በሌላውም ፡ በኮል ፡ ለመዝገብ ፡ እያያዝ ፡ እንዲመች ፣ የቦታው ፡ ስፋት ፡ ተለክቶ ፡ ሜትር ፡ ካሬው ፡ ተገልጾ ፡ እንዲጸፍላቸው ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፣ ተከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዳመለከተው ፡ በአስቸኳይ ፡ ቦታውን ፡ ለነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ያልታዘዙ ፡ መኾና ቸውን ፡ ማዘዣው ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ።

እንዲሁም ፡ ተከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በወዲሱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭ሺሕ፪፻፷፭ ፡ የተጻፈውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የራሱ ፡ የኾነውን ፡ ቦታ ፡ ይቅርና ፡ ማናቸውንም ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ የኾነውን ፡ ቦታ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላልና ፡ አንቀጽ ፡ ይደግፈኛል ፡ ብሎ ፡ ስለአቀረበው ፡ ክርክር ፡ መንግሥት ፡ ለባለንብረቱ ፡ ወይም ፡ ለተከራዩ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ኪሣራውን ፡ ወይም ፡

ዋጋውን ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ለመውሰድ ፡ ምሉ ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ አይካድም ። ይኸ ውም ፡ አንቀጽ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ እና ፡ ፹፰ ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፱ ፡ እና ፡ ፺ ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ የሚደገፍ ፡ ነው ።

ይኹን ፡ እንጂ ፡ ተከሳሽ ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የጠቀሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ በክርክሩ ፡ ካለው ፡ ጉዳይ ፡ አንዳችም ፡ ተገቢነት ፡ የለውም ፤ ምክንያቱም ፡ አኹን ፡ በክርክሩ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ውሉን ፡ አስቀድሞ ፡ ለማፍረስ ፡ ሲኾን ፡ ተከሳሽ ፡ የጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ ስለሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚወስደው ፡ ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

የኾነ ፡ ኹኖ ፡ በከሳሽና ፡ በተከሳሽ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ በአንቀጽ ፡ ሦስት ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ስንመለከተው ፡ ከሳሽ ፡ ቤቱን ፡ ለመልቀቅ ፡ ሲፈልግ ፡ ከዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ለተከሳሽ ፡ ለማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ እንደገባና ፡ በበኩሉም ፡ ተከሳሽ ፡ ቤቱን ፡ እንዲለቅለት ፡ የፈለገ ፡ እንደኾነ ፡ ከኹለት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ለተከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ እንዳለበት ፡ ኹለቱ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በየበኩላቸው ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ግዴታ ፡ እንደገቡ ፡ ውሉ ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ።

ቀድሞውንም ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታውን ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበው ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሽ ፡ የኹለት ፡ ወር ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ ውሉን ፡ በመተላለፍ ፡ በእንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ቤቱን ፡ ለምን ፡ ልቀቅ ፡ አለኝ ፡ በማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በውሉ ፡ በሦስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ከተጻፈው ፡ ቃል ፡ ውል ፡ እንዲፈጸምለት ፡ እንዳልጠየቀ ፡ በጻፈው ፡ ማመልከቻ ፡ ታውቋል ።

ከሳሽ ፡ በአቤቱታው ፡ ለውርድበጅ ፡ ያኸል ፡ ቤቱ ፡ የተፈለገ ፡ ለመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሳይኾን ፡ ለንጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ዐጠር ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ሰንዝረዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሲባል ፡ ጠቅላላ ፡ ስም ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ ፡ ሲኾን ፤ መንግሥት ፡ ንግድ ፡ እንዲሰፋፋ ፡ አገር ፡ እንዲለማ ፡ ማናቸውም ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚመለከተው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በመንግሥት ፡ መሪነት ፡ የሚሠራ ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በተለይም ፡ በክርክሩ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ ለማከናወን ፡ ይመች ፡ ዘንድ ፡ ፕላኑ ፡ በመንግሥት ፡ የተመራ ፡ ለመኾኑ ፡ ለማንም ፡ ሥውር ፡ አይደለም ።

እኹን ፡ ከሳሽ ፡ በውሉ ፡ በሦስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ በተጻፈው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ መብቴ ፡ እንዲጠበቅልኝ ፡ በማለት ፡ ያቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ሕጋዊና ፡ የሚገባ ፡ ጥያቄ ፡ ኹኖ ፡ አግኝተነዋል ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውሉ ፡ በአንቀጽ ፡ ሦስት ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ተላልፎ ፡ አስቀድሞ ፡ የኹለት ፡ ወር ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ቤቱን ፡ እንዲለቅ ፡ ብሎ ፡ ለከሳሽ ፡ ኩባንያ ፡ በጥር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፱ ፡ ዓ. ም. የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ከኀባበት ፡ ውል ፡ ተቃራኒ ፡ ስለኾነ ፡ ደብዳቤውን ፡ ውድቅ ፡ እድርገን ፡ የዳኝነት ፡ በደረሰኝ ፡ ኪሣራ ፡ ዐምሳ ፡ ብር ፡ ተከሳሽ ፡ ለከሳሽ ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርደናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Com. Div. No. 2

S.A.C.A.F.E.T., SOCIETA' ANONIMA v. THE MINISTRY OF STATE DOMAINS AND MINES

Civil Case No. 178/54 E.C.

Constitution - - Property - - Expropriation - - Rights which are capable of expropriation - - Procedure for expropriation - - Arts. 44, 88, 89, 90 *Rev. Const. - - Art.* 1461 *Civ. C.*

In an action for injunction, the petitioner claimed that termination notice sent by the respondent under their lease agreement was insufficient in that the notice required was not given and the termination was not for "government use" as required by the lease; similarly that expropriation proceedings under Art. 1461 Civ. C. were not properly instituted, so that the respondent cannot now claim that an expropriation was intended.

Held: Permanent injunction granted.

1. The Civil Code provisions setting forth the procedure for expropriation constitute the special expropriation law referred to in Art. 44 Rev. Const.

2. If the government wishes to expropriate a person's rights under a lease, it must follow the procedures set down in the Civil Code, which contains the special expropriation law enacted pursuant to Art. 44 Rev. Const.

3. A simple letter from the Minister of Pen to the Ministry of State Domains to the effect that premises should be earmarked for a certain purpose, with no mention of an existing lease, does not amount to a ministerial order to breach the lease as is required by Art. 44 Rev. Const. and by the Civil Code.

Megabit 13, 1954 E.C. (March 22, 1962 G.C.); Judges: Dr. W. Buhagiar, Ato Josef Tekle Mikael, Ato Mekonnen Getahun: — In his statement of claim, the plaintiff company stated that there was an agreement of lease entered into between that company and the defendant Ministry for premises to be used as a workshop at Mexico Square for a period of one year ending on Maskaram 30, 1955. This agreement is evidenced by Contract of Lease No. 2167 (Exh. P/1). The plaintiff also stated that by letter dated Ter 22, 1954, No. 4731/3181/54, (Exh. P/2), the defendant Ministry requested the plaintiff company to vacate the said premises by Ter 30, 1954. It is submitted by the plaintiff company that such request to vacate the premises is contrary to the lease agreement, which, in clause 3, stipulates that in case the premises are required for *Government use*, the plaintiff company is to be notified at least two months in advance for the purpose of terminating the lease and handing over the premises. The plaintiff company further states that apart from the fact that the provisions of clause 3 of the agreement have not been followed as regards the notice to be given, the purpose for which the premises are required are not "for Government use"; in fact, the letter of Ter 22, 1954 clearly states that the premises have been assigned to the Chamber of Commerce; according to the submission of the plaintiff company the Chamber of Commerce is not a Government Department. Having premised the above, the plaintiff company prayed that the defendant Ministry

be enjoined from proceeding with the request of taking over the premises on Ter 30, 1954, and also prayed for a declaration that the notice (Exh. P/2) is contrary to the terms of the agreement and therefore null and void.

By interlocutory order dated Ter 29, 1954, this Court prohibited the defendant Ministry from proceeding with the eviction until further Order of Court.

By the defence, dated Yekatit 26, 1954, the defendant Ministry did not deny the facts as alleged in the statement of claim or any of the documents produced by the plaintiff company, but, the defence stated, the order for the taking over of the said premises for use as a Chamber of Commerce was given by His Excellency the Minister of Pen, and in support of this there was submitted a letter from that Ministry to the Vice Minister of the Imperial State Domains dated November 3, 1961, Ref. No. 1310/8/868/17, (Exh. D/1). Furthermore, it was submitted in the defence that it is possible to take over the said premises under the provisions of Article 1461 of the Civil Code. Now as regards the letter from the Ministry of Pen, this amounts to a direction that the premises in question be earmarked for the Chamber of Commerce; it is not an order for the immediate possession of the premises; furthermore, nothing is stated therein regarding the present existing lease in favour of the plaintiff company; such letter therefore cannot amount to an order to the defendant Ministry to breach the agreement existing in favour of the plaintiff company.

As regards the submission of the defendant Ministry that the lease could be taken over under the provisions of Article 1461 of the Civil Code, it is true that under the Civil Code the competent authority may take action to expropriate land and that under Article 1461 expropriation proceedings may be used for terminating a contract of lease prior to the agreed term, but the Civil Code lays down a definite procedure for expropriation. This procedure, as laid down in the Civil Code, is the special expropriation law enacted in accordance with Articles 88, 89, or 90 of the Revised Constitution, pursuant to Article 44 of that Constitution. In the present case, no expropriation proceedings have been taken in accordance with Article 44 of the Constitution or the articles of the Civil Code; it cannot, therefore, be said that there has been any expropriation, since if there had been, such expropriation would have been against the Constitution.

For the above reasons, the Court holds that article 3 of the lease agreement (Exh. P/1) has not been followed by the defendant Ministry in that, even if the premises in question were required for Government use, a notice of two months is required under article 3 for the termination of the lease and the evacuation of the premises, and therefore the notice given by the defendant Ministry by letter dated Ter 22, 1954 (Exh. P/2) is illegal and of no effect.

The defendant Ministry shall pay the plaintiff company court fees according to receipt and costs of E$100.

ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፤

አዲስ ፣ አበባ ፣ የንግድ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ኹለተኛ ፣ ችሎት ።

ኤች.ቪ.ኤ.ኢትዮጵያ ፣ ይግባኝ ፣ ባይ ፣ ያገር ፣ ውስጥ ፣ ኀቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ መልስ ፣ ሰጭ ።

የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ የንግድ ፣ ነገር ፣ ቍጥር ፣ ፭ / ፶፬ ፣ ዓ. ም ።

ቀረጥ — የገቢ ፣ ግብር — ቅነሳ — የመጓጓዣ ፣ ወጪ — የጽሑፍ ፣ ስምምነት — የገቢ ፣ ወጪ — ዋና ፣ ወጪ — ማደሻዎች ፤ የገቢ ፣ ግብር ፣ ድንጋጌ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም. (ድንጋጌ ፣ ቍጥር ፣ ፲፱ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም.) አንቀጽ ፣ ፶፱ — የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ ፲፱፻፶ ፣ ዓ. ም. አንቀጽ ፣ ፮ (ሀ) ፣ ፯ (ለ) ፣ ፯ (ረ) ፣ እና ፣ ፰ (ሠ) ።

፩ኛ ፤ ይግባኝ ፣ ባይ ፣ ኩባንያ ፣ ስለኩባንያው ፣ ምክር ፣ እንዲሰጡት ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ደርሶ ፣ መልስ ፣ ባለልዩ ፣ ችሎታዎች ፣ (ኤክስፐርቶች) ሲያስመጣ ፣ ለነሱ ፣ መጓጓዣ ፣ ያደረገው ፣ ወጭ ፣ በኤክስፐርቶቹና ፣ በኩባንያው ፣ መካከል ፣ በተደረገ ፣ የጽሑፍ ፣ ስምምነት ፣ መሠረት ፣ ባለመደረጉ ፣ ምክንያት ፤ ፪ተኛ ፣ ለመሥሪያ ፣ መኪናዎች ፣ የተደረገ ፣ የማደሻ ፣ ወጭ ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ የሚያገለግል ፣ በመኾኑ ፣ ዋና ፣ ወጭ፡ ስለኾነ ፣ እነዚህ ፣ ኹለቱም ፣ ወጭዎች ፣ ለታክስ ፣ እገማ ፣ ጉዳይ ፣ ከገቢ ፣ ላይ ፣ ተቀናሽ ፣ አይኾኑም ፣ ብሎ ፣ የታክስ ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚ ፣ ኮሚቴ ፣ ስለወሰነ ፣ ይግባኙ ፣ ቀረበ ።

ውሳኔ ፡- በመዝገቡ ፣ ወጪ ፣ ጉዳይ ፣ የተደረገው ፣ ውሳኔ ፣ ውድቅ ፣ ኹኖ ፣ ጉዳዩ ፣ ለኮሚቴው ፣ ተመልሶለት ፣ ወጥቶበታል ፣ ለተባለው ፣ ነገር ፣ ወጪው ፣ መውጣቱን ፣ ኮሚቴው ፣ እንዲያረጋግጥ፣ በኹለተኛው፣ ወጪ ፣ ጉዳይ ፣ ደግሞ ፣ የተደረገው ፣ ውሳኔ ፣ ውድቅ ፣ ኾኖ ፣ ወጪው ፣ ተቀናሽ ፣ እንዲኾን ፣ ተወስንዋል ።

፭ ፤ በሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ ፲፱፻፶ ፣ ዓ. ም. አንቀጽ ፣ ፮ (ለ) እና ፣ (ረ) መሠረት ፣ ለኤክስፐርቶች ፣ የተደረገ ፣ ወጪ ፣ መኖሩን ፣ ለማረጋገጥ ፣ በኤክስፐርቶቹና ፣ ኤክስፐርቶቹን ፣ ባስመጣው ፣ ኩባንያ ፣ መካከል ፣ የጽሑፍ ፣ ስምምነት ፣ መኖሩን ፣ ማሳየት ፣ አያሻም ።

፮ ፤ በሕግ ፣ ማስታወቂያ ፣ ክፍል ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ ፲፱፻፶ ፣ ዓ. ም. አንቀጽ ፣ ፰ (ሠ) መሠረት ፣ የዋና ፣ ግንዘብ ፣ ወጪ ፣ ማለት ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ የሚደረግ ፣ ለንግዱ ፣ ወይም ፣ ለሥራው ፣ ማዳበሪያ ፣ ወይም ፣ ጥቅም ፣ የሚኾን ፣ ቋሚ ፣ ሀብት ፣ የሚያስገኝ ፣ ወጪ ፣ ሲኾን ፣ የገቢ ፣ ግንዘብ ፣ ወጪ ፣ ማለት ፣ ግን ፣ በየዓመቱ ፣ የሚደጋገም ፣ ወጪ ፣ ነው ።

፫ ፤ ለንግዱ ፣ ወይም ፣ ለሥራው ፣ ወጪ ፣ የተደረገው ፣ ግንዘብ ፣ ወዲህ ፣ ዋና ፣ ግንዘብ ፣ (ካፒታል፣) የማያመጣ ፣ ከኾነ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ያለውን ፣ ዋና ፣ ግንዘብ ፣ ለማጠንከር ፣ (ማለት ፣ ለመሣሪያ ፣ ማደሻ፣) የተደረገ ፣ ሲሆን ፣ መሣሪያዎቹም ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ የሚያገለግሉ ፣ ወይም ፣ የማያገለግሉ ፣ ቢኾኑም ፣ ቅሉ ፣ እንደዚህ ፣ ያለው፡ ወጪ ፣ የገቢ ፣ ግንዘብ ፣ ወጪ ፣ እንጂ ፣ የዋና ፣ ግንዘብ ፣ ወጪ ፣ አይባልም ።

(የአዘጋጁው ፡ ማሳሰቢያ ፡- የገቢ ፣ ግብር ፣ ድንጋጌ ፣ ቍጥር ፣ ፲፱ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም. እና ፣ የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ ፲፱፻፶ ፣ ዓ. ም. የገቢ ፣ ግብር ፣ ደንብ ፣ ተሠርዘው ፣ በሌላ ፣ ሕግ ፣ ተተክተዋል ። በመዝገቡ ፣ ፈንታ ፣ የተተካው ፣ የገቢ ፣ ግብር ፣ ዐዋጅ ፣ ቍጥር ፣ ፭፻፫፫ ፣ ፲፱፻፺፩ ፣ ዓ. ም. ሲኾን ፤ በኹለተኛው ፣ ፈንታ ፣ የተተካው ፣ የሕግ ፣ ማስታወቂያ ፣ ክፍል ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፶፰ ፣ ፲፱፻፶፬ ፣ ዓ. ም. የገቢ ፣ ግብር ፣ ደንብ ፣ ነው ። ሕጉ ፣ ምንም ፣ ያክል ፣ ልዩነት ፣ አልተደረገበትም ። የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ አንቀጽ ፣ ፮ (ሀ) ፣ (ለ) እና ፣ ፰ (ሠ) በተተካው ፣ በሕግ ፣ ማስታወቂያ ፣ ክፍል ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፶፰ ፣ ውስጥ ፣ እንደዚያው ፣ እንደነበሩ ፣ ተጽፈዋል ። በዚህም ፣ በዐዲሱ ፣ ደንብ ፣ አንቀጽ ፣ ፲፯ (ሀ) ፣ (ለ) እና ፣ ፲፯ (ጨ) ተብለው ፣ ተጽፈዋል ። የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፲፭ ፣ አንቀጽ ፣ ፮ (ረ) በሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፶፰ ፣ ተጽፎ ፣ ባይገኝም ፣ ጠቅላላ ፣ ሐሳቡ ፣ ከዐዋጅ ፣ ቍጥር ፣ ፭፻፫፫ ፣ አንቀጽ ፣ ፲፯ ፣ ጋራ ፣ ተመሳሳይ ፣ ነው ። ኤክስፐርት ፣ መራተኞችን ፣ ስለሚመለከት ፣ ጉዳይ ፣ ዐዲሱ ፣ የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፻፶፰ ፣ ሌላ ፣ ተጨማሪ ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፲፯ (ሠ) ውስጥ ፣ ጨምሮአል ።)

መጋቢት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፱ ፡ ዓ. ም. ዳኞች ፦ ዶክተር ፡ ቦሐጅያር ፡ አቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ አቶ ፡ መኩንን ፡ ጌታዥን ። ይህ ፡ ይግባኝ ፡ የቀረበው ፡ የታክስ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ነሐሴ ፡ ፭፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፫ ፡ ዓ . ም ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ብመቃወም ፡ በ፲፱፻፺፱ ፡ ዓ. ም. በቅጥር ፡ ፲፩ ፡ በወጣው ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ድንጋጌ ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፱ ኛው ፡ መሠረት ፡ ነው ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኙን ፡ ያቀረቡት ፡ በኹለት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ፦ ከነዚህም ፡ ኹለት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለሚያከናውኑት ፡ ሥራ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ላስመጡአቸው ፡ ኤክስፔርቶች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደርሶ ፡ መልስ ፡ ለመጓጓዝ ያ ፡ ወጪ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ የኢት. ብር. 97,538 ሲኾን ፡ ሌላው ፡ ደ ግሞ ፡ ለሚሊንግሮልስ ፡ (ለዐገዳ ፡ መዳመጫዎች) ፡ ለመግሪያዎች ፡ ማደሻና ፡ ለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ወጪ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ የኢት. ብር. 122,769.50 ሒሳብ ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኙን ፡ ያቀረቡበት ፡ ምክንያት ፡ በ፲፱፻፺ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፮(ለ) ፡ ፯(ረ) በሚያዘው ፡ መሠ ረት ፡ ሊቀንስ ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ታክስ ፡ እንዲከፍልበት ፡ የታ ክስ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ በመወሰኑ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ተሳስቷል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ይኸው ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ አንቀጽ ፡ ፯(ሠ) ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ በትክክል ፡ አልተረጐመ ውም ፡ ወይም ፡ አልሠራበትም ፡ በማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ የኾነበት ፡ ምክንያት ፡ ይኸው ፡ አንቀጽ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ (ካፒታል ፡ ኤክስፔንዲቸር) በሚለው ፡ አርእስት ፡ ጠቅ ላላ ፡ ወጪንም ፡ ስለሚጠቅሰው ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ለታክስ ፡ ሊቀነስ ፡ የሚገባ ውንም ፡ ገንዘብ ፡ ይጠቀልላል ፡ ነው ።

ለኤክስፔርቶች ፡ ስለ ፡ ተከፈለው ፡ መጓጓዣ ፡ 97,538 ብር. ጉዳይ ፡ የሒሳብ ፡ ተቈጣጣሪው ፡ እንዳመለከቱት ፡ ስለዚህ ፡ ወጪ ፡ የተደረገ ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ባለ መኖሩ ፡ ይህ ፡ ወጪ ፡ ሊቀነስ ፡ አይቻልም ፡ በማለት ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ወስኗል ። ይህም ፡ ስለ ፡ ኩባንያው ፡ ማለት ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመምጣትና ፡ ከኢትዮጵያም ፡ በመኼድ ፡ ለተመላለሱት ፡ ኤክስፔርቶች ፡ የአየር ፡ መጓጓዣ ፡ ወጪ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፈል ፡ አይገባም ፡ ማለት ፡ ነው ።

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚቴ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ስምምነት ፡ ማድረጉን ፡ ጠይቋል ። ይግባኝ ፡ ባዮችም ፡ በሰጡት ፡ መልስ ፡ የቃል ፡ ስምምነት ፡ መኖሩን ፡ ገልጸዋል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚቴ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ወንጂ ፡ የስኳር ፡ ፋብሪካ ፡ ያለ ፡ ኩባንያ ፡ የቃል ፡ ስምምነት ፡ ብቻ ፡ ማድ ረግ ፡ ተገቢ ፡ ባለመሆኑ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወጪ ፡ ግብር ፡ እንዲከፈልበት ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ ወስኗል ።

በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ የማይረባና ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ስምምነት ፡ በጽሑፍ ፡ መደ ረግ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ የለም ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ እንደ ፡ ወንጂ ፡ ስኳር ፡ ፋብ ሪካ ፡ ያሉ ፡ ትልልቅ ፡ ኩባንያዎች ፡ ስለ ፡ ሠራተኞቻቸው ፡ አገልግሎት ፡ የራሳቸው ፡ ደንብና ፡ ድንጋጌ ፡ ያላቸው ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዮችም ፡ የኩባንያውን ፡ ደንብ ፡ እቅርበዋል ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ኤክስፔርቶቹ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲገቡ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የአቀረቡትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማመል ከቻዎች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቅርበው ፡ አሳይተዋል ። ይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ ለኩባንያው ፡ ገቢ ፡ ማዳበሪያ ፡ አስፈላጊ ፡ ለኾኑት ፡ ኤክስፔርቶች ፡ ወጪ ፡ ማድረጉን ፡ የሚያስረዱ በት ፡ በቂ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላል ። የኾነ ፡ ኹኖ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚመለከተው ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ አገባብ ፡ ነው ። በሕጉም ፡ መሠረት ፡ የኾነ ፡

እንደኾነ ፣ ገንዘቡ ፡ ወጪ ፣ ተደረገ ፡ ስተባለው ፡ ጉዳይ ፣ በርግጥ ፡ ለዚያው ፡ ወጪ ፣ መኾኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የጽሑፍ ፣ ማስረጃ ፣ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚቴ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ስሕተት ፡ ስለኾነ ፡ ሽረነዋል ።

ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገዘንብ ፡ (ወጪ ፡) ለኤክስፔርት ፡ ሠራተኞች ፡ ወጪ ፡ ማድረጋቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ ያሏቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ኹሉ ፡ እንዲያቀርቡ ፣ ጉዳዩን ፡ ለግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ መልሰነዋል ።

ኹለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ኢት. ብር. 122,769.50 ነው ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፷(ሠ) መሠረት ፡ ስለ ፡ ታክስ ፡ አገማመት ፡ ጉዳይ ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ (ካፒታል ፡ ኤክስፔንዲቸር ፡) የሚቀነስ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ክርክሩ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ አንቀጽ ፡ ፮(ሀ) ወይም ፡ ፮(ረ) መሠረት ፡ የተባለው ፡ ወጪ ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ (ካፒታል ፡ ኤክስ ፔንዲቸር) ወይም ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ መኾን ፡ አለመኾኑን ፡ መለየት ፡ ነው ።

ከኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ 3,120.00 በስተቀር ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወጪ ፡ የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ መኾኑን ፡ የታክስ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ አረጋግጦታል ። የታክስ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ የሒሳብ ፡ ተቋጣጣሪው ፡ የሰጠውን ፡ ሐሳብ ፡ ነው ።

የሒሳብ ፡ ተቋጣጣሪው ፡ በሰጠው ፡ ሐሳብ ፡ ይህ ፡ ወጪ ፡ ከፍ ፡ ላሉ ፡ ዕቃዎችና ፡ ለማደሻ ፡ ወጪ ፡ የተደረገ ፡ በመኾኑና ፡ ይህም ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የማይሸጥ ፡ ስለኾነ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወጪ ፡ በየጊዜው ፡ በመቀነስ ፡ ሪገድ ፡ በብዙ ፡ ዓመታት ፡ ላይ ፡ እንዲቻቻል ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡ ብለዋል ።

የሒሳብ ፡ ተቋጣጣሪው ፡ ሒሳቡን ፡ በሚመረምሩበት ፡ ጊዜ ፡ የተጠቀሱት ፡ ዕቃዎች ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ የሚያገለግሉ ፡ መኾናቸውን ፡ የፋብሪካው ፡ መሐንዲሶች ፡ የነገዱዋቸው ፡ መኾኑን ፡ አስረድተዋል ።

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በጉልሕ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወጪ ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፷(ሠ) መሠረት ፡ ለማሻሻያና ፡ ለመለወጫ ፡ የተደረገ ፡ ወጪ ፡ መሆኑን ፡ አልተገንዘበውም ። ኮሚቴው ፡ ውሳኔውን ፡ የሰጠው ፡ የታደሱትን ፡ ነገሮች ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የማይሸጡ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ የሒሳብ ፡ ተቋጣጣሪው ፡ በሰጠው ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ የኾነው ፡ ለማደሻ ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። በዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪና ፡ የገቢ ፡ ወጪ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ሙገንዘብ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። የነዚህንም ፡ ልዩነት ፡ ለማወቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ፤ በኾለቱም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ይህ ፡ ነው ። የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ ለንግዱ ፡ ወይም ፡ ለሥራው ፡ ማዳበሪያ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ የሚኾን ፡ ቋሚ ፡ ሀብት ፡ የሚያስገኝ ፡ ወጪ ፡ ነው ። የገቢ ፡ ወጪ ፡ ማስተካከያ ፡ በየ ዓመቱ ፡ የሚደጋገም ፡ ወጪ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሲኾን ፡ በንግድ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ መሣሪያዎች ፡ በማደስ ፡ ለንግዱ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ሀብት ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ የሚያመጡ ፡ ወይም ፡ የሚያስገኙ ፡ ነገሮች ፡ አይደሉም ። ሀብቱ ከዚያ ፡ በለጥ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ የማደሱ ፡ ሥራ ፡ ሀብቱ ፡ ለንግዱ ፡ ወይም ፡ ለሥራው ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ በደንብ ፡ በመሥራት ፡ ገቢ ፡ እንዲያስገኝ ፡ ለማድረግ ፡ የሚረዳ ፡ ነው ። በሌላ ፡ አገላለጽም ፡ ለንግዱ ፡ ወይም ፡ ለሥራው ፡ ወጪ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡

ወዲስ ፡ ካፒታል ፡ የማያወጣ ፡ ከኾነ ፡ ማለት ፡ ሕንጻውን ፡ በምሉ ፡ የማይለውጠው ፡ ከኾነ ፡ ያው ፡ ካፒታል ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ብቻ ፡ ወጪ ፡ የተደረገ ፡ ከኾነ ፡ የገቢ ፡ ወጪ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ከላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ፡ በክርክሩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ብር ፡ ከኀምሳ ፡ ሳንቲም ፡ 122,769.50 የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ (ካፒታል ፡ ኤክስፔንዲቸር) ነው ፡ ሲል ፡ የወሰነው ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሳሳተ ፡ ስለኾነ ፡ ውሳኔውን ፡ ሽረነዋል ። ይህ ፡ ወጪ ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፭ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭(ሀ) እና ፡ (ረ) መሠረት ፡ ተቀናሽ ፡ መኾን ፡ ይገባዋል ፡ በማለት ፡ ወስነናል ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ የዳኝነቱን ፡ በደረሰኝ ፡ ልዩ ፡ ኪሣራ ፡ ጎምላ ፡ (፱) ብር ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ እንዲከፍል ፡ አዘናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Com. Div. No. 2

H.V.A. ETHIOPIA v. THE INLAND REVENUE DEPARTMENT

Civil Case No. 20/54 E.C.

Taxation - - Income tax - - Deductions - - Travel expenses - - Written agreement - - Revenue expenditures - - Capital expenditures - - Repairs - - Art. 59 Income Tax Decree of 1956 *(Decree No.* 19/56*) - - Arts.* 7 *(a),* 7 *(b),* 7 *(f), and* 8 *(e) Leg. Not. No.* 215/58.

On appeal from a decision of the Tax Appeal Committee denying deductions from income for purposes of taxation (1) for traveling expenses of foreign experts traveling to and from Ethiopia in connection with the appellants' concern, on the ground that the appellants' concern had no written agreement with the experts in respect of such expenses, and (2) for expenses for repairs of machinery, etc., on the ground that the repairs were usable for a long term and therefore constituted capital expenditure, which is not deductible.

Held: Decision on the first point reversed and the matter referred back to the Committee to examine appellants' documents to see whether, as a matter of fact, the expenses were incurred for the alleged purpose; decision on the second point reversed and the expenditures ruled deductible.

1. No written agreement between a concern and expert personnel is required to establish that expenses were incurred by the concern for such personnel under Arts. 7 (b) and 7 (f) of Leg. Not. No. 215/58.

2. Capital expenditure, within the meaning of Art. 8 (e) of Leg. Not. No. 215/58, is an expenditure that is made once and for all and that brings into existence an asset or advantage for the enduring benefit of the trade or business, while a revenue expenditure is one which will recur year by year.

3. Where expenses incurred in the trade or business do not bring any new capital, but are only intended to maintain existing capital, such as repairs of machinery, whether or not usable for several years, such expenses constitute revenue expenditure and not capital expenditure.

(Ed. Note: The Income Tax Decree, 1956, Dec. No. 19/56, and the Income Tax Regulations, 1958, Leg. Not. No. 215/58, have been repealed and replaced, respectively, by the Income Tax Proclamation, 1961, Proc. No. 173/61, and the Income Tax Regulations, 1962, Leg. Not. No. 258/62. The law remains substantially the same, however, Arts. 7 (a), 7 (b) and 8 (e) of Leg. Not. No. 215 are the same as Arts. 16 (a). 16 (b) and 17 (b) (v) of Leg. Not. No. 258. Art. 7 (f) of Leg. Not. No. 215 does not appear in Leg. Not, No. 258, but is substantially the same as Art. 16 of Proc. No. 173. With regard to expenses for professional personnel, Leg. Not. No. 258 added a new provision in Art. 16 (c).)

Megabit 20, 1954 E.C. (March 29, 1962 G.C.); Judges: Dr. W. Buhagiar, Ato Josef Tekle Mikael, Ato Mekonnen Getahun: — This is an appeal under Article 59 of the Income Tax Decree of 1956 (Decree No. 19 of 1956) from two points in a decision of the Tax Appeal Committee given on September 4, 1961. These two points concern an item of E$97,538, which the appellants allege was incurred as traveling expenses of foreign experts traveling to and from Ethiopia in connection with the appellants' concern, and an item of E$122,769.50, which the appellants allege was incurred by them as expenses of a current nature such as milling rolls, repairing machinery, etc. The ground of the appeal is that the Tax Appeal Committee erred in law in assessing the appellant to pay tax on items which are deductible under Article 7 (b) and 7 (f) of Legal Notice No. 215

of 1958 and also erred in law in the interpretation and application of article 8 (e) of the said Legal Notice in that it included ordinary general expenses as "capital expenditure" and thus included amounts which should have been deducted for purposes of taxation.

Now with regard to the item of E$97,538, the Tax Appeal Committee considered that these expenses could not be deducted on the ground that, as the auditor pointed out, there were no written agreements concerning these expenses, that is, expenses for air passages for experts in the service of the appellant company who traveled to and from Ethiopia in connection with the work of the company. In the decision of the Tax Appeal Committee it is stated that that Committee asked the appellants whether there was any agreement about such expenses and the appellants replied that there were only verbal agreements; the Committee went on to state that taking into consideration the fact that for such an enterprise as the Wonji Sugar Factory to have only verbal agreements was unreasonable, the expenses should be subject to taxation. In the opinion of this Court, this is a poor and untenable argument. As a matter of fact, there is nothing in law which requires agreements of this nature to be in writing. Furthermore, it is well known that an enterprise of the scale of the Wonji Sugar Factory has its rules and regulations governing the terms of service of their employees, and in fact, appellants showed the Court such regulations of the appellant company. There has also been shown to the Court various applications to the Ministry of Interior regarding entry visas for the employees of the company in respect of whom such traveling expenses were incurred. It seems that the appellants have sufficient documentary evidence to show that these expenses were in fact incurred for their expert employees, who in turn are necessary for the production of the income. This Court is, however, concerned only with a point of law and as a matter of law this Court holds that no written agreement is required to establish that the expenses were incurred for the purpose alleged. On this point, therefore, the ruling of the Tax Appeal Committee is quashed as being legally untenable, and the matter is referred back to the Tax Appeal Committee to examine any documents the appellants have to satisfy the Committee that the expenses were incurred for expert personnel.

With regard to the second point, that is, the item of E$122,769.50, there can be no question that under Article 8 (e) of Legal Notice No. 215, capital expenditure is not deductible for purposes of assessing tax. The argument in this case is whether appellants' above-mentioned expenditures were capital expenditures or other expenditures under Article 7 (a) or Article 7 (f) of the said Legal Notice. The Tax Appeal Committee held that they were capital expenditure (except for an amount of E$3,120); the Tax Appeal Committee based itself on the opinion given by the auditor who suggested that the said expenses should be written off in a number of years in terms of depreciation because these were expenses made on goods and on repairs of a large scale, usable for a long term; the auditor also mentioned that during his examination he was told by the engineers of the factory that the said goods could be used for a number of years. It is quite clear from the decision of the Tax Appeal Committee that that Committee did not consider such expenses as being expenses incurred in improvement and alterations as laid down in Article 8 (e) of Legal Notice No. 215. Their decision was based solely on the suggestion of the auditor that the repairs were usable for a long term. There is no question, therefore, that these expenses were expenses for repairs. The distinction between capital expenditure and revenue expenditure is of great importance. Various tests may be suggested for this distinction, but substantially the distinction lies in this, that capital expenditure is an expenditure that is made once and for all and that brings into existence an asset or an advantage for the enduring benefit of the trade or business, while revenue expenditure is one which will recur year by year. Now there can be no question that any repairs which are carried out on machinery in a trade or business are an advantage to the trade but

they are not such as *bring into existence* an asset or an advantage; the asset was there already, and the repairs have the effect of enabling such asset to continue to bring income to the business, with more efficient working. In other words, where expenses incurred in the trade or business do not bring any new capital (such as the complete renewal of a building) but are only intended to maintain existing capital, they are revenue expenditure, not capital expenditure. For these reasons, the Court holds that the Tax Appeal Committee was wrong in law in deciding that the expenses of E$122,769.50 were capital expenditure, reverses their decision on this point, and decides that such expenses are deductible under Article 7 (a) and (f).

The respondent shall pay half the court fees, according to receipt, and costs of E$50 to the appellant.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ የንግድ ፡ ችሎት ።

ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ አብዲ ፡ አመልካች ፤ የጆቴ ፡ ወርቅ ፡ ለገሰ ፡ ተቃዋሚ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፸፻፻/፸፯ ፡ ዓ. ም ።

ውርስ—እንደራሴነት—የቤተሰብ ፡ ሀብት ፡ (ንብረት)—የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናትን ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ መስጠት—የፀላባ ፡ መብት—የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አሳቅጽ ፡ ፭፻፱ ፡ ፭፻፱፭ ፡ ፭፻፱፻ ፡ ፭፻፱፫ ፡ ፭፻፱፱ ፡ እና ፡ ከፍ፻፱፪ ፡ እስከ ፡ ፭፻፱፯ ።

ሕግን ፡ መተርጐም ።

የሚች ፡ እናት ፡ የውርስ ፡ መብታቸው ፡ እንዲታወቅላቸው ፡ ባደረጉት ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ የሚች ፡ በአባት ፡ ወገን ፡ ወንድም ፡ የኾነ ፡ ንብረቱ ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ የመጣ ፡ የዘር ፡ ንብረት ፡ ስለኾነ ፡ እኔም ፡ የአባቱ ፡ እንደራሴ ፡ እንደመኾኔ ፡ መጠን ፡ የሚች ፡ እናት ፡ ላይኾኑ ፡ እኔ ፡ መውረስ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ መቃወሚያ ፡ አቀረበ ።

ውሳኔ ፡- የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቃወሚያውን ፡ አክብሮታል ።

፩ ፤ ሚች ፡ ወደታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ሳይተካ ፡ ከሞተ ፡ ንብረቱን ፡ ሊወርሱ ፡ የሚችሉት ፡ ወላጆቹ ፡ ናቸው ፤ በዚህም ፡ ወይነት ፡ ኹኔታ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የንብረቱን ፡ ግማሽ ፡ ለመውረስ ፡ ይችላሉ ።

፪ ፤ አባት ፡ ከወላጆቹ ፡ ቀድሞ ፡ ሲሞት ፡ በሱ ፡ እግር ፡ የሚተኩት ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቹ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናትን ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ ስለመስጠት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፶፱ ፡ ውስጥ ፡ የተደነገገው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ንብረቱን ፡ ካፈራው ፡ ባለ ፡ ሀብት ፡ ሳያጸርጥ ፡ ወደ ፡ ኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትውልድ ፡ ለኾኑት ፡ ደረጃዎች ፡ ይወርዳል ፡ የሚለውን ፡ ጠቅላላ ፡ የውርስ ፡ ደንብ ፡ ሳይከተል ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ ሕግ ፡ ያቀማል ።

፬ ፤ የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናትን ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ በመስጠት ፡ ሕግ ፡ የሚተዳደር ፡ ንብረት ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ የመጣው ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ ሊተላለፍ ፡ አይቻልም ፤ እንዲሁም ፡ ከእናት ፡ ወገን ፡ የመጣው ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ ሊተላለፍ ፡ አይቻልም ።

፭ ፤ በአባት ፡ ወይም ፡ በእናት ፡ ወገን ፡ ወራሽ ፡ የሌለ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ የሕጉ ፡ በላማ ፡ ዋጋ ፡ አይኖረው ምና ፡ ተፈጻሚ ፡ አይኾንም ።

፮ ፤ ንብረቱ ፡ "የዘር ፡ ንብረት ፡" ባይኾን ፡ ኑሮ ፡ ንብረቱን ፡ ሊወስድ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ የፀላባ ፡ (የሪም ፡) መብቱ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ነው ።

፯ ፤ ማንኛውም ፡ በሕግ ፡ ውስዋ ፡ የተጻፈ ፡ ቃል ፡ ሲተረጕም ፡ ዋጋ ፡ ሊያስገኝለት ፡ የሚችለውን ፡ ትር ጕም ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ የሕግ ፡ ትርጕም ፡ ደንብ ፡ እንዱ ፡ ነው ።

ጎሐር ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ. ም ። ዳኞች ፤- አቶ ፡ በላቸው ፡ ወሥራት ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ጌታኹን ፡ ብላታ ፡ ይሥሐቅ ፡ ተፈሪ ። አመልካች ፡ ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወር ቅ ፡ አብዲ ፡ ከአቶ ፡ ለገሰ ፡ ወርቅ ፡ እንግዳ ፡ የወለዱት ፡ ቃለ ፡ አብ ፡ ለገሰ ፡ የሚባለው ፡

ልጃቸው ፡ ዘር ፡ ሳይተው ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ውርሱ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ይህን ፡ መዝገብ ፡ ከ ፍተዋል ።

ተቃዋሚ ፡ እንዳለም ፡ ለማወቅ ፡ በጋዜጣ ፡ ጥሪ ፡ ተደርጎ ፡ የሚቹ ፡ ወንድም ፡ አቶ ፡ የጅቴ ፡ ወርቅ ፡ ለገሰ ፡ ቀርበዋል ። ተቃዋሚው ፡ የሚቹ ፡ የቃለ ፡ አብ ፡ ለገሰ ፡ ንብረት ፡ ከዘር ፡ የመጣ ፡ ንብረት ፡ ስለኾነ ፡ ለርሳቸው ፡ እንጂ ፡ ባዕድ ፡ ለኾኑት ፡ ለአመልካች ፡ አይገባም ፡ በማለት ፡ አመልክተዋል ።

ቃለ ፡ አብ ፡ የአቶ ፡ ለገሰ ፡ እና ፡ የአመልካች ፡ ልጅ ፡ መኾኑ ፡ አልተካደም ። የቃለ ፡ አብም ፡ ንብረት ፡ የመጣው ፡ ከአቶ ፡ ለገሰ ፡ ወርቅ ፡ ከፈታውራሪ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ መኾኑን ፡ አመልካች ፡ ሚያዝያ ፡ ፭/፸፮ ፡ በጻፉት ፡ ማመልከቻ ፡ ገልጠዋል ።

ሳይናዘዝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ ከቁ. ፰፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ቁ. ፰፻፶፮ ፡ ባሉት ፡ የፍ ትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕጎች ፡ ተወስኗል ።

ቃለ ፡ አብ ፡ ለገሰ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ሳይተካ ፡ ከሞተ ፡ ንብረ ቱን ፡ ሊወርስ ፡ የሚችሉት ፡ ወላጆቹ ፡ ናቸው ። ወላጆቹም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የንብረቱን ፡ ግማሽ ፡ ለመውረስ ፡ ይችላሉ ። ከወላጆቹ ፡ አባቱ ፡ በሕይወት ፡ ስለሌሉ ፡ የአባትየውን ፡ ድርሻ ፡ የአቶ ፡ ለገሰ ፡ ወርቅ ፡ እንግዳ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ በምትክነት ፡ ሊወርስ ፡ ይችላል ። ተቃዋሚው ፡ አቶ ፡ የጅቴ ፡ ወርቅ ፡ ለገሰ ፡ የአቶ ፡ ለገሰ ፡ ወርቅ ፡ ልጅ ፡ ስለኾኑ ፡ በአባታቸው ፡ እግር ፡ ገብተው ፡ ለአባታቸው ፡ ይደርስ ፡ የነበረውን ፡ የቃለ ፡ አብን ፡ ንብረት ፡ ግማሽ ፡ በውርስ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ የቃለ ፡ አብ ፡ ለገሰን ፡ ንብረት ፡ አኹን ፡ ለመውረስ ፡ የሚችሉት ፡ ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ አብዲና ፡ አቶ ፡ የጅቴ ፡ ወርቅ ፡ ለገሰ ፡ ይኾናሉ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የቃለ ፡ አብ ፡ ንብረት ፡ የዘር ፡ ንብረት ፡ ስለኾነ ፡ አመልካች ፡ መውረስ ፡ አይገባቸውም ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ ችግርን ፡ ይፈጥራል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፰፻፶፱(፩) እና ፡ (፪) መሠረት ፡ ለሚቹ ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ ከ አባቱ ፡ መሥመር ፡ ወጣ ፡ የመጣለትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለእናት ፡ መሥ መር ፡ ወጣ ፡ ለኾኑ ፡ ወራሾች ፡ በርስትነት ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ። እንዲሁም ፡ ከእናት ፡ መሥመር ፡ ወጣ ፡ በተባለው ፡ ዐይነት ፡ የመጣለትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የአ ባት ፡ መሥመር ፡ ወጣ ፡ ለኾነ ፡ ወራሽ ፡ በወራሽነት ፡ ለመስጠት ፡ አይቻልም ። የሕ ጉም ፡ ዐላማ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሲተላለፍ ፡ የቈየውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዘመድ ፡ ላልኾነ ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ እንዳይሰጥ ፡ ለማድረግ ፡ መኾኑ ፡ የተሰወረ ፡ አይደለም ። በአባት ፡ ወይም ፡ በእናት ፡ ወገን ፡ ወራሽ ፡ የሌለ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ የሕጉ ፡ ዐላማ ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውምና ፡ ተፈጻሚ ፡ አይኾንም ።

"የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናትን ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡" የሚለውን ፡ ደንብ ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ አስቀድሞ ፡ "የዘር ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡" የሚባ ለው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የትኛው ፡ እንደኾነ ፡ መወሰን ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ ግልጥ ፡ የኾነ ፡ ርዳታን ፡ አይሰጥም ።

ቁ. ፰፻፶፱(፫) ፡ "ከአባት ፡ ወገን ፡ አያት ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ የተገ ኘው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የእናት ፡ ወገን ፡ ለኾነ ፡ ተወላጅ ፡ እንዳይተላለፍ ፤ እንዲሁም ፡ ከእናት ፡ ወገን ፡ አያት ፡ የተገኘው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ከኹለት ፡ ጎይለ-ቃሎች ፡ የተነካው ፡ ደንብ ፡ ለኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትውልድም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይኾናል ፡" ይላል ።

"ለኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትውልድም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይኾናል ፡" የሚለው ፡ አንጋገር ፡ ከሌ

ሎቹ ፣ የቀደሙት ፣ ሥጥሮች ፣ ጋራ ፣ የተያያዘ ፣ መስሎ ፣ ስለማይታይ ፣ ዐሳቡ ፣ ግልጥ ፣ ኹኖ ፣ አይገኝም ።

የትውልድ ፣ ደረጃ ፣ እቁጣጠር ፣ በቍ. ፭፻፶ ፣ እና ፣ ፭፻፶፭ ፣ እንደ ፣ ተነገረው ፣ ነው ። "ለኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ፡" የተባለው ፣ በቍ. ፭፻፶ ፣ እና ፣ በቍ. ፭፻፶፭ ፣ የተገለጠውን ፣ የሚመለከት ፣ እንጂ ፣ አንዳንድ ፣ ሰዎች ፣ እንደሚያስቡት ፣ "የመዠመሪያ ፣ ዝምድና ፣ ደረጃ ፣ ... ኹለተኛ፣ የዝምድና ፣ ደረጃ ፣ እየተባለ ፡" በቍ. ፭፻፶፱ ፣ እና ፣ ፭፻፶፫ ፣ የተነገረውን ፣ አይደለም ። ምክንያቱም ፣ ግልጥ ፣ ነው ። "የመዠመሪያ ፣ ዝምድና ፣ ደረጃ ፡" (፭፻፶፱) ልጆችን ፣ የልጅ ፣ ልጆችን ፣ እና ፣ ማንኛውንም ፣ ወደ ፣ ታች ፣ የሚቈጠር ፣ ተወላጅ ፣ ሲጨምር ፣ የመዠመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፣ ማን ፣ ወላጆችንና ፣ ልጆችን ፣ ብቻ ፣ ይመለከታል ። "የኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ፡" አያቶችንና ፣ ልጆችን ፣ ብቻ ፣ ይመለከታል ።

በቍ. ፭፻፶፭(ፎ) የተነገረው ፣ "ኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፡" የሚቈጠረው ፣ ከሟች ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ ነውን ፣ ወይስ ፣ ከላይ ፣ ወደ ፣ ሟቹ? ከቅም-ቅም ፣ አያት ፣ የመጣ ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ቢኖርና ፣ "ለኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ፣ ተፈጻሚ ፣ ይኾናል ፡" የተባለው ፣ ከሟቹ ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ የሚቈጠረውን ፣ ነው ፣ ቢባል ፣ የተባለው ፣ ንብረት ፣ ሟች ፣ አያት ፣ ዘንድ ፣ ሲገባ ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፣ "ይኾንና ፣ ወደ ፣ ሟቹ ፣ አባትና ፣ ወደ ፣ ሟቹ ፣ ሲተላለፍ ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" መኾኑ ፣ ይቀራል ፣ ማለት ፣ ይኾናል ። እንዲሁም ፣ ከላይ ፣ ወደ ፣ ሟቹ ፣ የሚቈጠረውን ፣ ነው ፣ የተባለ ፣ እንደኾነ ፣ ንብረቱን ፣ ከአፈራው ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ እስከ ፣ ኹለት ፣ ትውልድ ፣ ድረስ ፣ ብቻ ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" ይኾናል ፣ ማለት ፣ ነው ። ቀደም ፣ ብሎ ፣ እንደተገለጠው ፣ ግን ፣ የሕጉ ፣ መንፈስ ፣ እንደ ዚህ ፣ አይደለም ። የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ከትውልድ ፣ ወደ ፣ ትውልድ ፣ እየተሳለፈ ፣ ሲኼድ ፣ "የዘር ፣ ንብረትነቱ ፡" የበለጠውን ፣ እየጠነከረ ፣ ይኼዳል ፣ እንጂ ፣ አይላላም ። "ለኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ፡..." የተባለውን ፣ በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ መንገድ ፣ መተር ጕም ፣ የሕጉን ፣ መንፈስ ፣ መከተል ፣ ኹኖ ፣ አይገኝም ።

"ለኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ፣ ተፈጻሚ ፣ ይኾናል ፡" የተባለው ፣ አንጋገር ፣ ዋጋ ፣ እንዲኖረው ፣ ይገባል ። ማንኛውም ፣ በሕጉ ፣ ውስጥ ፣ ተጽፎ ፣ የሚገኝ ፣ ቃል ፣ ዋጋ ፣ አለው ፣ ተብሎ ፣ ይታሰ፡ል ። ዋጋ ፣ የሌለው ፣ መስሎ ፣ ሲገኝም ፣ ዋጋ ፣ ሊያስገኝ ለት ፣ የሚችለውን ፣ ትርጒም ፣ መስጠት ፣ ይገባል ። ይኸውም ፣ የሕግ ፣ ትርጒም ፣ ደን ቦች ፣ ከኾኑት ፣ እንዱ ፣ ነው ።

ስለዚህ ፣ በእኛ ፣ አስተያየት ፣ "ለኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድም ..." የተባለው ፣ አንጋገር ፣ ከክፍሉ ፣ ዐሳብ ፣ ጋራ ፣ ተቀናብሮ ፣ ዋጋ ፣ ሊያገኝ ፣ የሚችለው ፣ "የዘር ፣ ንብ ረት ፡" የሚባለውን ፣ ለመለየት ፣ ሲያስችል ፣ ነው ። በዚህም ፣ ትርጒም ፣ መሠረት ፣ አንድ ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" ነው ፣ የሚባለው ፣ ንብረቱን ፣ ከአፈራው ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ ወደ ፣ መዠመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፣ ተላልፎ ፣ ከዚያም ፣ ወደ ፣ ኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፣ ሲደርስ ፣ ነው ። ንብረቱን ፣ በአፈራው ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ በዕርግጥ ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" አይባልም ። ንብረቱን ፣ በተረከበው ፣ በመዠመሪያ ፣ ትው ልድ ፣ እጅም ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" አይኾንም ። ንብረቱን ፣ በወረሰው ፣ ወይም ፣ በስጦታ ፣ በአገኘው ፣ የኹለተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፣ እጅ ፣ ግን ፣ "የዘር ፣ ንብረት ፡" ይኾናል ። ያን ፣ ጊዜና ፣ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ቍ. ፭፻፶፱(፩) ፣ እና ፣ (፪) ተፈጻሚዎች ፣ ይኾናሉ ። እን ግዲህ ፣ ከአባት ፣ ወገን ፣ የመጣውን ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ለእናት ፣ ወገን ፣ ያለማ ስተላለፉ ፣ ከእናት ፣ ወገን ፣ የመጣውንም ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ለአባት ፣ ወገን ፣ ያለማስተላለፉ ፣ ደንብ ፣ ተፈጻሚ ፣ የሚኾነው ፣ ንብረቱን ፣ ለአፈራው ፣ ሰው ፣ የኹለ ተኛ ፣ ደረጃ ፣ ትውልድ ፣ ለሚኾኑትና ፣ ለተከታዩ ፣ ትውልዶች ፣ ነው ።

የያዝነውን ፣ ጉዳይ ፣ በዚህ ፣ ዐይን ፣ ስናይ ፣ የቃለ ፣ አብ ፣ ለገሰ ፣ ንብረት ፣ ከአ ያቱ ፣ በአባቱ ፣ በሞል ፣ ስለ ፣ መጣ ፣ ኹለተኛ ፣ የትውልድ ፣ ደረጃ ፣ ላይ ፣ ያለ ፣ ንብረት ፣ ኹኖ ፣ ‘‘የዘር ፣ ንብረት ፣’’ ይኾናል ። ከአባት ፣ ወገን ፣ በውርስ ፣ የመጣ ፣ የማይንቀሳቀስ፣ ‘‘የዘር ፣ ንብረት፣’’ ስለኾነም ፣ ለቃለ ፣ አብ ፣ እናት ፣ ለአመልካቿ ፣ በርስትነት ፣ ሊደርሳ ቸው ፣ አይችልም ።

‘‘የዘር ፣ ንብረት ፣’’ ባይኾን ፣ ኑሮ ፣ አመልካቿ ፣ የልጇቸውን ፣ ግማሽ ፣ ንብረት፣ ለማግኘት ፣ ይችሉ ፣ ስለ ፣ ነበርና ፣ ‘‘የዘር ፣ ንብረት ፣’’ በመኾኑ ፣ ምክንያት ፣ ይህን፣ መብታቸውን ፣ ስላጡ ፣ በቍ. ፷፻፶(፩) የተደነገገው ፣ ተፈጸሚ ፣ ይኾንላቸዋል ።

ስለዚህ ፣ የቃለ ፣ አብ ፣ ለገሰን ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ በምሉ ፣ አቶ ፣ የጀቴ ፣ ወርቅ ፣ ለገሰ ፣ በርስትነት ፣ እንዲረከቡ ፣ በዚሁ ፣ በቃለ ፣ አብ ፣ ንብረት ፣ ግማሽ ፣ ላይ ፣ ግን ፣ አመልካቿ ፣ በሕይወት ፣ እስከ ፣ አሉ ፣ ድረስ ፣ የሪም ፣ መብት ፣ እንዲኖራቸው ፤ ይህም ፣ ቃለ ፣ አብ ፣ ለገሰ ፣ ከሞተበት ፣ ቀን ፣ ዠምሮ ፣ እንዲፈጸም ፣ በማለት ፣ ወስነናል ።

ባለጉዳዮቹ ፣ የደረሰባቸውን ፣ ኪሣራ ፣ ይቻሉ ።

ውሳኔው ፣ በፍርድ ፣ አስፈጻሚ ፣ በሞል ፣ እንዲፈጸም ፣ ትእዛዝ ፣ ይተላለፍ ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Com. Div.

TENAGNE WORKE ABDI v. YEJOTE WORKE LEGESSE

Civil Case No. 202/56 E.C.

Successions - - Representation - - Family property - - Paterna paternis materna maternis - - Usufructuary right - - Arts. 550, 551, 842, 843, 849, *and* 842-856 *Civ. C.*

Statutory interpretation.

In response to a petition by the mother of the deceased for a declaration of her successional rights, the half-brother of the deceased objected that the property in question was family property from the paternal line and, therefore, should devolve upon him as the representative of his father rather than upon the deceased's mother.

Held: Objection sustained.

1. Where the deceased is not survived by a descendant, his father and mother shall be called to his succession and each shall receive half of the inheritance.

2. A predeceased father shall be represented by his descendants.

3. The rule *paterna paternis materna maternis*, which is contained in Art. 849 Civ. C., provides an exception to the general successional rules in the case of immovable property that has devolved without interruption to the second degree (generation), and later degrees, from the person who first acquired it.

4. Property that is subject to the rule *paterna paternis materna maternis* shall not be transferred from the paternal line of the family to the maternal, or vice versa.

5. In the absence of an heir in either the paternal line or the maternal line, the rationale for the rule may disappear, together with its legal effect.

6. The person who would be entitled to the property if it were not "family property" is still entitled to a usufructuary interest in it.

7. It is a principle of statutory interpretation that every word of the law is to be construed in such a way as to have a meaning.

Hedar 15, 1957 E.C. (December 24, 1964 G.C.); Judges: Ato Belatchew Asrat, Ato Mekonnen Getahun, Blatta Yishack Tefferi: — Woz. Tenagne Worke Abdi petitioned the Court to declare her right to the estate of her son, Kaleab Legesse, who died intestate without a descendant.

In reply to notice given in a newspaper, the deceased's half-brother, Ato Yejote Worke Legesse, appeared and filed an objection that the inheritance should devolve on him and not on the petitioner. The ground for his objection is that the immovables constituting the succession are family property derived from the paternal line of the deceased's family, and cannot, therefore, be assigned to the maternal line.

It is conceded that the deceased was the son of the petitioner and Ato Legesse Worke

Ingida. The petitioner stated in her petition of Miazia 1, 1956 E.C. that the property of the deceased is derived from the deceased's paternal grandfather.

Questions of intestate succession are governed by Articles 842-856 of the Civil Code.

Where the deceased is not survived by a descendant, his father and mother shall be called to his succession. The father and mother shall each receive a half of the inheritance. The predeceased father shall be represented by his descendants. The respondent is the son of Ato Legesse Worke and can, therefore, represent his father. Hence Woz. Tenagne Worke Abdi and Ato Yejote Worke Legesse are the persons entitled to the deceased's succession.

The objection that the deceased's property deriving from the paternal line should not be assigned to the petitioner raises a problem. Article 849 lays down the rule "paterna paternis materna maternis." It is evident that the rationale for the rule is to prevent the transfer of immovable property outside natural relations. In the absence of an heir in either the paternal line or the maternal line, the rationale for the rule may disappear, together with its legal effect.

Before the rule "paterna paternis materna maternis" can be put into effect, one has to determine what is "family property or family land." The law does not define these terms unequivocally.

Article 849 (3) states: "The rules laid down in sub-articles (1) and (2) shall apply up to the second degree so that immovable property deriving by donation or succession from the grandpaternal line be not assigned to an heir of the grandmaternal and vice versa."

The phrase "shall apply up to the second degree" does not seem to be related to the preceding articles and, therefore, the concept is not clear.

Degree of relationship is governed by Articles 550 and 551. "The second degree" mentioned in Article 849 (3) refers to Articles 550 and 551; it does not refer to "first relationship" and "second relationship" as they are used in Articles 842 and 843. "First relationship" in Article 842 includes children, grandchildren and any other descendants, while "the first degree" (generation) includes only parents and children. "The second degree" (generation) includes grandparents, parents, and children.

Is "the second degree" mentioned in Article 849 (3) to be counted from the deceased or from ascendants toward the deceased? If there is immovable property deriving from a great-great-grandfather and if we count the "degree" up from the deceased, the property becomes "family property" when it is traced back to the grandfather, but ceases to be "family property" upon passing to the deceased's father and to the deceased himself. If the degree is counted toward the deceased, it means that the property shall be considered "family property" at the second generation from the first owner of the property. As stated above, this is not in accordance with the spirit of the law. The familial nature of an immovable never weakens; it strengthens the longer it is handed down through the generations. To interpret "the second degree" (generation) in a sense that weakens the familial nature of property upon the passing of an additional generation would be to deviate from the spirit of the law.

The phrase "shall apply up to the second degree" must be given effect. Every word of the law is construed to have a meaning. If it appears to be meaningless at first, it must be construed in such a way that it has a meaning. This is one of the principles of statutory interpretation.

In our opinion, "the second degree" (generation) referred to can have meaning within the spirit of the section where it helps to determine what is "family property." According to this construction, an immovable is "family property" when it passes from the first owner to the first degree (generation) and then from there on to the second degree (generation). It cannot be considered "family property" upon acquisition by the first owner, nor upon devolution on the first degree (generation). As soon as the second degree (generation) receives the property by succession or donation, it becomes "family property." From then on, Article 849 (1) and (2) can apply. The rule "paterna paternis materna maternis" therefore applies to immovable property that has devolved without interruption to the second degree (generation), and later degrees, from the person who first acquired it.

The immovable property of Kaleab Legesse derives from his grandfather through his father and, in light of our discussion, is "family property." As such it cannot be assigned to the deceased's mother, the petitioner. The petitioner would have been entitled to half the property if it were not "family property" derived from the paternal line. She is still entitled to the rights reserved under Article 850 (1).

Effective upon the death of the deceased, the ownership over the immovable property of the deceased must devolve upon Ato Yejote Worke Legesse, while the petitioner keeps her usufructuary right to one half of such property.

The parties shall defray their own costs.

The execution officer shall be instructed to execute the decision accordingly.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ የንግድ ፡ ችሎት ።

አቶ ፡ ተፈራ ፡ ግዛው ፡ እመልካች ፤ ወይዘሮ ፡ መና ፡ ተቃዋሚ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፱/፶፬ ፡ ዓ. ም ።

የማደን ፡ ልጅነት ፡ (ጉዲፈቻ ፡) ልማዳዊ ፡ ሕግ—የሚፈጸሙ ፡ ሥርዐቶች—የማር ፡ ልጅ ።

አመልካች ፡ እኅቱ ፡ ወራሽ ፡ ሳይኖራትና ፡ ሳትናዘዝ ፡ ሞታለችና ፡ ሀብቷን ፡ (ንብረቷን ፡) እኔ ፡ መውረስ ፡ አለብኝ ፡ ባለው ፡ ላይ ፡ የሚችዋ ፡ የማር ፡ ልጅና ፡ በምስጢርም ፡ የማደን ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ እኔ ፡ መውረስ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ሌላ ፡ ተቃዋሚ ፡ ቢቀርብም ፡ ሀብቱን ፡ አመልካች ፡ እንዲወርስ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለፈረደ ፡ ፍርዱ ፡ ቀጥኖብኛልና ፡ ይግባኝ ፡ ቢባል ፡ ጠቅላይ ፡ ፍትሑ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነጥሩ ፡ እንደ ገና ፡ እንዲታይ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመለሰው ፡ ለኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ቀረበ ።

ውሳኔ ፡- አመልካች ፡ እንዲወርስ ፡ ተፈረደ ።

፩ ፤ የማር ፡ ልጅነት ፡ የመፋቀርንና ፡ የቀረበ ፡ ግንኙነትን ፡ የሚፈጥር ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ እንደ ፡ ውርስ ፡ የመውረስን ፡ መብት ፡ ያለ ፡ የማደን ፡ ልጅነት ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ አይፈጥርም ።

፪ ፤ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የማደን ፡ ልጅነትን ፡ ለመፍጠር ፡ የኹለቱንም ፡ ወገኖች ፡ ፍላጎትና ፡ ፈቃድ ፡ በግልጥ ፡ የሚያሳይ ፡ ሥርዐት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

፫ ፤ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ሰዎች ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ በምስጢር ፡ የሚደረግ ፡ የማደን ፡ ልጅነት ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ ፍላጎትና ፡ ሕሳብ ፡ በርግጥ ፡ መኖሩን ፡ የሚያጠራጥር ፡ ስለኾነ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የማደን ፡ ልጅነት ፡ አለ ፡ አይባልም ።

ጥር ፡ ፭፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም ። ዳኞች ፡- አቶ ፡ በላቸው ፡ ዐሥራት ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ጌታቹን ፡ ብሳታ ፡ ይሥሐቅ ፡ ተፈሪ ። ወይዘሮ ፡ በቀለች ፡ ግዛው ፡ ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ሊወርሳቸው ፡ የሚችል ፡ ተወላጅ ፡ ሳይተዉ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ውርሱ ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ ወንድማቸው ፡ አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ግዛው ፡ ይህን ፡ መዝገብ ፡ ከፍተዋል ።

ዐያሌ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ቀርበው ፡ ጉዳያቸውን ፡ ካመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ውርሱ ፡ ለእመልካች ፡ ብቻ ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የካቲት ፡ ፭፭ ፡ ቀን ፡ ፶፭ ፡ ፈረደ ።

ከተቃዋሚዎች ፡ መካከል ፡ ወይዘሮ ፡ መና ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ ስለ ፡ አሉ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቍ. ፬፻፹፱/፶፭ ፡ "የማር ፡ ልጅ" እደራረጉ ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ መኾኑን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መርምሮ ፡ እንደ ገና ፡ እንዲፈርድ ፡ ሲል ፡ ጥር ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፶፭ ፡ ስለ ፡ ወሰነ ፡ ጉዳዩ ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀጠለ ።

ወይዘሮ ፡ መና ፡ የማር ፡ ልጅ ፡ መኾኔን ፡ ያስረዱልኛል ፡ ያሉዋቸው ፡ ምስክሮች ፡ ተሰሙ ፤ እመልካችም ፡ አፍራሽ ፡ ምስክሮችን ፡ አሰሙ ።

ወይዘሮ ፣ መና ፣ ‘‘እንዶ ፣ ልጅ ፣ እንደ ፣ ወራሽ ፣ ቆራሽ ፣ በሚጀ ፣ ብቻ ፣ ያደጉ ፣’’ መኾኑንና ፣ ‘‘በሚችቷ ፣ የተዳሩና ፣ የተኳሉ ፣ ለመኾኑ ፣’’ ማስረጃ ፣ እንዲያቀርቡ ፣ ጠይቀው ፣ ይህ ፣ ዋያቄ ፣ በማደን ፣ ልጅነት ፣ ዋያቄ ፣ ውስጥ ፣ አግባብ ፣ የለውም ፣ ሲል ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ወስኖባቸዋል ።

በጠቅላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ውሳኔ ፣ መሠረት ፣ በአገር ፣ ልማድ ፣ ደንብ ፣ ወይዘሮ ፣ መና ፣ የማደን ፣ ወይም ፣ የማር ፣ ልጅ ፣ እለመኾናቸውን ፣ መርምረናል ።

፩ኛ ፤ የተቃዋሚ ፣ (የወይዘሮ ፣ መና ፣) ምስክር ፣ ወይዘሮ ፣ ሥርጕተ ፣ ወልደ ፣ ዮሐንስ ፣ ‘‘ወይዘሮ ፣ መና ፣ ክርስትና ፣ ተነሱና ፣ ወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ የክርስትና፡ እናት ፣ ኾኑ፤ ተጋባገሮች ፣ የተጠሩት ፣ ለክርስትና ፣ ነው ፤ ወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ በማደን ፣ ለመውለድ ፣ ያደረጉት ፣ በምስጢር ፣ ነው ፤ ልብስና ፣ ሻሽ ፣ መጠቅለያ ፣ አመጡላቸው ፣ (ለወይዘሮ ፣ መና)፤ ‘በማርና ፣ በወተት ፣ አሳድጋቸዋለኹ ፤ ከዛሬ ፣ ዠምሮ ፣ ልጂ ፣ አደርጋቸዋለኹ’ ብለዋል፣’’ ሲሉ ፣ መስክረዋል ። እኻህ ፣ ምስክር ፣ የወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ ወላጅ ፣ እናት ፣ ናቸውና ፣ ጉዳዩን ፣ የበለጠ ፣ ሳያውቁ ፣ አይቀርም ፣ የሚል ፣ ግምት ፣ በሚገባ ፣ ዐድሮብ ናል ። እኻህ ፣ ምስክር ፣ ‘‘ወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ ወይዘሮ ፣ መናን ፣ በማደን ፣ ለመውለድ ፣ የፈለጉት ፣ በምስጢር ፣ ነው ፣’’ ሲሉ ፣ የመሰክሩት ፣ የጉዳዩ ፣ መፍትሔ ፣ መሠረት ፣ ነው ።

ይህን ፣ ‘‘በምስጢር ፣ እንዲፈጸም ፣ ተፈልጓል ፣’’ ሲባል ፣ በወይዘሮ ፣ መና ፣ እናት ፣ የተነገረውን ፣ ቃል ፣ ፫ኛ ፣ ፬ኛ ፣ ፭ኛ ፣ የተቃዋሚ ፣ ምስክሮች ፣ ማደጎው ፣ በይፋ ፣ እንደ ፣ ተነገረ ፣ አድርገው ፣ ስለ ፣ መሰክሩ ፣ የወይዘሮ ፣ ሥርጕትን ፣ ቃል ፣ ሽረዋል ። የተቃዋሚዋ ፣ ወላጅ ፣ እናት ፣ ከኾኑት ፣ ምስክርና ፣ በጉዳዩ ፣ ይበልጥ ፣ ያሉበት ፣ ከኾኑት ፣ ምስክር ፣ ቃል ፣ ይልቅ ፣ የውጭ ፣ ሰምችና ፣ በጉዳዩ ፣ ማለት ፣ በክርስትናውም ፣ ኾነ ፣ በማደጎው ፣ እንደ ፣ ወይዘሮ ፣ መና ፣ እናት ፣ የሌሉበት ፣ ሰዎች ፣ ቃል ፣ የተሻለ ፣ ዋጋ ፣ ይሰጠዋል ፣ ለማለት ፣ የሚያስችል ፣ ነገር ፣ የለም ። ስለዚህ ፣ ወይዘሮ ፣ ሥርጕተ ፣ የማደጎው ፣ ልጅነት ፣ በምስጢር ፣ ነው ፣ ያሉትን ፣ ተቀብለናል ።

በተቃዋሚ ፣ ምስክሮች ፣ ቃል ፣ ‘‘ወይዘሮ ፣ መናን ፣ ልጅ ፣ ያደረጉ ፣ ወይዘሮ ፣ በቀለችና ፣ ባለቤታቸው ፣ ናቸው ፣’’ ሲባል ፣ ተገልጿል ። ይህም ፣ ማለት ፣ ወይዘሮ ፣ በቀለችና ፣ ባለቤታቸው ፣ ወይዘሮ ፣ መናን ፣ በምስጢር ፣ የማደጎ ፣ ልጅ ፣ አድርገዋል ፣ ማለት ፣ ይኾናል ።

በአገራችን ፣ ልማድ ፣ በሥጋ ፣ ያልተወለደውን ፣ ሰው ፣ በሥጋ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ ዐይነት ፣ ለማድረግና ፣ በሥጋ ፣ የተወለደ ፣ ቢኾን ፣ ኖሮ ፣ ሊያገኘ ፣ ይችል ፣ የነበረውን ፣ የቤተ ፣ ሰብነት ፣ መብትና ፣ ግዴታ ፣ የመውረስንም ፣ መብት ፣ እንዲያገኝ ፣ ለማድረግ ፣ በልዩ ፣ ሥርዐት ፣ ልጅ ፣ ይደረጋል ። ሥርዐቱ ፣ ተፈጽሞ ፣ ልጅ ፣ ነው ፣ ሲባል ፣ በሥጋ ፣ ከተወለደ ፣ ልጅ ፣ በመብት ፣ ግዴታው ፣ አይለይም ።

ባዕድ ፣ የኾነውን ፣ ሰው ፣ በሥጋ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ ዐይነት ፣ የሚያደርገው ፣ ኹነታ ፣ አብዛኛውን ፣ በጋሎች ፣ ዘንድ ፣ ይገኛል ፤ መጠሪያ ፣ ስሙም ፣ ‘‘ጉዲፈቻ’’ ነው ። በዐማራውም ፣ ሥርዐት ፣ ‘‘የማር ፣ ልጅ ፣’’ ወይም ፣ ‘‘የጡት ፣ ልጅ ፣’’ የሚባል ፣ ነገር ፣ አለ ፤ የሚያስከትለው ፣ ውጤት ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ጉዲፈቻ ፣ ላይኾን ፣ ይችላል ። የጉዲፈቻ ፣ ልጅ ፣ የሚባለው ፣ በሥጋ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ የሚታሰበው ፣ ነው ። የማር ፣ ልጅ ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ በሥጋ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ አይታይም ። የማር ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ በሥጋ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ ዐይነት ፣ በሕግ ፣ እንዲታይ ፣ ያስፈለገ ፣ እንደኾነ ፣ ይህንኑ ፣ የሚያሳይ ፣ ግልጥ ፣ የኾነና ፣ ጥርጣሬን ፣ የማያሳድር ፣ ሥርዐት ፣ እንዲፈጸም ፣ ይገባል ።

ባዕድ ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ይጠየቅ ፡ የነበረው ፡ ሥርዐት ፡ ልጅ ፡ እንዲኾን ፡ የሚፈለገው ፡ ሰው ፡ በዕርግጥ ፡ ልጅ ፡ እንዲኾን ፡ መፈቀዱ ንና ፡ መፈለጉን ፡ የሚያመለክተውን ፡ ማንኛውንም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ነገር ፡ መፈጸም ፡ ነው ። ይህን ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ ተፈላጊ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉትን ፡ ደን ቦች ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ዘርዝሮ ፡ ስለማይገኝ ፤ ብየጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ልጅ ፡ ተደረገ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ ልጅ ፡ ተደርጓል ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ይታያል ። በጠቅላላው ፡ ሲመረመር ፡ አንድ ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ ጕልቶ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ አፈጻጸሙ ፡ የተለያየ ፡ ዅኖ ፡ ቢገኝም ፡ የወላጅና ፡ የተወላጅን ፡ መተ ሳሰር ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚችል ፡ ሥርዐት ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያስፈልግ ፡ መኹኑን ፡ የሚደ ነግግ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሥርዐት ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ዐይነት ፡ በሕግ ፡ የሚታየውን ፡ ልጅ ፡ ከሌላው ፡ በሕግ ፡ ሳይኾን ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ልጅ ፡ ከሚባለው ፡ ሰው ፡ ይለየዋል ።

የወላጅና ፡ የተወላጅ ፡ ዐይነት ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ ከኹሉ ፡ አስ ቀድሞ ፡ ጕዳዩ ፡ በምስጢር ፡ ሳይኾን ፡ በይፋ ፡ መፈጸም ፡ ይገባዋል ። ልጅ ፡ የሚደረገው ፡ ሰው ፡ በሥጋ ፡ የወለዱትንና ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶቹን ፡ ትቶ ፡ በሥጋ ፡ ወደ ፡ አልወለዱት ፡ የሚዛመድ ፡ ስለሚኾን ፡ የዱሮው ፡ ዘመዶቹም ፡ ኹኑ ፡ ዐዲሱ ፡ ዘመዶቹ ፡ ነገሩን ፡ እንዲ ያውቁት ፡ ያስፈልጋል ። ዝምድና ፡ በተለይ ፡ ሰዎች ፡ በውል ፡ መልክ ፡ በሚፈጥሩት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ዘንድ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ ነውና ፡ ምስጢር ፡ የሚኾንበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ የፈለገ ፡ ሰው ፡ ነገሩን ፡ በሥውር ፡ ለመፈጸም ፡ ከተነሣ ፡ ምሉ ፡ ፍላጎት ፡ አለው ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። በግልጥ ፡ የሚፈጸም ፡ ነገር ፡ ለመቃወም ፡ የሚፈልገውን ፡ ሰው ፡ ዕድል ፡ ይሰጠዋል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሥጋ ፡ ያልወለደ ውን ፡ ልጅ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በጉዲፈቻ ፡ ሊሰጥ ፡ ቢፈልግና ፡ ነገሩ ፡ በምስጢር ፡ ቢፈጸም ፡ ልጁን ፡ በሥጋ ፡ የወለዱት ፡ ሰዎች ፡ ጕዳዩን ፡ ስለሚያውቁት ፡ ሊቃወሙ ፡ አይችሉም ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዲፈቻ ፡ ተፈጽሟል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶቹን ፡ ትቶ ፡ ዐዲስ ፡ ዘመዶችን ፡ ያፈራል ። ይህንን ፡ ዅነታ ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶቹም ፡ ኾኑ ፡ ዐዲሶቹ ፡ ዘመዶቹ ፡ እንዲያውቁት ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ልጅ ፡ የማድረግ ፡ ሥርዐት ፡ በዝርዝር ፡ ባይገኝ ፡ ሥርዐቱ ፡ በግልጥ ፡ መፈጸም ፡ ይገባ ዋል ፡ የሚባለው ፡ ደንብ ፡ የታወቀ ፡ የተለመደና ፡ የተፈቀደ ፡ ይመስለናል ። ልጅ ፡ የሚ ደረግ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ለሚያደርገው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ለባዕ ድም ፡ ጭምር ፡ ልጅ ፡ የሚያደርገው ፡ ሰው ፡ (ለጉዲፈቻ ፡ ወላጁ ፡) ልጅ ፡ መኾኑ ፡ መታ ወቅ ፡ ይገባዋል ። አልበለዚያ ፡ ለሕግና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የሥርዐቱ ፡ ዐላማ ፡ ባለዋጋ ነት ፡ ሊታይ ፡ አይቻልም ።

የወላጅና ፡ የተወላጅ ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰርን ፡ የሚያስገኘው ፡ ሥርዐት ፡ ሳይሠወር ፡ በግልጥ ፡ ተመርቶ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በዕርግጥ ፡ የተባለው ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ ተገ ኝቶ ፡ እንደኾነ ፡ ከተፈጸመው ፡ ሥርዐት ፡ ሊታወቅ ፡ ይችላል ። የሚያስተሳስረው ፡ ልዩ ፡ ሥርዐት ፡ በየባህሉ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በማናቸውም ፡ ጠባይ ፡ ቢኾን ፡ በጉዲፈቻ ፡ ወላጅ ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡ ለመውለድ ፡ መፍቀዱንና ፡ መፈለጉን ፡ ዋርጣሬ ፡ በሌለው ፡ መንገድ ፡ የሚያሳይ ፡ ልዩ ፡ ሥርዐት ፡ መኾን ፡ ይገባዋል ። የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ የሚደረ ገውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በዕድሜው ፡ ትንሽ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ የሥጋ ፡ ወላጁ ፡ መፍቀዱ ንና ፡ መፈለጉን ፡ የሚያሳይ ፡ ሥርዐት ፡ መኾን ፡ ይገባዋል ። አልበለዚያ ፡ በዕርግጥ ፡ የሚፈለገው ፡ ዐይነት ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ እንዲገኝ ፡ መፈቀዱና ፡ መፈለጉ ፡ ሊታወቅ ፡ አይችልም ።

በአንዱ ፡ ባህል ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈለገው ፡ ሰው ፡ ድግስ ፡ ደግሶ ፡ ሰው ፡ ጋብዞ ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ መፈለጉን ፡ ሲገልጥ ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ ተፈጽሟል ፡ ይባ ላል ። በሌላው ፡ ባህል ፡ ልጅ ፡ የሚያደርገው ፡ ልጅ ፡ የሚደረገው ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ልጅ ፡

ሊያየው ፣ ከሥጋ ፣ ልጁ ፣ ሳይለየው ፣ በቁስ ፣ ፊት ፣ ምሎ ፣ ሲገዘት ፣ ሕጋዊ ፣ መተሳ ሰሩ ፣ ተፈጽሟል ፣ ይባላል ። ሌሎች ፣ ባህሎችም ፣ ሕጋዊ ፣ መተሳሰርን ፣ የሚያስገኙ ፣ ሥርዐቶች ፣ ሳይኖሯቸው ፣ አይቀርም ።

የጉዲፈቻ ፣ ዐይነት ፣ ልጅነት ፣ አለ ፣ ሕጋዊ ፣ ውጤቱ ፣ ግን ፣ የተለየ ፣ ነው ። እንዳ ንዴ ፣ ሰዎች ፣ የክርስትና ፣ ልጃቸውን ፣ ልጁ ፣ እያሉ ፣ ያሳድጋሉ ። ይህ ፣ ዅነታ ፣ ግን ፣ የክርስትና ፣ ልጅ ፣ የተባለውን ፣ በሥጋ ፣ የተወለደ ፣ ልጅ ፣ ወይም ፣ የጉዲፈቻ ፣ ልጅ ፣ አያደርገውም ፤ የውርስ ፣ መብትም ፣ አያስገኝለትም ። የክርስትና ፣ አባት ፣ የዅነው ፣ ሰው ፣ ኑዛዜ ፣ ትቶ ፣ እንደሞነ ፣ ለክርስትና ፣ ልጅ ፣ ስጦታ ፣ ሊያደርግለት ፣ ይችላል ፤ ግዴታ ፣ ግን ፣ የለበትም ። የክርስትና ፣ አባት ፣ የዅነው ፣ ሰው ፣ ሳይናዘዝ ፣ ቢሞት ፣ የክር ስትና ፣ ልጅ ፣ ወራሽ ፣ ነኝ ፣ ብሎ ፣ ሊጠይቅ ፣ አይችልም ። ይህ ፣ ቢዅን ፣ ኖሮ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ክርስትና ፣ ማንሣቱን ፣ ይተዉ ፣ ነበር ።

የማር ፣ ልጅ ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ የሚባለውም ፣ ማር ፣ ከሚያልሰውና ፣ ጡት ፣ ከሚያጠባው ፣ ሰው ፣ ጋራ ፣ ቀረብ ፣ ያለ ፣ ግንኙነት ፣ እንዲያደርግ ፣ የተሻለ ፣ አስተያየት ፣ እንዲያርፍበት ፣ የቤተ ፣ ሰብነት ፣ ስሜት ፣ ዐድሮበት ፣ በደስታም ፣ ዅነ ፣ በመከራ ፣ እንደ ፣ ዘመድ ፣ እንዲዅን ፣ የሚያደርግ ፣ ዅነታ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የሕግ ፣ ልጅነትን ፣ የሚ ያስከትል ፣ አይደለም ። የማር ፣ ልጅ ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ በኑዛዜ ፣ ስጦታ ፣ ወይም ፣ ውርስ ፣ ሊያገኝ ፣ ይችላል ፣ ተናዛዥ ፣ ግን ፣ ግዴታ ፣ የለበትም ። የማር ፣ አባት ፣ (ወይም ፣ እናት) ፣ የጡት ፣ አባት ፣ (ወይም ፣ እናት ፣) ካለ ፣ ኑዛዜ ፣ ቢሞቱ ፣ የማር ፣ ልጅ ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ ወራሽ ፣ ነኝ ፣ ብሎ ፣ ሊቀርብ ፣ አይችልም ። ይህ ፣ መዅኑ ፣ ቢታወቅ ፣ ዐያሌ ፣ ሰዎች ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ የማር ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ ዅነታን ፣ ከማስገ ኘት ፣ ራሳቸውን ፣ ያግዱ ፣ ነበር ። ሰዎችም ፣ ዘመዶቻቸውን ፣ ልጂ ፣ እያሉ ፣ ማሳደጋቸ ውን ፣ ይተዉ ፣ ነበር ።

የክርስትና ፣ አባት ፣ (ወይም ፣ እናት) ፣ የማር ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ አባት ፣ (ወይም ፣ እናት) ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ተነገረው ፣ በግልጥ ፣ (በይፋ) ፣ ሕጋዊ ፣ መተሳሰርን ፣ የሚ ያስገኘውን ፣ ልዩ ፣ ሥርዐት ፣ በመፈጸም ፣ የክርስትና ፣ የማር ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጃቸ ውን ፣ የማደጎ ፣ ወይም ፣ የጉዲፈቻ ፣ ልጅ ፣ ሊያደርጉ ፣ ይችላሉ ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ አስፈላ ጊው ፣ ሥርዐት ፣ ተፈጽሟልና ፣ የክርስትና ፣ ዅነ ፣ የማር ፣ ወይም ፣ የጡት ፣ ልጅ ፣ በሕግ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ ተቈጥሮ ፣ የልጅነትን ፣ መብት ፣ ለማግኘት ፣ ይችላል ።

ከዚህ ፣ በላይ ፣ የዘረዘርናቸውን ፣ ጠቅላላ ፣ መግለጫዎች ፣ ከዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ጋራ ፣ በማዛመድ ፣ እንቀጥላለን ።

ወይዘሮ ፣ መና ፣ የክርስትና ፣ ልጅ ፣ መዅናቸው ፣ ተረጋግጧል ። ወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ ዘንድ ፣ ማደጋቸውም ፣ ታውቋል ። ወይዘሮ ፣ በቀለች ፣ የወይዘሮ ፣ መና ፣ አክስት ፣ ናቸው። የማደጎ ፣ ልጅ ፣ ናቸው ፣ የሚያሰኝ ፣ ሥርዐት ፣ ግን ፣ ተፈጽሞ ፣ አላገኘንም ። ማደጎ ፣ ተፈ ጽሟል ፣ ቢባልም ፣ ይህን ፣ የሚያመለክት ፣ ጥሩ ፣ ማስረጃ ፣ የለም ፣ እንጂ ፣ በምስጢር ፣ ዅኗል ፣ የተባለው ፣ ብቻ ፣ ዋጋ ፣ ሊያሳጣው ፣ ይችል ፣ ነበር ። ሕጋዊ ፣ መተሳሰርን ፣ ሊያ ስገኝ ፣ የሚችለው ፣ ሥርዐት ፣ ተፈጽሞ ፣ አልተገኘም ። በአገር ፣ ልማድ ፣ መሠረት ፣ ወይ ዘሮ ፣ በቀለች ፣ ‘‘ወይዘሮ ፣ መናን ፣ ልጂ ፣ አደርጋለኹ ፣ በሥጋ ፣ ልጅ ፣ ዐይን ፣ እመለ ከታለኹ ፣’’ ብለው ፣ ወይም ፣ ይህን ፣ መሰል ፣ ጥርጣሬን ፣ የማያስገባ ፣ ነገረ ፣ ቱናግረው ፣ በመሐላና ፣ በግዝት ፣ አጽድቀውት ፣ አልተገኙም ። የክርስትና ፣ ድግስ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ከ ድግሱ ፣ በኋላ ፣ ቁስ ፣ ‘‘ስብሐት’’ ፣ ቢል ፣ ማንኛውም ፣ ማእድ ፣ ላይ ፣ የሚፈጸም ፣ ነገር ፣ ነውና ፣ ልዩ ፣ ሥርዐትን ፣ አያመለክትም ። ወይዘሮ ፣ በቀለችም ፣ የክርስትና ፣ ልጃቸ ውን ፣ ማሳደጋቸው ፣ የሕግ ፣ ልጅ ፣ አደረጓቸው ፣ የሚያሰኝ ፣ አይደለም ።

እኛ ፡ እንደሚመስለን ፡ ወይዘሮ ፡ በቀለች ፡ ወይዘሮ ፡ መናን ፡ ክርስትና ፡ ማንሣታ ቸውና ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ማኖራቸው ፡ የተቃዋሚዋን ፡ ምስክሮች ፡ ሳያሳስት ፡ አል ቀረም ።

ወይዘሮ ፡ መናን ፡ ወይዘሮ ፡ በቀለችና ፡ ባለቤታቸው ፡ ልጅ ፡ አደረጉ ፡ ሲባል ፡ ወይዘሮ ፡ መና ፡ የወይዘሮ ፡ በቀለችን ፡ ባለቤት ፡ ስም ፡ ለምን ፡ እንዳልያዙ ፡ አልገባንም ።

ጸሐፊው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የኢትዮጵያዊውን ፡ የተወላጅነትና ፡ የምህላው ፡ (ዶሚሳይል) ሕግ ፡ እና ፡ የግል ፡ አቋም ፡ ጉዳይን ፡ ለመቍረጥ ፡ (ለመወሰን) ፡ የሚያገለግለውን ፡ ሕግ ፡ ለመመራመር ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ። ምንጊዜም ፡ ቢኾን ፡ የውጭ ፡ አገሩ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ደኅና-ኀብ ፡ (-መጥ ፡) ነው ። ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለረዥም ፡ ዘመናት ፡ ከዚሁ ፡ ይኖራሉ ፡ ይሠራሉ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ (ተወላጅ) ፡ አይኾኑም ። እነሆ ፡ እንግዲህ ፡ ቍጥሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ያለባት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ ጣጣዎች ፡ ማለት ፡ ምህላዉን ፡ ከዚህ ፡ ያደረገው ፡ ማን ፡ ነው ፡ በሚያሰኙ ፡ ችግሮች ፡ እና ፡ የትኛውስ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ የግል ፡ ነጠላ ፡ ሰዎችን ፡ አቋምንና ፡ ግንኙነቶችን ፡ የሚዳኝ ፡ በሚያሰኙ ፡ ምርምሮች ፡ ተወጥራ ፡ ተይዛለች ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ያሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነትን ፡ የሚመለከቱ ፡ የሕግ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለማቅረብ ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ልዩነቶችን ፡ ለመፈተሽ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በደንበኛ ፡ ሰዎች ፡ ምህላው ፡ ላይ ፡ የተዘረጉ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለማብላላት ፡ እና ፡ ስለ ፡ ዳኟው ፡ (ገዢው ፡) የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ ጣጣዎች ፡ ለማውጣትና ፡ ለማውረድ ፡ ወቅዳለኹ ።

ተወላጅነት ።

ኢትዮጵያዊ ፡ ተወላጅነትን ፡ ስለማግኘትና ፡ ስለማጣት ፡

በተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፭ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነትንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን ፡ ለማግኘትና ፡ ለማጣት ፡ የሚያስችሉ ፡ ኹኔታዎችን ፡ ሕጉ ፡ ይቀምራል ፡ (ይወስናል)[1] " ሲል ፡ ይናገራል ። በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እስካኹን ፡ ድረስ ፡ ባለ ፡ ውጤት ፡ የኾነው ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የ፲፱፻፴ ፡ ዓ . ም . የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡[2] ነው ። የ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ . ም . የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ ምንባር ፡

---

[1] ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም. ሕገ-መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ይኸው ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ዐርፎበት ፡ ይገኛል ።
[2] የጁላይ ፡ (ሐምሌ) ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. ሕግ ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ የምንገለገልበት ፡ ቢሉላ ፡ አኳኋን ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ግሬጎሪያዊውን ፡ (አውሮጳዊውን) የዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ነው ።

በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ውሳኔዎችን ፡ የያዘ ፡ ቢኾንም ፡ ተወላጅነትን ፡ ስለማግኘት ፡ ወይም ፡ ስለማጣት ፡ ነክ ፡ ስለኾነው ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የያዘው ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደሌሉ ፡ ልብ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ።

ተወላጅነትንና፡ ዜግነትን ፡[3] ለመለየት ፡ ዅለት ፡ መሠረታዊ ፡ አቀራረቦች ፡ አሉ ፤ እነዚሁም ፡ የዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ (በደም ፡ ዜግነት) እና ፡ የዩስ ፡ ሶሊ ፡ (በውልደት ፡ ዜግነት) ናቸው ። በዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ (በደም ፡ ዜግነት) ልም ፡ ወይም ፡ መሠረተ-ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ የትም ፡ ስፍራ ፡ ቢኾን ፡ ይወለድ ፡ የወላጆቹን ፡ ዜግነት ፡ (የወላጆቹ ፡ ተወላጅነት ፡ ሲለያይ ፡ ይበልጥ ፡ የተለመደው ፡ ያባትን ፡ ዜግነት ፡ ነው) ይቀበላል ። ለምሳሌ ፡ ያቹል ፡ ጀርመን ፡ ወላጅነትን ፡ እንደ ፡ ቄራጭ-ፈላጭ ፡ (ደም ዳሚ) ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ይቀበለዋል ፤ በጀርመን ፡ ይኹን ፡ ወይም ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡ ከጀርመን ፡ ወላጆች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ጀርመኖች ፡ ሲኾኑ ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ የተወለዱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ የጀርመን ፡ ዜግነት ፡ ሳይኾን ፡ የወላጆቻቸውን ፡ ዜግነት ፡ ይይዛሉ [4] ።

በዩስ ፡ ሶሊ ፡ (በውልደት ፡ ዜግነት) ዐይነተኛ ፡ ሐሳብ ፡ ወይም ፡ ልም ፡ መሠረት ፡ መላጆቹ ፡ የዚያው ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ይኹኑ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ የዚያው ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ይኾናሉ ፤ ይህን ፡ ሥርዐት ፡ ሲያ ገላብጡት ፡ ወይም ፡ ሲያዘዋውሩት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከተቀመጡ ፡ ያንድ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ የዚያች ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ አይደሉም ፡[5] ማለት ፡ ነው ። አርጀንቲና ፡ በተለይ ፡ ወሳኝና ፡ አውራ ፡ ምክንያቱ ፡[6] የተወለዱበት ፡ ግዛት ፡ ከሚኾንበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የተመደበች ፡ ነች ።

ብዙዎቹ ፡ አገሮች ፡ ከነዚህ ፡ አብዛኛውን ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዅለተኛው ፡ ጉልቶና ፡

---

3 ከነዚህ ፡ ዅለት ፡ ቃል ፡ አገባቦች ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ያነጋገር ፡ አገባብ ፡ ፍች ፡ "ተወላጅነትን" በበለጥ ፡ ሲጠቀሙበት ፡ "ዜግነት" የራስ ፡ (የግል) ወይም ፡ የቀበሌ ፡ ስፍራ ፡ ቃል ፡ አሰካክ ፡ ነው ። የቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ባሏቸው ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በዜጎችና ፡ በተወላጆች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ልዩነት ፡ ይደረጋል ። ለም ሳሌ ፡ በተባበረው ፡ (የአሜሪካ) መንግሥታት ፡ አሰኘታ ፡ (ግዛት) ውስጥ ፡ የተወለደው ፡ ሰው ፡ ዚጋ ፡ ከመ ባሉ ፡ ይልቅ ፡ ተወላጅ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። የተባበሩት ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ርእስ ፡ ፭ ፡ መደብ ፡ (ክፍል) ፭፪ሕ፬፬፭ ። ለኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ አገልግሎት ፡ በዜጎችና ፡ በተወላጆች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አያወጣም ። በጠቅላላው ፡ የሲልቢንግን ፡ ናቪናሊቲ ፡ ኢን ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡ (ዜግነት ፡ በተመጣጣኝ ፡ ሕግ) ፭፻፲ ፡ ፭፻፲፭ ፡ (፲፱፻፲፯) ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዘውድ ፡ ወይም ፡ የሡፋን ፡ መንግሥት ፡ አጽም ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ተወላጆች ፡ አንዳንዱ ፡ ተገዦች ፡ ይሰኛሉ ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ተገለገልንባቸው ፡ ግን ፡ "ተወላጅነት" እና ፡ "ዜግነት" አንድ ፡ ዐይነት ፡ ፍች ፡ አላቸው ።

4 ራይሽ ፡ እና ፡ ሀገር ፡ ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ የጀላይ ፡ ፩፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ . ም ፡ ንሌስ ፡ አንቀጽ ፡ ፮ ። (በምዕራብ ፡ ጀርመን) በፌዴራል ፡ ሬፑብሊኩ ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፲፭ ፡ መሠረት ፡ የጀርመን ፡ ተወላጅነት ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ከነገደ ፡ ጀርመን ፡ ተወልደው ፡ እስከ ፡ ዲሴምቤር ፡ (ታኅሣሥ) ፴፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ. ም. መቀበልን ፡ የተዋኟ ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፡ ጀርመኖች ፡ ናቸው ። በናዚ ፡ መንግሥት ፡ ዝማጅት ፡ ትእዛዞች ፡ የጀርመን ፡ ተወላጅነታቸውን ፡ ያጡ ፡ ሰዎች ፡ ሲጠይቁ ፡ ተወላጅነታቸው ፡ እንደገና ፡ ይሰጣቸ ዋል ። ሌላ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ ዘንዳ ፡ የፕ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ. ም. ሕግ ፡ የተወላጅነት ፡ መሠረታዊው ፡ ሕግ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ያንዷ ፡ ጀርመናዊት ፡ ከግእሰረ-ጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ጀርመናዊ ፡ እንደኾነ ፡ ዅሉ ፡ ያንድ ፡ ጀርመናዊ ፡ አባት ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅም ፡ ጀርመናዊ ፡ ነው ። በአፔንሐይም ፡ አንቱር ናሽናል ፡ ሎው ፡ (የኢንቱርናሽናል ፡ ሕግ ፡ ጅኖ ፡ እትም ፡ ላውቱርፓሽት) ፡ ቮሉም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፲፩ ፡ ያለውን ፡ ምርምር ፡ ይመለከቷል ።

5 ከዚያው ፡ ከአፔንሐይም ፡ መጽሐፍ ። ይህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ወኪሎች ፡ ልጆችን ፡ ከቶ ፡ የሚጨምር ፡ አይደለም ።

6 ከዚያው ፡ ከአፔንሐይም ፡ መጽሐፍ ።

ደምቆ ፡ የሚታይባቸው ፡ እድርገው ፡ [7] በተወላጅነት ፡ ሕጋቸው ፡ የኹለቱንም ፡ ልሞች ፡ ጠባዮች ፡ ያወቁዋቸውና ፡ የተቀበሏቸው ፡ ናቸው ። የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የዩስ ፡ ሶሲ ፡ አገር ፡ ነው ። የሕገ-መንግሥቱ ፡ ዐሥራራተኛው ፡ ማሻሻያ ፡ "በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱ ፡ ወይም ፡ ዜግነትን ፡ የተቀቡ ፡ (የዜጉ) ፡ እና ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣኑም ፡ ተገዥ ፡ የኾኑ ፡ ኹሉ ፡ የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ዜጎች ፡ ናቸው ፡" ሲል ፡ ያትታል ። ይህ ፡ ውሳኔ ፡ አኹን ፡ ገና ፡ ዐርነት ፡ (ነጻ) የወጡት ፡ ኔግሮዎችና ፡ ልጆቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ያሜሪካ ፡ዜጎች ፡ እንደሚኾኑ ፡ አረጋግጧል ። ደግሞም ፡ ባሥራዘጠኝኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ-ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ግድም ፡ በነበረው ፡ ወደ ፡ ተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ መግባት ፡ (ኢሚግሬሺን) ከፍ ፡ ባለው ፡ ማዕበል ፡ ጊዜ ፡ ከዐዲስ-ገብ ፡ ወይም ፡ ደረስ ፡ ወላጆች ፡ የተወለዱ ፡ ሕፃናችን ፡ ኹሉ ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጎች ፡ ስለእደረጋቸው ። [8] ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዋጋ ፡ ግሙቱን ፡ አረጋግጧል ። ባንዳንድ ፡ አኳኋኖች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ዜጎች ፡ ተብለው ፡ ይገመታሉ ። [9] ሕፃኑ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ቢወለድም ፡ ቅሉ ፡ ጥንዱ ፡ ወላጁቹ ፡ የአሜሪካን ፡ ዜጋዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ወይም ፡ ባለኀታዎቿ ፡ (በግዛቶቿ) ምቅማጥ ፡ (ኑዋሪነት) የነበረው ፡ እስከኾነ ፡ ድረስ ፡ ልጁ ፡ በውልዱ ፡ [10] የአሜሪካን ፡ ዜጋ ፡ ተብሎ ፡ ይቁጠራል ። ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ዜጋ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ (እንግዲያስ) ያው ፡ ወላጅ ፡ ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ [11] በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ወይም ፡ በይዞቶቿ ፡ (ባለኀታዎቿ) ውስጥ ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ተቀማጭ ፡ ኹኖ ፡ መገኘት ፡ ይገባዋል ። አንደኛው ፡ ወላጅ ፡ የአሜሪካን ፡ ዜጋ ፡ ሳለ ፡ ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ያልተቀመጠ ፡ ግን ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ወይም ፡ በይዞቶቿ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቶ ፡ እንደነበረ ወይም ፡ በወታደራዊ ፡ አገልግሎቶች ፡ ሲዳመሩ ፡ ፲ ፡ ዓመታት ፡ ለሚኾኑ ፡ ጊዜዎች ፡ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ ዐምስት ፡ ዓመታቱን ፡ በዕድሜው ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ ያገለገላቸው ፡ ከኾነ ፡ ካገር ፡ ውጭ ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ዜጋ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ በዕድሜው ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ከመምላቱና ፡ ከ፲፬ ፡ ዓመቱ ፡ በኋላ ፡ ቢያንስ ፡ ፭ ፡ ዓመታት ፡ ሳያቋርጥ ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ መቈየት ፡ ወይም ፡ ማሳለፍ ፡ አለበት ። እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ በጣም ፡ ወሳኞች ፡

---

7 ባ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ. ም. ጥናት ፡ መሠረት ፡ የቆመውን ፡ ወደ ፡ ተወላጅነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አቀራረቦች ፡ አዘራዘር ፡ ቢሾፕ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ (የኢንተርናሽናል ፡ ሕግ) ፳፻፲፭ (፱ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፷፰) ይመለከቷል ። የመዝመሪያው ፡ ዕይተኝኛ ፡ ጥናት፡ በ፷፱ ፡ አሜሪካን ፡ ጆርናል ፡ አቭ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ (የአሜሪካ ፡ ኢንቴርናሽናላዊ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት) ፱፻፵፰ ፡ ፱፻፶፯ ፡ (፲፱፻፴፭) ውስጥ ፡ ይገኛል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እንዳንድ ፡ ለውጦች ፡ ያለጥርጥር ፡ ቢደረግባቸው ፡ ቅሉ ፡ ስለልዩ ፡ ልዩ ፡ አቀራረቦች ፡ አመዳደባቸው ፡ ጥናቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብን ፡ ይሰጣል ።

8 ምንም ፡ እንኳ ፡ ወላጆቹ ፡ የቅላት ፡ ዜግነትን ፡ ለማግኘት ፡ የበቁ ፡ ባይኖሩም ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት፡ እና፡ በምንም፡ ኪም፡ አርክ፡ ፭፻፷፱ ፡ ፪. ኤስ. ፻፸፱ ፡ (፲፰፻፺፰) ፡ በነበረው ፡ ነገር፡ ጠቅላይ፡ ፍርድ፡ቤቱ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ከቻይና ፡ ወላጆች ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት፡ ዜጋ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በየነ ። በዩስ ፡ ሶሲ ፡ አቀራረብ ፡ መሠረት ፡ ልጁ ፡ የተወለደበት ፡ አገር ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተገዥ ፡ እስከኾኑ ፡ ድረስ ፡ ማለት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሹማምት ፡ እስካልኾኑ ፡ የወላጆቹ ፡ አቋም ፡ ወይም ፡ ዜኑታ ፡ ለጉዳዩ ፡ አያስፈልግም ፡ (ትርፍ ፡ ጉዳይ ፡ ነው) ።

9 ይህ ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ሕጉ ፡ ርእስ ፡ ፭ ፡ መደብ ፡ ፭ሺሕ፪፻፭ ፡ ቍልጭ ፡ ብሎ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

10 ፡ጉሬዚዴንት ፡ ለመኾን ፡ የሚበቁት ፡ በውልደታቸው ፡ የአሜሪካን ፡ ዜጎች ፡ የኾኑት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

11 የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ (ኮድ) ፡ ርእስ ፡ ፭ ፡ መደብ ፡ ፭ሺሕ፪፻፭ (፭) ይመለከቷል ።

(ጨባሮች፥) መኾናቸው ፣ ግልጥ ፣ (ጉልሕ) ሲኾን ፣ በተባበረው ፣ (አ.) መንግሥታት ፣ ለዜግነት ፣ ተቀዳሚ ፣ መሠረት ፣ ከዚያው ፣ መወለዱ ፣ ነው ።

ፈረንሳይ ፣ በመዠመሪያ ፣ የዩስ ፣ ሳንጉይኒስ ፣ ልምን ፣ በጣም ፣ አጥብቃ ፣ ተከትላ ፣ ነበረ ። በፈረንሳይ ፣ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፣ እንቀጽ ፣ ፲ ፣ መሠረት ፣ "በባዕድ ፡ አገር ፣ ከአንድ ፡ ፈረንሳይ ፡ የተወለደው ፡ ማናቸውም ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳይ ፡ ነበረ ።" ምንም ፡ እንኳ ፡ በሕጉ ፡ (ኮዱ) እንቀጽ ፡ ፱ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ከአንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ ነፍስ ፡ ሲያውቅ ፡ ወይም ፡ አከልነቱን ፡ (በቅመ-አዳም) ሲያደርስ ፡ የፈረንሳይ ፡ ዜግነት ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይች ላል ፡ ቢባልም ፡ ቅሉ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከማናቸውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የተወለደው ፡ ማናቸውም ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳይ ፡ አይኾንም ፡ ነበረ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የተወላጅ ነት ፡ ሕጎች ፡ በተሠሩ ፡ ቍጥር ፡ የፈረንሳዩ ፡ አቀራረብ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ይወጣና ፡ ይወርድ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ የፈረንሳይ ፡ ዜጎችን ፡ ቍጥር ፡ ለማዳበር ፡ ሲል ፡ የ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም. የፈረንሳይ ፡ ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ ዅሉቱንም ፡ ልምች ፡ ደንና ፡ አድርጎ ፡ አስፋፍቶና ፡ ዘርግቶ ፡ አስቲበቃው ፡ ካገልግሎት ፡ አውሏቸዋል ። መንግሥት ፡ የተቻለ ውን ፡ ያኽል ፡ የዜጎቹን ፡ ቍጥር ፡ ለማሳደግ ፡ የሚያደርገውን ፡ ድካምና ፡ ጥረት ፡ ቍልጭ አድርገው ፡ ስለሚያሳዩ ፡ ውሳኔዎቹ ፡ አስተውሎን ፡ የሚጠይቁ ፡ ናቸው ።

በአናቅጽ ፡ ፲፮ ፡ እና ፡ ፲፰ ፡ የትም ፡ ከቶ ፡ ቢወለድ ፡ ከፈረንሳይ ፡ አባት ፡ የተወለ ደው ፡ ደንበኛ ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳይ ፡ እንደኾነ ፡ ያባቱ ፡ ተወላጅነት ፡ ያልታወቀው ፡ ከማንኛዋም ፡ ፈረንሳዊት ፡ የተወለደ ፡ ደንበኛ ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳይ ፡ ነው ። እንደ ተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ልምድ ፡ ሳይኾን ፡ በወላጆች ፡ ላይ ፡ የተጫነው ፡ የመቀ መጥ ፡ (መኖር) ግዴታዎች ፡ የሉባቸውም ። በፍርድ ፡ ባንድ ፡ ፈረንሳይ ፡ ወላጅ ፡ ላይ ፡ ልጅነቱን ፡ [12] እንዱ ፡ ልጅ ፡ ሲያረጋግጥ ፡ (ሲረታ) ፡ ያረጋገጠው ፡ ባባትም ፡ ላይ ፡ ኾነ ፡ በናት ፡ ላይ ፡ ያ ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ አንዱ ፡ ወላጅ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ኹኖና ፡ የመዠመሪያው ፡ ከስ ፡ የቀረበበት ፡ ወላጅ ፡ ተወላጅነት ፡ ያልታወቀ ፡ እንደ ኾነ ፡ በፈረንሳዊው ፡ ወላጅ ፡ ላይ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ በሚገባ ፡ ልጅነቱን ፡ ከረታ ፡ ልጁ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ይኾናል ፡ ማለት ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ ለመገልበጥ ፡ (ለመሻር) ቢፈቀድም ፡ ያንዲት ፡ ፈረንሳዊት ፡ እናትና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አባት ፡ ደንበኛ ፡ ሕጋዊ ፡ (ከማእሰረ-ጋብቻ ፡ የተወለደ) ልጅ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሲኾን ፡ የባሕርይ ፡ (ዲቃላ) ልጅነቱን ፡ ከኹለት ፡ ወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ፈረንሳዊ ፡ መኾን ፡ የታወቀለት ፡ ወይም ፡ ልጅነቱን ፡ በፍርድ ፡ የረ ታው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ነው ። የተወለዱበት ፡ አገር ፡ ለጉዳዩ ፡ አስፈላጊ ፡ ስላልኾነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የሰፈሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ በግዴታ ፡ በዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸው ።

ደግሞም ፡ የፈረንሳዊው ፡ ሕግ ፡ የዩስ ፡ ሶሊ ፡ [13] ብዙ ፡ ጠባዮችን ፡ የያዘ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በግድ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ዜጋ ፡ ባይኾን ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ከተወለደ ፡ አባት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ነው ። ልጅነቱን ፡ በመዠመሪያ ፡ ካረ ጋገጠበት ፡ ወላጅ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የተወለደ ፡ በኾነ ፡ ጊዜም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ከተወለደችው ፡ እናት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የተወለደው ፡ ደን በኛ ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅ ፡ (እኹንም ፡ የመግልበጥ ፡ መብቱ ፡ እንደተጠበቀለት ፡ ነው) ፡ ፈረን

---

12 ልጅነት ፡ ዘርጋ ፡ ባለው ፡ በሰፈው ፡ አስተውሎ ፡ ያንድ ፡ ልጅ ፡ ወላጅ ፡ መኾን ፡ የሚረጋገጥበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ይመለከቷል ። ደግሞም ፡ የዚህ፡ የነገር ፡ አሰካክ ፡ ልጅነቱ ፡ በፍርዳዊ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይጸናለት ፡ ዘንድ ፡ ልጁ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ከስ ፡ ሊመራ መር ፡ ወይም ፡ ሊነካ ፡ ይችላል ።

13 በተለይም ፡ ያ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም. የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅነት ፡ ሕግን ፡ አናቅጽ ፡ ፭፫ ፡ ፭፮ ፡ ፶፱ ፡ እና ፡ ፶፪ ፡ ይመለከቷል ።

ሳዊ ፣ ሲኹን ፣ ልጅነቱን ፣ ለኹለተኛ ፣ ጊዜ ፣ ካረጋገጠበት ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ከተወለደ ፣ ወላጅ ፣ የተወለደው ፣ ልጅም ፣ ቅሉ ፣ እንደዚያው ፣ ነው ። በአንቀጽ ፣ ፭፩ ፣ መሠረት ፣ ተወላጅነታቸው ፣ ካልታወቀ ፣ ወላጆች ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ የተወለደ ፣ ልጅ ፣ ተወላጅ ፣ ዝምድናው ፣ ካልተገኘና ፣ ያባቱን ፣ ዜግነት ፣ ካልተቀበለ ፣ በቀር ፣ ፈረንሳዊ ፣ ነው ።

ኹለቱም ፣ ፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ካልተወለዱ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ወላጆች ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ሲወለድ ፣ አኪልኑቱን ፣ በሚያደርስበት ፣ ጊዜ ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ የሚቀመጥ ፣ እና ፣ በዕድሜው ፣ ከ፲፯ ፣ ዓመቱ ፣ [14] ዝምሮ ፣ ከዚያው ፣ ሲኖር ፣ የነበረ ፣ ከኾነ ፣ ልጁ ፣ ፈረንሳዊ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ። ባንዳንድ ፣ አኳኋኖች ፣ የተነሣ ፣ የፈረንሳይ ፣ ተወላጅነቱን ፣ ከመቀበል ፣ ለመተው ፣ ይችል ፣ ይኾናል ፣ ባንዳንድ ፣ አኳኋኖች ፣ የተነሣም ፣ ማመልከቻ ፣ ጥያቄውን ፣ መንግሥቱ ፣ ሊቃወም ፣ ይችል ፣ ይኾናል ። በዲሴምበር ፣ (ታኅሣሥ) ፭፪ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፷፭ ፣ ዓ. ም. በወጣው ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ወታደራዊ ፣ አገልግሎት ፣ ለዐምስቱ ፣ ዓመታት ፣ መቀመጥ ፣ (መኖር) ሊተካ ፣ ይችላል ። ደግሞም ፣ እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ልጅ ፣ ወቅመ-አዳም ፣ ከመድረሱ ፣ በፊት ፣ ለዐምስት ፣ ዓመታት ፣ ተቀምጦ ፣ እንደኾነ ፣ የፈረንሳይ ፣ ተወላጅነት ፣ ይገባኛል ፣ ብሎ ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ። ዕድሜው ፣ ከ፲፰ ፣ ዓመት ፣ በታች ፣ የኾነ ፣ እንደኾነ ፣ የይገባኛል ፣ ጥያቄው ፣ በጠባቂው ፣ (አሳዳጊው) ሊቀርብ ፣ ይችላል ። በዚያው ፣ ባይወለዱም ፣ ቅሉ ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ያደጉ ፣ ልጆችን ፣ የሚመለከቱ ፣ ልዩ ፣ ውሳኔዎች ፣ አሉ ፤ እነሱም ፣ ካንዳንድ ፣ አኳኋኖች ፣ የተነሣ ፣ የፈረንሳይ ፣ ተወላጅነትን ፣ [15] ለማግኘት ፣ ይችላሉ ። ፈረንሳይ ፣ የዩስ ፣ ሳንጉይኒስ ፣ መሠረታዊ ፣ ልምን ፣ ይዛ ፣ ሳለች ፣ የፈረንሳይ ፣ ዜጎችን ፣ ቍጥር ፣ ለማሳደግ ፣ ስትል ፣ ብዙ ፣ የዩስ ፣ ሶሊ ፣ ጠባዮችን ፣ መቀበሏ ፣ ጕልሕ ፣ ነው ።

አንዳንድ ፣ አገሮች ፣ በዩስ ፣ ሶሊ ፣ ሌሎችም ፣ በዩስ ፣ ሳንጉይኒስ ፣ ብዙዎቹም ፣ ከኹለቱም ፣ በተዋሐደ ፣ ልም ፣ ስለሚገለገሉ ፣ እንዳንድ ፣ ነጠላ ፣ ሰዎች ፣ ዋንድ ፣ ተወላጅነትን ፣ እንደያዙ ፣ መወሰዳቸው ፣ እንግዳ ፣ አይኾንም ፣ (አይደለም) ። ለምሳሌ ፣ ያኸል ፣ የጀርመን ፣ ዜግነታቸውን ፣ ካላወረዱ ፣ ከጀርመን-መጦች ፣ (-ገቦች ፣ ወይም ፣ ኢሚግራንትስ) ፣ በተባበረው ፣ (አ.) መንግሥታት ፣ የተወለደ ፣ ልጅ ፣ በተባበረው ፣ (አ.) መንግሥታት ፣ አሜሪካዊ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ይገመታል ፤ በጀርመን ፣ (መንግሥት) ደግሞ ፣ ጀርመናዊ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ። ደግሞም ፣ እንዲት ፣ ሴት ፣ በማግባቷ ፣ በሱ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የባሏን ፣ ተወላጅነት ፣ የተቀበለች ፣ እንደኾነና ፣ በሏ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የራሷን ፣ ተወላጅነት ፣ ያላጣች ፣ እንደኾነ ፣ የጥንድ ፣ ተወላጅነት ፣ ጕዳይ ፣ ሊነሣ ፣ ይችላል ። በአንዳንድ ፣ አገሮች ፣ አንዱ ፣ ተወላጅ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ተወላጅነት ፣ ሲቀበል ፣ ተወላጅነቱን ፣ (የፊተኛውን) እንዲያጣ ፣ ያደርጋሉ ፤ ሌሎችም ፣ የመዠመሪያውን ተወላጅነታቸውን ፣ ሳያጡ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ተወላጅነትን ፣ እንዲይዙ ፣ ለተወላጆቻቸው ፣ ይፈቅዳሉ ። በዚህ ፣ በኹለተኛው ፣ ጕዳይ ፣ ጥንድ ፣ ተወላጅነትም ፣ ሊመጣ ይችላል ። ሠርክ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ግጭቶች ፣ ይነሣሣሉ ፤ ለምሳሌ ፣ ያኸል ፣ በኹለተኛው ፣ ዓለም ፣ ጦርነት ፣ ዘመን ፣ ከባዕድ ፣ ወላጆች ፣ በተባበረው ፣ (አ.) መንግሥታት ፣ የተወለዱት ፣ ልጆች ፣ የወላጆቻቸውን ፣ የትውልድ ፣ አገር ፣ ይጎበኙ ፣ በነበሩበት ፣ ጊዜ ፣ በወላ

---

[14] የዩስ ፣ ሶሊ ፣ ልምን ፣ አጥብቀው ፣ ቢከተሉ ፣ ኑሮ ፣ የትም ፣ ቢቀመጥ ፣ (ቢኖር) ልጁ ፣ ፈረንሳዊ ፣ ይኾን ፣ ነበረ ።

[15] የዲሴምበር ፣ ፭፪ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፷፭ ፣ ዓ. ም. ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፱፩ ።

ጀቻቸው ፡ ዜግነት ፡ የተነሣ ፡ [16] ዜጎች ፡ ናቸው ፡ በመባል ፡ በነዚያው ፡ አገሮች ፡ ብዙ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ተመልምለው ፡ ነበረ ። ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ለጥ ንድ ፡ ዜግነት ፡ [17] ችግር ፡ መውጫ ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ጥረቶች ፡ ተደርገዋል ።

ሌላ ፡ ሊነሣ ፡ የሚችል ፡ ጉዳይ ፡ አገር-አልባነት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የሚመጣው ፡ እንዱ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ተወላጅነት ፡ ሳያገኝ ፡ ያንደኛውን ፡ አገር ፡ ተወላጅነትን ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያቹል ፡ ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ እንዲት ፡ ሴት ፡ የውጭ አገር ፡ ሰውን ፡ በማግባቷ ፡ ተወላጅነቷን ፡ ታጣለች ፤ የባሏ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ የሱን ፡ ተወላጅነት ፡ ያልሰጣት ፡ እንደኾነም ፡ አገር-አልባ ፡ ትኾናለች ። ባንዳንድ ፡ አኳኋኖች ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ [18] ሌላ ፡ ተወላጅነት ፡ ሳያገኝ ፡ [19] ተወላጅነቱን ፡ ሊገፈፍ ፡ (ሊነፈግ) ይችላል ። ዝቅ ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ ከኹለ ቱም ፡ የጥንድ ፡ ዜግነትና ፡ አገር-አልባነት ፡ (ጉዳት) ለማምለጥ ፡ የተቻለውን ፡ ማናቸ ውንም ፡ ጥረት ፡ ያደርጋል ።

እንግዲህ ፡ በተወላጅነት ፡ እንዱን ፡ ካንደኛው ፡ ጋራ ፡ ለማመጣጠን ፡ ያሉትን ፡ አቀራረቦች ፡ ከተመራመርን ፡ ዘንዳ ፡ የ፲፱፻፺፩ ፡ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነት ፡ ሕግን ፡ እስቲ ፡ እንመልከተው ። ኢትዮጵያ ፡ የዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ ልምን ፡ አጠንክራ ፡ የምትከ ተል ፡ አገር ፡ ነች ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከኢትዮጵያዊ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ ከኢትዮጵያዊት ፡ እናት ፡ የተወለደ ፡ ማናቸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዥ ፡

---

16 ጠያቂ ፡ (ይገባኛል ፡ ባዩ) የዚያው ፡ የይገባኛል ፡ ባዩ ፡ መንግሥትና ፡ ጥያቄው ፡ የቀረበበት ፡ መንግሥት፡ (የኹለቱም) ዜጋ ፡ ቢኾን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ በሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ ግጭት ፡ ሊነሣ ፡ ይች ላል ። የዚያው፡በካኔቪር፡ነገር፡የፔሩቪያ፡መንግሥት፡ራሱ፡ላንድ፡ንግድ፡ቤት፡መድበ፡ያወጣውን፡ቼክ፡ካለማ ከበሩ ፡ የተነሣ ፡ የተቀሰቀሰውን ፡ ጭቅጭቅ ፡ በጽሚው ፡ (ነባሩ) የዕርቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ. ም. ተወሰና ፡ የይገባኛል ፡ ጥያቄውን ፡ የኢጣልያና ፡ የፔሩቪያ ፡ መንግሥታት ፡ ለዕርቅ ፡ ድርድር ፡ ለማቅረብ ፡ ተስማሙ ። የይገባኛል ፡ ከርክሩም ፡ ወደእንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እጆች ፡ ስለተላለፈ ፡ ከነሱም ፡ አንዱ ፡ ራፋኖል ፡ ካኔቪር ፡ ነበረ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ከፔሩቪያ ፡ መንግሥት ፡ የኢጣልያ ፡ ተወ ላጆች ፡ የሚጠይቁትን ፡ ለማየት ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ካኔቪር ፡ የኢጣልያ ፡ ተወላጅ ፡ የነበረ ፡ ባይኾን ፡ ኦር ፡ እቤቱታውን ፡ ለመስማት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምንም ፡ ወይነት ፡ የፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ እይኖረ ውም ፡ ነበረ ፡ ነው ። ዜግነትን ፡ ለመለየት ፡ (ለመወሰን) ፔሩ ፡ ዩስ ፡ ሶሲን ፡ ስትከተል ፡ ኢጣልያ ፡ ዩስ ፡ ሳንጉይኒስን ፡ ተከትላለች ። ካንድ ፡ ኢጣልያዊ ፡ አባት ፡ በፔሩ ፡ ከተወለደ ፡ ዘንዳ ፡ ፔሩና ፡ ኢጣልያ ፡ ኹለቱም ፡ የየራሳቸው ፡ ተወላጅ ፡ ቁጠሩት ። ለከሳሽነቱ ፡ እቋም ፡ ጉዳዮች ፡ ሲባል ፡ ሰውዬውን ፡ ፔሩ ፡ እንደተወላጁ ፡ እንዲቈጥረውና ፡ በዕርቁ ፡ ስምምነት ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ የኢጣልያ ፡ ተወላጅ ፡ አልነ በረም ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቈረጠ ።

17 አንዱም ፡ የኤፕሪል ፡ (ሚያዝያ) ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ. ም. የሕጉ ፡ ቃል-ኪዳን ፡ ነው ። ኹለተኛው ፡ ባን ዳንድ ፡ የጥንድ ፡ ተወላጅነት ፡ ጉዳዮች ፡ ስለወታደራዊ ፡ ግዴታዎች ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ (ፕሮቶ ኮል) ነው ። በነዚህ ፡ ስምምነቶች ፡ ኹሉም ፡ አገሮች ፡ ፈራሚዎች ፡ አይደሉም ።

18 በናዚ ፡ አገዛዝ ፡ ጊዜ ፡ በየይማኖታቸው ፡ ወይም ፡ በፖለቲካ ፡ ማኅበርተኛነታቸው ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጀርመን ፡ ተወላጅነታቸውን ፡ ተነፍገው ፡ (ተነሥተው) ነበረ ። ይኸውና ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አገር-አልባ ዎች ፡ ተደርገው ፡ ነበረ ። ደግሞም ፡ አንዳንድ ፡ ተግባርን ፡ (ድርጊቶችን) ከመፈጸም ፡ የተነሣ ፡ ዜግነትን፡ የሚያስወርስ ፡ መንግድ ፡ እንዲኖር ፡ አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ይደነግጋሉ ፤ ዜግነቱን ፡ ያስወረሰውም ፡ ሰው ፡ አገር-አልባ ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

19 በቢሾፐ ፡ ኢንቴርናሽናላዊ ፡ ሕግ ፡ ጀኒፔ ፡ (ጀኖ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም.) ያገር-አልባዎችን ፡ መብት ፡ ስለመጠበቅ ፡ የተደረጉ ፡ ሙከራዎች ፡ ምርምርንና ፡ በዚያው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለ ከቷል ።

(ዜጋ ፡ ወይም ፡ ተወላጅ) ነው ። [20] አባትየው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዥ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ልጁ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያላንዳች ፡ ጭቅጭቅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን ፡ ያገኛል ፤ እናትየዋ ፡ ብቻ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ የኾነች ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ ልጁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በመኖርና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅነትን ፡ አውልቆ ፡ መጣሉን ፡ በማስረዳት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመኾን ፡ ፈቅዶ ፡ እንዲመርጥ ፡ ይገባል ። እንደዚህ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ በውልደቱ ፡ [21] የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንደኾነ ፡ ይቈጠራል ። ካንዲት ፡ ካላገባች ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሴት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ይኾናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከውጭ ፡ አገር ፡ ወላጆች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለተወለደ ፡ ልጅ ፡ ዜግነትን ፡ በመቀባት ፡ ካልተቀበለ ፡ (ጠይቆ ፡ ካልዜገ ፡ ወይም ፡ ናቹራላይዜሺን) በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ስለሚኾንበት ፡ ወይም ፡ ሊኾን ፡ ስለሚችልበት ፡ መንገድ ፡ ምንም ፡ ውሳኔዎች ፡ ሕጉ ፡ አልያዘም ። በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ሲገለጥ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ የዩስ ፡ ሶሊ ፡ ፅንሰ-ሓሳብ ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ (በደፈናው) ይህ ፡ ለአስተውሎ ፡ የሚገባ ፡ ማለፊያ ፡ ነገር ፡ ነው ። በዚህ ፡ አገር ፡ ከሚኖሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሚበዙት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህልና ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የጐሣ ፡ አጋ ፡ (ወገን) የመጡ ፡ ኤውሮጳውያኖች ፡ ናቸው ። ከእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ወላጆች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ወዲያውኑ ፡ (ያለ ፡ ከርክር) እንደተወለዱ ፡ እንደኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ እንዲቈጠሩ ፡ አያሻም ፡ ምናልባትም ፡ እነሱ ፡ ራሳቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ እንደተወለዱ ፡ ወዲያውኑ ፡ መቀላቀል ፡ አይሹ ፡ ይኾናል ። እንደዚህ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈልጉ ፡ በመቀባት ፡ (የራስን ፡ ትቶ ፡ ሌላ ፡ በመቀበል) የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ ደቡባዊ ፡ ሱዳን ፡ ሰሜናዊ ፡ ኬኒያና ፡ ሶማሊያ ፡ ከመሰሉት ፡ ክፍለ-ሀገሮች ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተዋል ። ከዳር ፡ ደንበር ፡ (ወሰን) ክፍለ-ሀገር ፡ እንደሚኖሩት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ያሉ ፡ የጐሣ ፡ አጋዎች ፡ (ወገኖች) የወረዱ ፡ ስለኾነ ፡ እንደገቡ ፡ በምሉ ፡ (በፍጹም) ተቀላቅለው ፡ ይዋጣሉ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎችና ፡ ውልዶቻቸው ፡ ከወሰኑ ፡ አጠገብ ፡ ከሚቀመጡት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ሊለዩ ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እነሱም ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ውልዶቻቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ አይደሉም ። ምናልባት ፡ በነባርነት ፡ (ለምንጊዜውም) በኾነ ፡ አኳኋን ፡ [22] ከዚሁ ፡ ለመቅረት ፡ ላቀዱ ፡ (ላሰቡ) በኢትዮጵያ ፡ ለሚኖሩ ፡ ያንዳንድ ፡ ተለይተው ፡ የተመደቡ ፡ የጐሣ ፡ አጋዎች ፡ አባሎች ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ይቈጠሩ ፡ ዘንድ ፡ እና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱ ፡ የነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ልጆችም ፡ በመወለድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ለመኾን ፡ የሚ

---

20 "ተገዥ" የሚለው ፡ የንግግር ፡ አገባብ ፡ የተደረገው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዘውድ-ሙሉን ፡ አገር ፡ ስለኾነች ፡ ነው ። ለኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ ጉዳዮች ፡ ሲኾን ፡ በተወላጅ ፡ በዜጋ ፡ ወይም ፡ በተገዥ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ እንደሌለ ፡ ይገነዘባል ። በኤርትራ ፡ የሚኖሩ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ እቋም ፡ የሚዳኘው ፡ በዲሴም ቤር ፡ (ታኅሣሥ?) ፪ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ዐዋጅ ፡ ቍ. ፲፻፯ (፩) ነው ። ከውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ በቀር ፡ የኤሪትራ ፡ ኗሪዎች ፡ ዅሉ ፡ የፌዴሬሺኑ ፡ ተወላጆች ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በቀረው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ዅልጊዜም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተብለው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ስለነበሩ ፡ ኤሪትራ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እንደገና ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕጉ ፡ ትርጉም ፡ በሚፈታው ፡ አገባብ ፡ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ ከኢትዮጵያዊት ፡ እናት ፡ እንደተወለዱ ፡ ሰዎች ፡ ዅነው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ይቀላቀላሉ ፡ (ይዳመራሉ) ። በተቈረጠው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ኤሪትራውያኖች ፡ (ማለት ፡ ከዚያ ፡ የተወለዱ ፡ እና ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ያገሩ ፡ ተወላጅ ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ወላጅ-አያት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች) ከፈዴሬሽኑ ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነትን ፡ ለመያዝ ፡ ሊመርጡ ፡ ይችላሉ ።

21 ቢፖለቲካዊ ፡ መብቶች ፡ መጠቀም ፡ ረገድ ፡ በመወለድ ፡ ተግዥኖና ፡ በሌሎቹ ፡ መካከል ፡ ልዩነቶች ፡ ስላሉ ፡ ይህ ፡ አውራ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በማሳሰቢያ ፡ ፴፮ ፡ እና ፡ በወባሪው ፡ ጽሑፍ ፡ ያለውን ፡ ምርምር ፡ ይመለከቷል ።

22 በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሲታይ ፡ ምንባሩን ፡ ከዚሁ ፡ ኢንፍራ ፡ (ዝቅ ፡ ብሎ ፡) ከማስገንዘቢያ ፡ ቍ. ፱ቮ-፴፱ና ፡ ወጃቢ ፡ ጽሑፉን ፡ ይመለከቷል ።

ያበቋቸው ፣ አንዳንድ ፣ ማሻሻያዎች ፣ ሳያስፈልጉ ፣ አይቀሩም ። ምናልባት ፣ ይህ ን ፣ ከልማድ ፣ ለመውጣት ፣ የሚችል ፣ ልዩነት ፣ በማድረግ ፣ የዩስ ፣ ሳንጦይኢስ ፣ ልም ፣ ለኢትዮ ጵያ ፣ ደኅና ፣ አድርን ፣ የበጀ ፣ (የተሰማማ) ይመስላል ።

ኢትዮጵያዊ ፣ ዜጋ ፣ በመኾን ፣ ስለሚመጣው ፣ የጋብቻ ፣ የደንበኛና ፣ ሕጋዊ ፣ የመኾን ፣ እና ፣ የጉዲፈቻ ፣ ውጤትን ፣ የሚመለከቱ ፣ ውሳኔዎችን ፣ ሕጉ ፣ ይዟል ። ከእንድ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ጋራ ፣ ወደ ፣ ሕጋዊ ፣ ማእሰረ-ጋብቻ ፣ የምትገባ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሴት ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜግነትን ፣ ትይዛለች ። የውጭ ፣ አገር ፣ ሰውን ፣ የምታገባ ፣ ኢትዮጵያዊት ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነቷን ፣ የምታጣው ፣ የባሏ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ የ ሱን ፣ ተወላጅነት ፣ ለሏም ፣ ያለበሳት ፣ ወይም ፣ የሸለማት ፣ (የሰጣት) እንደኾነ ፣ ነው ። ግንም ፣ ኢትዮጵያዊት ፣ በተቻለበት ፣ ላይ ፣ በጋብቻዋ ፣ አገር-አልባ ፣ እንዳትኾን ፣ ይህ ፣ ዋስትናን ፣ ይሰጣታል ፣ እንዲሁም ፣ ያገቡ ፣ ሴቶች ፣ ባንዴ ፣ ዅለት ፣ ዜግነት ፣ [23] እንዳይ ኖራቸው ፣ ለማገድ ፣ ይሞክራል ።

በደንብ ፣ ሕጋዊ ፣ በማድረግ ፣ ረገድ ፣ ላይም ፣ ይኸው ፣ መሠረተ-ሓሳብ ፣ የሚፈጸ ምበት ፣ ነው ። በደንብ ፣ ሕጋዊ ፣ ያለመኾንንት ፣ የሕግ ፣ ፅንሰ-ሓሳብ ፣ (አስተያየት) ስለሌለ ፣ በደንብ ፣ ሕጋዊ ፣ መኾን ፣ በኢትዮጵያ ፣ አለመኖሩን ፣ ይገነዘቧል ። አንድ ፣ ልጅ ፣ ተወላጅነቱን ፣ በፍርድ ፣ ሊያረጋግጥባቸው ፣ የቻለባቸው ፣ ወላጆች ፣ ልጅ ፣ ነው ፤ ልጅነቱን ፣ አንዱ ፣ ካረጋገጠ ፣ ዘንዳም ፣ ወላጅነቱ ፣ የተረጋገጠበት ፣ ማግባቱ ፣ ወይም ፣ አለማግባቱ ፣ ለጉዳዩ ፣ አስፈላጊነት ፣ የለውም ። እንግዲህ ፣ በመወለድ ፣ ከኢትዮጵያዊት ፣ እናት ፣ ወይም ፣ ከኢትዮጵያዊ ፣ አባት ፣ ጋራ ፣ ሊገናኝ ፣ (ሊዛመድ) የቻለ ፣ ልጅ ፣ ኢትዮ ጵያዊ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ካላገባች ፣ ኢትዮጵያዊት ፣ እናት ፣ የተወለደ ፣ ልጅን ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ አባቱ ፣ በራሱ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ያወቀለት ፣ (በደንብ ፣ ሕጋዊ ፣ ያደረገው) እንደ ኾነ ፣ ችግሮች ፣ ይነሣሉ ። እኹንም ፣ ቢኾን ፣ ከጥንድ ፣ ተወላጅነት ፣ (ዜግነት) ኾነ ፣ ወይም ፣ ካገር-አልባነት ፣ ለማምለጥ ፣ በመድከም ፣ ያባትየው ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ ያባትየ ውን ፣ ተወላጅነት ፣ ከነመብቶቹና ፣ ጓዙ ፣ ጋራ ፣ ለልጁ ፣ ለማላበስ ፣ የሚችል ፣ የኾነ ፣ እንደኾነ ፣ ብቻ ፣ ልጁ ፣ በደንብ ፣ ሕጋዊነትን ፣ በማግኘቱ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነቱን ፣ እንዲያጣ ፣ ሕግ ፣ ይፈቅዳል ።

እንድ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ልጅን ፣ በጉዲፈቻ ፣ (ጡት ፣ በማጥባት) የውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ስለያዘው ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነቱን ፣ እንዲያሳጣው ፣ ምክንያት ፣ አይኾንም ። እንደዚሁም ፣ ይህን ፣ በመገልበጥ ፣ (በማዘዋወር) ፣ በጉዲፈቻ ፣ ልጅነት ፣ በእንድ ፣ ኢት ዮጵያዊ ፣ የተያዘው ፣ ልጅ ፣ ከዚሁ ፣ (ብቻ) የተነሣ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅ ፣ አይኾንም ። ከዚህ ፣ ላይ ፣ ጥንድ ፣ ተወላጅነትና ፣ አገር-አልባነት ፣ ሊኖር ፣ ይችላል ። ለምሳሌ ፣ ያኸል፣ ኢትዮጵያዊውን ፣ ልጅ ፣ የውጭ ፣ አገሩ ፣ ሰው ፣ በጉዲፈቻ ፣ የያዘው ፣ እንደኾነና ፣ በጉዲ ፈቻው ፣ (ጡት ፣ ዐጥቢው) ወላጅ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ያባቱን ፣ ተወላጅነት ፣ የወሰደ ፣ እንደኾነ ፣ ልጁ ፣ ባንዴ ፣ ዅለት ፣ (ጥንድ) ዜግነትን ፣ ያገኛል ። እንደተባለው ፣ በዚሁ ፣ ወይነት ፣ መንገድ ፣ ኢትዮጵያዊው ፣ በጉዲፈቻ ፣ የያዘው ፣ ልጅ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የቀድሞው ፣ ተወላጅነቱን ፣ ያጣ ፣ እንደኾነ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜግነትን ፣ በመቀባት ፣ ካላገኘ ፣ በቀር ፣ አገር-አልባ ፣ ይኾናል ። ይህ ፣ ሊኾን ፣ የቻለበት ፣ ምክን ያት ፣ ሕጉ ፣ በተሠራበት ፣ በ፲፱፻፸ ፣ ዓ. ም. ኢትዮጵያውያኖች ፣ በጉዲፈቻ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎችን ፣ የመያዛቸው ፣ ተግባር ፣ ያነሰ ፣ (ያጠጠ) ስለነበረ ፣ ጥሪቱ ፣ ኢትዮጵያዊው ሕፃን ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነቱን ፣ እንዳያጣ ፣ ለመከላከል ፣ ኑሮ ፣ ሊኾን ፣ ይችላል ።

---

23 ቢጋብቻዋ ፣ የተነሣ ፣ ብሔራዊ ፣ ሕግ ፣ ዜግነቷን ፣ እንድታጣ ፣ ያላደረጋት ፣ ከኢትዮጵያዊ ፣ ጋራ ፣ የተጋባ ችው ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሴት ፣ ጥንድ ፣ ዜግነት ፣ ሊኖራት ፣ ይችል ፣ ይኾናል ። ዅኖም ፣ ከኢትዮጵያ ፣ በዙል፣ ዅና ፣ ሲመለከቱት ፣ ያገባች ፣ ሴት ፣ ከባሏ ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ የኾነ ፣ ዜግነት ፣ እንዲኖራት ፣ የሚፈለግ ፣ ነው ።

አኹን ፣ (ግን) በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ የጉዲፈቻ ፣ ጉዳይ ፣ [24] በምሉ ፣ ከተዘረጋ ፣ ዘንዳ ፣ በኢትዮጵያውያኖችና ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ በጉዲፈቻ ፣ የመያያዙ ፣ ተግባር ፣ እያደገ ፣ ሊኼድ ፣ ይችል ፣ ይኾናል ። ምናልባትም ፣ የተወላጅነት ፣ ሕጉ ፣ ውሳኔዎች ፣ እንደገና ፣ እንዲመረመሩና ፣ እንዲገመገሙ ፣ ያስፈልግ ፣ ይኾናል ። በውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ በደንበኛ ፣ በሕግ ፣ ከታወቀለት ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ልጅ ፣ አቋም ፣ የሚለይበቱን ፣ ለመመራመር ፣ ቢያስቸግርም ፣ ቅሉ ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ በጉዲፈቻነት ፣ የተያዘው ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ልጅ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነቱን ፣ እንዲያጣ ፣ የማያስፈልግ ፣ ሊኾን ፣ ይችላል ። ይኹን ፣ እንጂ ፣ በጠራው ፣ መንገድ ፣ ሲታይ ፣ በጉዲፈቻ ፣ በኢትዮጵያዊው ፣ የተያዘው ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ልጅ ፣ በዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ የተነሣ ፣ አገር-አልባ ፣ እንዲደረግ ፣ አያስፈልግም ። የቀድሞውን ፣ ተወላጅነቱን ፣ ያጣ ፣ እንደኾነም ፣ በጉዲፈቻነቱ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተወላጅነትን ፣ እንዲያገኝ ፣ ያስፈልጋል ።

አንድ፣ የ ውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ለዐምስት ፣ ዓመት ፣ መቀመጫውን ፣ በኢትዮጵያ ፣ ካደረገ ፣ በኋላ ፣ በመቀባት ፣ ዜግነትን ፣ ለመቀበል ፣ ይችላል ። "በብሔራዊው ፣ ሕግ ፣ ደንቦች ፣ መሠረት ፣ የምሉ ፣ ዕድሜ ፣ ሰው ፣" በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፯፰ ፣ ዐሥራ ፣ ሰምንት ፣ ዓመቱን ፣ የመላ ፣ ሰው ፣ እንዲኾን ፣ ይገባዋል ። "ለራሱ ፣ ኑሮ ፣ የሚበቃን ፣ ለማፍራትና ፣ ራሱንና ፣ ቤተሰቡን ፣ የሚችል ፣" እንዲኾን ፣ ይገባዋል ። "ያማርኛ ፣ ቋንቋ ፣ በፍጹም ፣ የሚያውቅ ፣ ያለችግር ፣ በቀላሉ ፣ የሚናገርና ፣ የሚጥፍ ፣ [26] " እንዲኾን ፣ ይገባዋል ። ለመደምደሚያም ፣ "ከዚያ ፣ በፊት ፣ በወንጀለኛነት ፣ ወይም ፣ ሲወርድ ፣ ሲዋረድ ፣ የመጣን ፣ የልማዱን ፣ ሕግ ፣ በመጣሱ ፣ ማናቸውም ፣ ቅጣት ፣ ያልተፈረደበት ፣ (ያላገኘው)" ሰው ፣ እንዲኾን ፣ ይገባዋል ። ይህ ፣ የመጨረሻው ፣ ጥቃቅንን ፣ ኾነ ፣ ከባድ ፣ ወንጀሎችን ፣ የሚያጠቃልል ፣ የወንጀለኛ ፣ ሕጉን ፣ ያዘጋጀው ፣ ውሳኔ ፣ ከወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕጉ ፣ ጋራ ፣ በማነጣጠር ፣ (በማመሰካከር) የሚታይ ፣ ወይም ፣ የሚነበብ ፣ ነው ። ጥቃቅን ፣ ወንጀሎችን ፣ በመፈጸም ፣ የተፈረደበት ፣ ሰው ፣ የቅባት ፣ ዜግነትን ፣ (ተወላጅነትን) ይነፈጋል ፣ ብሎ ፣ ማመኑ ፣ ያጻግታል ። ምናልባት ፣ "ወንጀል ፣ ወይም ፣ ሲወርድ ፣ ሲዋረድ ፣ የመጣ ፣ የልማድ ፣ ሕግን ፣ መጣስ" የቃል ፣ አሰካክ ፣ "ግሉም ፣ ኢን ፣ ቤ ፣" (በራሱ ፣ መጥር ፣ የኾነ) ማለት ፣ በወግና ፣ ልማድ ፣ እንደ ፣ ወንጀሎች ፣ ተቁጥረው ፣ በኢትዮጵያ ፣ የሚያስቀጡ ፣ ድርጊያዎች ፣ ወይም ፣ በኹሉም ፣ ዘንድ ፣ ዋፋት ፣ ናቸው ፣ ተብለው ፣ የታወቁ ፣ ተብሎ ፣ እንዲተረጐሙ ፣ ያሻል ። ይሀን ፣ ጉዳይ ፣ የቅባት ፣ ተወላጅነት ፣ ማመልከቻዎችን ፣ (ጥያቄዎችን) ለመቀረጥ ፣ ዐላፊ ፣ የኾነው ፣ ኮሚሺን ፣ የሚከለለው ፣ ወይም ፣ የሚወስነው ፣ ነው ።

የተወላጅነቱ ፣ ሕግ ፣ ያገር ፣ ግዛት ፣ ሚኒስትሩን ፣ የውጭ ፣ ጉዳይ ፣ ሚኒስትሩንና ፣ ምናልባት ፣ በንጉሠ-ነገሥቱ ፣ የሚሾም ፣ ወይም ፣ የሚወከል ፣ እንድ ፣ ሌላን ፣ "የንጉሠ-ነገሥቱ ፣ መንግሥት ፣ ግዛት ፣ መኰንን" የሚከት፣ ልዩ ፣ የመንግሥት ፣ ኮሚሺን ፣ እንዲኖር ፣ ያዝዛል ። ኮሚሺኑ ፣ ማመልከቻዎችን ፣ የሚያይና ፣ ጠያቂውን ፣ ከፊቱ ፣ አቅርቦ ፣ የሚያዳምጥ ፣ ነው ። ውሳኔው ፣ መደምደሚያ ፣ ነው ። የቅባት ፣ ዜግነት ፣ የተቀበለውን ፣ ሰው ፣ ሚስት ፣ አይከትም ። ሚስቲቱ ፣ የራሷን ፣ ጥያቄ ፣ ማቅረብ ፣ ይገባታል ። ስለልጆች ፣ ሕጉ ፣ አንዳችም ፣ እይልም ፣ ግልጥ ፣ የኾነ ፣ ውሳኔ ፣ ከሌለ ፣ ዘንዳም ፣ በድሜያቸው ፣

---

24 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ ምዕራፍ ፣ ፲፭ ።

25 ፈረንሳይ ፣ ቀድሞ ፣ የፈረንሳዊነትን ፣ አጽም ፣ ለጉዲፈቻ ፣ ልጅ ፣ ትነፍግ ፣ ነበረ ። አኹን ፣ ግን ፣ እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ልጅ ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ የተቀመጠ ፣ እንደኾነ ፣ የፈረንሳይ ፣ ተወላጅነትን ፣ ይገባኛል ፣ ብሎ ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ። የጂሉሞቤር ፣ ፳፪ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፳፭ ፣ ዓ. ም. ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፱፭ ።

26 ቁየት ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ አቁጣጠር ፣ መስከረም ፣ ፳፭ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፳፻፯ ፣ ዓ. ም. በወጣው ፣ የተወላጅነት ፣ ሕግ ፣ ማሻሻያ ፣ ያምስት ፣ ዓመት ፣ መቀመጥና ፣ ያማርኛ ፣ ችሎታ ፣ እስፈላጊነት ፣ በኮሚሲዮን ፣ ሊታለፍ ፣ የሚቻል ፣ ነው ።

ፀሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሲመላቸው ፡ የራሳቸውን ፡ ጥያቄ ፡ ያቀርባሉ ፡ ተብሎ ፡ ሊታመን ፡ ይገባል ።

የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነት ፡ ሊታጣ ፡ የሚችለው ፡ የሌላ ፡ ተወላጅነት ፡ በማግኘት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለንዲት ፡ ሴት ፡ ጉዳይ ፡ ሲኾን ፡ የባልየው ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ተወላጅነቱን ፡ ሊያላብሳት ፡ ወይም ፡ ሊሰጣት ፡ [27] ከቻለ ፡ (ይህ ፡ ሒሳብ) ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመጋባት ፡ (ዜግነት) ማጣትን ፡ ያጠቃልላል ። አንድ ፡ ሰው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ተወላጅነትን ፡ ሲያገኝ ፡ ወይም ፡ ሲቀበል ፡ ያዲሱ ፡ ተወላጅነቱ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ባንዱ ፡ ኹለት ፡ ዜግነትን ፡ ቢፈቅድለትም ፡ [28] ቅሉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነቱን ፡ ያጣል ። አንዳንድ ፡ ተግባሮችን ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ ሕገ-ወጥ ፡ በኾነ ፡ ምግባር-አመራር ፡ (ከንዳክት) ላይ ፡ በመውደቅ ፡ ዜግነትን ፡ ወይም ፡ ተወላጅነት ፡ ስለማጣት ፡ ሕጉ ፡ የያዛቸው ፡ ምንም ፡ ውሳኔዎች ፡ የሉም ። ያንዳንድ ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ (ማና) እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ያቅፋሉ ። በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ምሳሌ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዲወጣ ፡ ሲያዘው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ (መንግሥት) የጦር ፡ ኀይሎች ፡ የሚያገለግል ፡ ዜጋ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተወላጅነቱን ፡ ያጣል ። ለመፈጸሙ ፡ ካልተሳነው ፡ (ካልቻለ) በቀር ፡ [29] ማስጠንቀቂያው ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ባሉት ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ መውጣት ፡ (መተው) ይገባዋል ። ደግሞም ፡ ፈረንሳይ ፡ በትውልዳቸው ፡ ሳይኾን ፡ የፈረንሳይ ፡ ዜግነትን ፡ ያገኙ ፡ ሰዎች ፡ አንዳንድ ፡ ተግባሮችን ፡ በመፈጸማቸው ፡ ምክንያት ፡ ዜግነታቸውን ፡ የሚያጡበትን ፡ ምክንያት ፡ [30] ይናገራል ። እነዚህ ፡ ተግባሮችም ፡ በፈረንሳይ ፡ ውስጣዊ ፡ ወይም ፡ አፍአዊ ፡ (የውጭ) ጸጥታ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ መፈረድን ፡ በፈረንሳዊው ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ [31] ከ፭፻፱-፭፻፴፩ ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ እናቅጽ ፡ የሚያስቀጡ ፡ ወንጀሎች ፡ በመፈጸም ፡ የተፈረደበትን ፡ (ከጦር ፡ ኀይሎች) በመክዳት ፡ የተፈረደበትን ፡ ለፈረንሳይ ፡ ጥቅሞች ፡ ተቃራኒ ፡ ኹኖ ፡ በባዕድ ፡ መንግሥት ፡ እግር ፡ (ስም) ኹኖ ፡ መሥራትን ፡ ወይም ፡ ከፈረንሳይ ፡ ጠባይ ፡ ጋራ ፡ የማይሰማማ ፡ ወይም ፡ የማይዋደድ ፡ ተግባር ፡ መፈጸምን ፡ ወይም ፡ የዐምስት ፡ ዓመታት ፡ እስራትን ፡ የሚያስከትል ፡ ማናቸውንም ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞ ፡ መፈረድን ፡ ኹሉ ፡ ያጠቃልላል ። እነዚህ ፡ ድርጊያዎች ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተወላጅነት ፡ ካገኙበት ፡ ቀን ፡ [32] አንሥቶ ፡ ባሉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ። ደግሞም ፡ ዜግነትን ፡ የማጣቱ ፡ ተግባር ፡ መዠመሪያውኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ ከኾኑና ፡ ይህንኑ ፡ ተወላጅነታቸውን ፡ ጠብቀው ፡ ከቈዩ ፡ [33] የሰውየውን ፡ ሚስትና ፡ ልጆች ፡ ይከታል ።

---

27 በአሜሪካዊው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በማግባቷ ፡ ምክንያት ፡ ተወላጅነቷን ፡ አታጣም ። በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ፈረንሳዊት ፡ ካልፋቀቸው ፡ በቀር ፡ (በወንድየው ፡ ሕግ ፡ የባዕጋ ፡ ዜግነት ፡ ለማግኘት ፡ ካልቻለች ፡ ልትሸረውም ፡ አትችል) ፡ በጋብቻዋ ፡ የፈረንሳይ ፡ ተወላጅነቷን ፡ ይዛ ፡ ትቀራለች ። የ፲፱፻፱፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፩ ።

28 አሜሪካዊው ፡ ሕግም ፡ የሚያመራው ፡ ወደዚያው ፡ ወይነት ፡ ውጤት ፡ ነው ። የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ርእስ ፡ ፭ ፡ መደብ ፡ ፭፲፯፻፹፭ (ø) ፡ (፩) ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ወቃደራዊ ፡ አገልግሎትን ፡ ለመፈጸም ፡ ከሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመታት ፡ እስከሚያልፉ ፡ ድረስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የፈረንሳይ ፡ ዜግነቱን ፡ አያጣም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነቱን ፡ ሲተወው ፡ ይችላል ፡ ይህን ፡ ካደረገ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተወላጅነቱን ፡ አያጣም ። የ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አናቅጽ ፡ ፫፮ ፡ ፫፰ ።

29 ያ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፮ ።

30 ያ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፩ ።

31 እነዚህ ፡ መደቦች ፡ (ከፍሎች) ሕጉ-መንግሥታዊውን ፡ ቻርተር ፡ ስለሚቃወሙ ፡ ወንጀሎች ፡ የሌሎችን ፡ ብሔራዊ ፡ መብቶች ፡ ስለመንካትና ፡ በነጻነት ፡ ላይ ፡ ስለመነሣት ፡ የሚኾኑ ፡ ናቸው ።

32 የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፭ ።

33 የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፫ ።

በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ተግባሮችን ፡ በመፈጸም ፡ ዜግነት ፡ ስለማጣቱ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ለመገዛት ፡ ቃለ-መሐላ ፡ መግባትን ፡ ያለተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ጎይሎች ፡ ማገልገልን ፡ የተገሸነት ፡ ቃለ-መሐላ ፡ መግባት ፡ የሚያስፈልግበት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ መቀበልን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ለመምረጥ ፡ ድምፅ ፡ መስጠትን ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ (ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት) መከዳትን ፡ ያገር ፡ ክሕደት ፡ መፈጸምንና ፡ ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ለማምለጥ ፡ በማቀድ ፡ [34] ከተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ተነሥቶ ፡ መኼድን ፡ (መልቀቅን) የሚጨምሩ ፡ የሰፋና ፡ የተዘረጉ ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ። በውጭ ፡ አገር ፡ የመምረጥ ፡ ድምፅን ፡ በመስጠት ፡ ዜግነት ፡ ስለማሳጣቱ ፡ ጉዳይ ፡ ኮንግሬሱ ፡ (ምክር ፡ ቤቶቹ) ያለውን ፡ ሥልጣንን ፡ የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲደግፈው ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ ስለከዳ ፡ ዜግነቱን ፡ መክላቱ ፡ [36] (ዕርግጥ ፡ ነው ፡ በመክዳቱ ፡ ሊቀጣ ፡ ይቻላል) ወይም ፡ ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ለማምለጥ ፡ ዐስቦና ፡ ዐቅዶ ፡ [37] የተባበረው ፡ መንግሥታትን ፡ ለቅቆ ፡ በመኼዱ ፡ (እኹንም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰውንም ፡ ቢኾን ፡ ዜግነትን ፡ በማሳጣት ፡ ላይኾን ፡ ሊቀጣ ፡ ይቻላል) ግን ፡ ኢሕገ-መንግሥታዊ ፡ ወይም ፡ ሕገ-መንግሥታዊ-ያይደለ ፡ ተግባር ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በይኗል ። ስለዜጉ ፡ (በመቀባት ፡ ዜግነትን ፡ የተቀበሉ) ዜጋዎች ፡ ዜግነት ፡ ማጣት ፡ የሚኾኑ ፡ አንዳንድ ፡ ውሳኔዎች ፡ በመወለድ ፡ በዜጉ ፡ ላይ ፡ የማይፈጸሙ ፡ [38] ስለኾነ ፡ ኢሕገ-መንግሥታዊ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ ተነግሯል ።

ዜግነትን ፡ ስለማጣት ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ ላሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እነዚህ ፡ የሚገልጡና ፡ የሚያብራሩ ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተስተካክሎ ፡ እንደተነገረው ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ አንዳችም ፡ ውሳኔዎች ፡ ከቶ ፡ የሉም ። ምናልባት ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ የተወላጅነት ፡ ፅንሰ-ሐሳብና ፡ ያደረገውንም ፡ ቢያደርግ ፡ የማናቸውንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አገር-አልባነት ፡ ካለመፈለጉ ፡ ጋራ ፡ የማይዋደዱ ፡ (የማይሰማሙ) በመኾናቸው ፡ ይኾናል ። እንግዲህ ፡ ሕጉ ፡ እኹን ፡ እንዳለው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተወላጅነት ፡ ሊታጣ ፡ የሚችለው ፡ በገዛ ፡ ፈቃድ ፡ ያንዱን ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ተወላጅነት ፡ በመቀበል ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ የሌላ ፡ አንዱን ፡ አገር ፡ ተወላጅነት ፡ በማግኘት ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ ሕጋዊነትን ፡ በማፍራት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የተወላጅነቱ ፡ ሕግ ፡ ዜግነቱን ፡ ላጣ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መልሶ ፡ የማግኘቱን ፡ ተግባር ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ያደርግለታል ። ያንዱን ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ በመቀበል ፡ ዜግነቱን ፡ ያጣ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚያስፈልግ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሶ ፡ ለንጉሠ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ (ላገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ላይኾን ፡ አይቀርም) እንደገና ፡ እንዲቀበሉት ፡ ጥያቄውን ፡ ማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጥያቄውንም ፡ የሚያስነፍግ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመጋባቷ ፡ ዜግነቷን ፡ ያጣች ፡ ሴት ፡ ጋብቻው ፡ በፍቺ ፡ በመለያየት ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ሲፈርስ ፡

---

34 የተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ (ኮድ) ፡ ርእስ ፡ ፰ ፡ መደብ ፡ ፩፻፬ሺ፱፻፹፭ ።

35 በፔሬዝና ፡ በብራውኔል ፡ መካከል ፡ የየግዜ ፡ ዩ. ኤስ. ፵፬ ፡ (፲፱፻፶፭) ።

36 በትሮፕና ፡ በዳላስ ፡ መካከል ፡ የየግዜ ፡ ዩ. ኤስ. ፴፻፲፭ ፡ (፲፱፻፶፯) ።

37 በኬኔዲ ፡ እና ፡ በሜንዶዛ-ማርቲኔዝ ፡ መካከል ፡ የየፅሁፍ ፡ ዩ. ኤስ. ፴፻፵፬ ፡ (፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም.) ።

38 በሽናይዴር ፡ እና ፡ በራስክ ፡ መካከል ፡ ፫፬ ፡ የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሬፖርተር ፡ (አስተዋቂ) ፭፻ሺ ፡ ፭፻፹፯ ፡ (፲፱፻፷፰) ፡ በተወለደበት ፡ አገሩ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ በመቀመጥ ፡ በመቀባት ፡ የዜገውን ፡ ዜጋ ፡ ዜግነት ፡ እንዲያጣ ፡ ሕገ-መንግሥቱ ፡ በሚፈቅደው ፡ መንገድ ፡ ኮንግሬስ ፡ ሲያዝ ፡ አይችልም ፡ ሲባል ፡ ተበየነ ። በውልደታቸው ፡ ዜጎች ፡ የኾኑትን ፡ ይህ ፡ ጭበጣ ፡ (ውሱንነት) የማይነካቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የፍትሕን ፡ ተገቢ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያቃውስ ፡ የማይገባና ፡ ትክክለኛ ፡ ያልኾነ ፡ በማበላለጥ ፡ መለየት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አጥብቆ ፡ አብራራ ።

ምንባሯን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደረገችና ፡ እንደገና ፡ እንዲቀበሏት ፡ የጠየቀች ፡ እንደኾነ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነቷን ፡ እንደገና ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለች ። ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተገለጠው፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ከአንዲት ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ተወልዶ ፡ የባዕድ ፡ አባቱን ፡ ዜግነት ፡ የያዘ ፡ ልጅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በመኖርና ፡ ያባቱን ፡ ተወላጅነት ፡ እውልቆ ፡ በመጣል ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነትን ፡ እንደገና ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ። ደንበኛ ፡ ሕጋዊ ፡ በመኾን ፡ ያባቱን ፡ ተወላጅነት ፡ ባገኘ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ አይፈጸምበትም ። ኢትዮጵያዊ ፡ ተወላጅነት ፡ እንደገና ፡ በሚገኝበት ፡ ላይ ፡ እንደዜና ፡ ከመገመት ፡ ይልቅ ፡ ሰው የውን ፡ በትውልዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተገዥ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቀላል ።

ለማጠቃለሉ ፡ ዜግነትን ፡ ለመከለል ፡ (ለመወሰን) ኢትዮጵያ ፡ የዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ ልምን ፡ ትከተላለች ። ምናልባት ፡ አባቶቻቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ቢኾኑም ፡ ቅሉ ፡ በጐሣቸው ፡ ከኢትዮጵያውያኖች ፡ የዘር ፡ ግንዳ ፡ አጋዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ከኾኑት ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ አቀራረብ ፡ በፍጹም ፡ አዋጋቢ ፡ ነው ። የተወላጅነቱ፡ ሕግ ፡ ጥንድ ፡ ተወላጅነትን ፡ ወይም ፡ አገር-አልባነትን ፡ ለመከላት ፡ ይሞክራል ። በሰውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በመቀባት ፡ መዜግ ፡ የሚኾኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ። ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነት ፡ ሊታጣ ፡ የሚቻለው ፡ ያንዱን ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ በመቀበል ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ ሕጋዊ ፡ በመኾን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከታጣ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነትን ፡ መልሶ ፡ ማግኘቱ ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ። በደፈናው ፡ የ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም. የተወላጅነቱ ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የዛሬ ፡ ችግሮቿ ፡ ደኅና ፡ የሚበጅ ፡ ይመስላል ።

በትውልድና ፡ በዜጉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜጎች ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ልዩነቶች ፡

በትውልድና ፡ በዜጉ ፡ ዜጎች ፡ መካከል ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉ ፡ ልዩነቶች ፡ የሚገኙት፡ በፖሊቲካዊ ፡ መብቶች ፡ ግንባር ፡ በኵል ፡ ብቻ ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡ በብሔራዊ ፡ (ሲቪል) መብቶች ፡ በመጠቀም ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያውያኖች ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ተገዦች) መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አይኑር ፡ ይላል። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፹፱(፪) መሠረት ፡ ብሔራዊ ፡ መብት ፡ ማለት ፡ በመፈጸም ፡ (በማድረጉ) በአገሪቱ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ አስተዳደር ፡ ማናቸውንም ፡ ተካፋይነትን ፡ የማያስከትል ፡ ነው ፡ [39] ሲባል ፡ ተወሰኖ ፡ ተተርጕሟል ። ለዜጉ ፡ ዜጎች ፡ የፖሊቲካ ፡ መብቶችን ፡ በማከናወን ፡ (በመፈጸም) ረገድ ፡ እንዳንድ ፡ ገደባዎች ፡ (ወሰኖች) አሉባቸው ።

በሕገ-መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፭ ፡ መሠረት ፡ ለሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንደ ራሴዎች ፡ ዕጩዎችን ፡ ለመምረጥ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ የሚችሉ ፡ በትውልድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዦ ፡ የኾኑ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፮ ፡ መሠረት ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ በትውልዳቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዦች ፡ እንዲኾኑ ፡ እንደዚሁም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፫ ፡ መሠረት ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ አማካሪዎች ፡ በትውልዳቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዦች ፡ መኾን ፡ እንደሚገባቸው ፡ ይወስናል ። ዳኞች ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ተገዦች ፡ መኾናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜጎች ፡ [40] እንዲኾኑ ፡ እንኳ ፡ የሚያስገድድ፡ አንዳች ፡ ግዳጅ ፡ የለም ። በሕገ-መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፯ ፡ መሠረት ፡ በተወለደበት ፡ ጊዜ ፡ ወላጆቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዦች ፡ ካልኾኑ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሚኒስትር ፡ ለመኾን ፡ አይችልም ፤ ካልነበሩ ፡ የሱ ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መኾን ፡ ትርፍና ፡

---

39 እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ተካፋይነት ፡ የሚያስከትሉ ፡ መብቶች ፡ በሚያመች ፡ አኳኋን ፡ የፖሊቲካ ፡ መብቶች ፡ ተብለው ፡ ሊጠሩ ፡ ይቻላል ።

40 በፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሸል ፡ ለመኾም ፡ በለሚያስፈልጉት ፡ ግዳጆች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት፡አንቀጽ ፡ ፩፻፭ ፡ተለይተው ፡ በመመደብ ፡ ተገልጠዋል ።

ሞጋ ፣ የሌለው ፣ ጉዳይ ፣ ነው ። ይኹን ፣ እንጂ ፣ ወላጆቹ ፣ በትውልድ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜጎች ፣ እንዲኾኑ ፣ የሚያስገድድ ፣ አንድም ፣ ነገር ፣ የለ ፤ በተወለደበት ፣ ጊዜ ፣ የዜጉ ፣ እስከኾነ ፣ ድረስ ፣ ከዜጉት ፣ ወላጆች ፣ አብራክ ፣ የወጣው ፣ ልጅ ፣ ሚኒስትር ፣ ለመኾን፡ ባለመብት ፣ ነው ። በነዚህ ፣ ጉዳዮች ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ በትውልድና ፣ በዜጉ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተገዦች ፣ መካከል ፣ ምንም ፣ ዐይነት ፣ ልዩነት ፣ የለም ።

በኢትዮጵያ ፣ ተገዦችና ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ያሉ ፣ ልዩነቶች

በያንዳንዱ ፣ አገር ፣ በመብቶች ፣ መጠቀም ፣ ረገድ ፣ ጉን ፣ በግዴታዎች ፣ መፈጸም ፣ ረገድ ፣ በዜጎችና ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ልዩነቶች ፣ አሉ ። ይህም ፣ በኢትዮጵያ ፣ ያለ ፣ ዕርግጥ ፣ ነገር ፣ ሲኾን ፣ ልዩነቶቹ ፣ ጉልሕ ፣ በመኾናቸው ፣ ከባድ ፣ የኾነን ፣ የችሎታ ፣ ዐቅም ፣ ማጠር ፣ ቀንበሮችን ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ [41] ለመጫን ፣ የተሞከረ ፣ አይደለም ። ይህም ፣ መንፈስ ፣ እንደሚከተለው ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ አንቀጽ ፣ ፫፻፹፱ ፣ የተገለጠ ፣ ነው ፡-

(ፈ) በብሔራዊ ፣ መብቶች ፣ በመጠቀምና ፣ በመብት ፣ መገልገል ፣ የችሎታ ፣ ዐቅም ፣ በሚመለከተው ፣ ረገድ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ከኢትዮጵያ ፣ ተገ ዦች ፣ ጋራ ፣ በፍጹም ፣ ተቀላቅለውና ፣ በነሱም ፣ ዐድረው ፣ እንደ ፣ ኢትዮጵ ያውያኖች ፣ ይቈጠራሉ ።

(ፐ) በሥራ ፣ ላይ ፣ ሲያውሏቸው ፣ በአገሪቷ ፣ መንግሥት ፣ ወይም ፣ አስተዳደር ፣ ተካፋይነትን ፣ የማያመጡ ፣ (የማያስከትሉ) መብቶች ፣ ኹሉ ፣ ብሔራዊ ፣ መብ ቶች ፣ ተብለው ፣ ይታሰባሉ ።

(ቮ) በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ ውስጥ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ እንዲ ሠራ ፣ ፈቃድ ፣ ስለመስጠት ፣ ተወሰነው ፣ ለመውጣት ፣ የሚችሉ ፣ ልዩ ፣ ኹነ ታዎችን ፣ የሚጐዳ ፣ አንዳችም ፣ ነገር ፣ የለም ።

ቢኾንም ፣ ቅሉ ፣ አንቀጽ ፣ ፫፻፹፱ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ተገዦችና ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ልዩነት ፣ ከሚያደርጉት ፣ ሌሎች ፣ የሕገ-መንግሥቱና ፣ የሕግ ፣ (ኮድ) ውሳኔዎች ፣ ጋራ ፣ በማስተያየት ፣ ሲነበብ ፣ (ሲታይ) የሚገባው ፣ ነው ። አውራ ፡ ሕጉ ጋዊ ፡ (ወዋጅ-ወጥ ፣ ሕግ) ወሳኝነቱ ፣ ወይም ፣ ጨባጭነቱ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ በንጉሥ ነ ገሥቱ ፣ ትእዛዝ ፣ [42] መሠረት ፣ ካልኾነ ፣ በቀር ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ሊኖራቸው ፣ አይችልም ፣ በሚለው ፣ ነው ። ደግሞም ፣ ይህ ፣ ከዐምሳ ፣ ዓመት ፣ ለሚልቅ ፣ ጊዜ ፣ የመ ጠቀም ፣ ወይም ፣ ለጊዜ ፣ ሞት ፣ ለሚፈጸም ፣ [43] (ይህንኑ) መሳይ ፣ ጥቅም ፣ መብቶች ፣ ላይ ፣ የሚሠራ ፣ ነው ። የውጭ ፣ አገሩ ፣ ሰው ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ንብረት ፣ በስድስት ፣ ወራት ፣ ውስጥ ፣ ወዳንድ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ እጅ ፣ ሊያዛውር ፣ ይገባል ፤ በተቀረ ፣ ንብረቱ ፣ ተገቢው ፣ የችሎታ ፣ ዐቅም ፣ ባላቸው ፣ ባለሥልጣኖች ፣ ተይዞ ፣ እንዲሸጥ ፣ ይኾናል ። [44]

---

41 በነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ፸ኦዋሪ ፣ (ጥር) ፴፩ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም. በወጣው ፣ ፻፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም. ፍትሐ ፡ አስተዳደር ፡ ዐዋጅ ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ግፈኛና ፡ ኢርትዓዊ ፡ የኾነ ፡ ልዩነትን ፡ የሚያመጣ ፡ ማናቸውንም ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳያውሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መከልከላቸውን ፡ ማውሳቱ ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ነው ።

42 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፶፫ ። እንደዚሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የዕ ርግ ፡ ሠራተኞች ፡ መረዳጃ ፡ (ማኅበር) አባሎች ፡ ሲኾኑ ፡ አይችሉም ። በአክቶበር ፡ (ጥቅምት) ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የርግ ፡ ሠራተኞች ፡ መረዳጃ ፡ ደንጋጌ ።

43 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፶፫ ።

44 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አናቅጽ ፡ ፫፻፶፩-፮ ።

ተለይተውና ፡ ተስተካክለው ፡ ተመድበው ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጉዳይ ፡ የሚኾኑት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አናቅጽ ፡ ከ፲፱፻፱-፲፱፻፲ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

በኢትዮጵያ ፡ ተገዦችና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ሌሎች ፡ ልዩነቶች ፡ በሕገ-መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ሰፍረው ፡ ይገኛሉ ። እውነት ፡ ነው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ለምርጫ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ የፖሊቲካ ፡ ቦታ ፡ (ሥራ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት) ፡ መያዝ ፡ አለመቻላቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፵፯ ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተገዥ ፡ በማናቸውም ፡ ሙያ ፡ ተሰማርቶ ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ አለው ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፹፬ (፫) እንደሚያመለክተውም [45] ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ረገድ ፡ (ከቶ) እንደዚህ ፡ አይደለም ። ሰላማዊ ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ [46] ወይም ፡ በድፍን ፡ የንጉሥ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ያልተጨበጠ ፡ (ውሱንነት ፡ የሌለው) የመንቀሳቀስ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ [47] ኢትዮጵያዊ ፡ ተገዦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዥ ፡ ከንጉሥ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ለመሰደድ ፡ (ለቅቆ ፡ እንዲወጣ) [48] ሊገደድ ፡ አይችልም ፡ ይኸውም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የማይቸር ፡ መብት ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ለመደምደሚያ ፡ ማንኛውንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተገዥ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ (መንግሥት) ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ፤ ሌሎችን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ የሚቻለውም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ውል ፡ በመሰለው ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሰምምነት ፡ [49] እንደተገለጠው ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ከደጅ ፡ አድርጎ ፡ እዙልና ፡ ትክክለኛ ፡ የሕጎች ፡ ጠባቂነት ፡ የንግግር ፡ ነጻነት ፡ የፍትሕ ፡ ተገቢ ፡ አፈጻጸም ፡ ለንጉሥ-ነገሥቱ ፡ እቤት ፡ የማለት ፡ እና ፡ በወንጀል ፡ ለተከሰሱ ፡ የተሰጡ ፡ ዋስትናዎች ፡ የመሰለት ፡ ኹሉ ፡ ማለት ፡ ሕገ-መንግሥቱ ፡ መድን ፡ ኹኖ ፡ ያረጋገጣቸው ፡ ሌሎች ፡ መብቶች ፡ ኹሉ ፡ ለዜጎች ፡ እንደተሰጡ ፡ እንዲሁም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የተሰጡ ፡ መብቶች ፡ ናቸው ። ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘው ፡ ጉዳይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ የታደጉ ፡ (የተተዉ) [50] መኾናቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ማስፈለጉ ፡ ነው ። በደፈናው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሕጉን ፡ ምሉ ፡ ጠባቂነትንና ፡ ዜጎች ፡ አግኝተው ፡ የሚጠቀሙባቸውን ፡ አብዛኞች ፡ መብቶች ፡ ኑረዋቸው ፡ የሚጠቀሙባቸው ፡ መኾኑ ፡ ጉልሕ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ ስለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔዎች ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ መጣል ፡ ያስፈልጋል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ ስለመመዝገብ ፡ የወጣው ፡ ዐዋጅ ፡ [51] በንጉሥ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ተቀማጭ ፡ የኾኑትን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንደደረሱ ፡ (እንደገቡ) በ፴ ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ከተገቢው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ያስገድዳል ። ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ዲሬክተሩ ፡ ዘንድ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ይገባቸዋል ፤ በማንኛቸውም ፡ ሌሎች ፡ ስፍራዎች ፡ ግን ፡ ከፖሊስ ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ (አዛዥ) ዘንድ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ይገባቸዋል ። ይኸውም ፡ በዕድሜ ፡ ከዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ በኾኑት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ። ምዝገባው ፡ በያመቱ ፡ እንዲታደስ ፡ ይገባል ።

---

45 ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሥራ ፡ ፈቃዶችን ፡ ማውጣት ፡ ነክ ፡ ስለ ፡ ኾነው ፡ ሕግ ፡ በሲፕቴምበር ፡ (መስከረም ፡ በኛ ፡ ነሐሴ ፡ ነው) ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ያገኘሁት ፡ ዓ. ም. ትእዛዝ ፡ ቁ ፡ ፩፯ ፡ ምዕራፍ ፡ ፮ኛን ፡ ይመለከታል ።

46 የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፭ ።

47 የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፮ ።

48 የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

49 የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶ ።

50 የኢትዮጵያ ፡ ተገዦችና ፡ የሌሎቹ ፡ ግዴታዎች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ-መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፱ ፡ የሰፈሩ ፡ ናቸው ።

51 በኤፕሪል ፡ (ሚያዝያ) ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ያገኘሁት ፡ ዓ. ም. ዐዋጅ ፡ ፶፭ ።

ባኹኑ ፡ ጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ ስለማባረርና ፡ ስለማስወገድ ፡ የሚመለከት ፡ የተጠቃለለና ፡ የተማላ ፡ ሕግ ፡ የለም ። ማንኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የማይፈለግ ፡ ኑዋሪ ፡ (ተቀማጭ) ነው ፡ ብሎ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትሩ ፡ በወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የመኖሪያ ፡ ፈቃዱን ፡ ሊፍቅበት ፡ ለሚችለው ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያስታውቃል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስለውጭ ፡ አገር ፡ ሰውየው ፡ መባረር ፡ [52] ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትሩ ፡ አስፈላጊውን ፡ ያከናውናል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ እንቀጽ ፡ ፩፻፬፩ ፡ ወንጀሉ ፡ ተገልጦበት ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ተራ ፡ እስራት ፡ የተፈረደበትን ፡ ወይም ፡ የለመደ ፡ ሕግን-ጣሽ ፡ በመኾን ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ እንዲቈይ ፡ የተፈረደበትን ፡ ወይም ፡ ዐላፊነት ፡ ሳይሰማው ፡ (ሽውዶት) ወይም ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ ዐላፊነት ፡ እየተሰማው ፡ ሕግን ፡ መጣሱ ፡ የተለየ ፡ ዕውቀት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ (ኤክስፔርት) አስተያየት ፡ ለሕዝብ ፡ ሥርወታዊ ፡ ኑሮ ፡ (ጸጥታ) አደገኛ ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠበት ፡ [53] የውጭ ፡ አገር ፡ ሰውን ፡ ለጊዜው ፡ (ለተወሰነ ፡ ጊዜ) ብቻ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ለምንጊዜውም ፡ (ለኑባር ፡ ወይም ፡ ቋሚ) ከንጉሠ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እንዲወገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያዝዝ ፡ ይችላል ። ስለመባረር ፡ የተጠቃለለና ፡ የተማላ ፡ ሕግ ፡ ፓርላሜንት ፡ ቢሠራና ፡ እንዲባረሩ ፡ ትእዛዝ ፡ የወጣባቸው ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ እንዲታይላቸው ፡ ቢያረግ ፡ ማለፊያ ፡ ነበረ ። ድንገተኛ ፡ አጣዳፊ ፡ (አስቸኳይ) ኹኔታዎች ፡ ሲለዩ ፡ (ወይም ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ ሊኾኑ) ይችላሉ ። በምንም ፡ አኳኋን ፡ ቢኾን ፡ በወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በሚመጣው ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ሊያስባርራቸው ፡ ስለሚችሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ባኹኑ ፡ ጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንዲያውቁት ፡ አልተደረገም ፡ (አልተገለጠላቸውም) ።

እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተወላጅና ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አቋም ፡ የሚመለከተውን ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ ካወጣን ፡ ካወረድን ፡ ዘንዳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ሳይኾኑ ፡ መኳናቸውን ፡ ከዚህ ፡ ወዳደረጉት፡ ሰዎች ፡ እስቲ፡ አስተውሎአችንን፡ እናዙር።

ምህላው

የምህላው ፡ ፍች ፤- ምህላውና፡ ምቅማጥ ፡ (መቀመጫ ፡ ስፍራ) ውሱን ፡ ትርጓሜ ፡

ያንድ ፡ ሰው ፡ መቀመጫ ፡ ቦታ ፡ (ምቅማጥ) ያለበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ። በሕግ ፡ ፊት ፡ ምቅማጥ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቋሚ ፡ አድርጎ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ቦታ ፡ (ስፍራ) [54] ነው ። በኢትዮጵያ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በኖረ ፡ ጊዜ ፡ መቀመጫ ፡ ቦታውን ፡ ከዚያው ፡ እንዳደረገ ፡ [55] ይታሰባል ። ላንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ (ለምሳሌ ፡ ላጥቢያ ፡ የፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ሲባል) ምቅማጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ብሂል ፡ (ፍች) ሊኖረው ፡ ሲችል ፡ በተረፈ ፡ በጠቅላላው ፡ ሕጋዊ ፡ ንክኪ ፡ (ግንኙነት) አይደለም ።

ምህላው ፡ (መካን) ከመቀመጫ ፡ ቦታ ፡ በኹለት ፡ በዙል ፡ የተለየ ፡ ነው ። አንደኛ ፡ ምህላው ፡ ራሱን ፡ የቻለና ፡ በቂ ፡ የኾነ ፡ ፅንሰ-ሓሳብ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ዐያሌ ፡ መቀመጫ ፡ ቦታዎች ፡ ሊኖሩት ፡ ይችል ፡ ይኾናል ፡ [56] እንጂ ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡

---

52 በኢጥሪል ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፻፲፱፻፵፫ ፡ ዓ. ም. ወዋጅ ፡ ፴፯ ። ይህ ፡ ሥሩዕ ፡ የውጭ ፡ አገር-ገብ ፡ ኑዋሪን ፡ (ኢሚግራሺንን) ፡ ይዳኛል ።

53 በንደዚህ ፡ ባለው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚከታቸው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ እንዲመካከር ፡ ያስፈልገዋል ።

54 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ።

55 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ (፪) ።

56 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ (፩) ።

ሊኖረው ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ መካን ፡ [57] ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ሐሳብ ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ባንዱ ፡ (በተወሰነው) ጊዜ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ምንባር፣ ብቻ ፡ ነው ፡ እንደማለት ፡ ሊቁጠር ፡ ይገባል ። ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ እንደምናየው ፡ ዅሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንግሥታት ፡ የተለያዩ ፡ የምህላው ፡ ፅንሰ ሐሳቦች ፡ አሏቸው ። ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማድረጉን ፡ በኢትዮጵያው ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ልታየው ፡ (ልትፈታው) ስትችል ፡ ፈረንሳይ ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ ሰውዬ ፡ በፈረንሳዩ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ [58] ምህላዉን ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እንዳደረገ ፡ አድርጋ ፡ ልትመለከተው ፡ ትችላለች ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ መጣኝ ፡ ኹኔታዎችን ፡ በመገንዘብ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ምህላው ፡ ብቻ ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ። ዅለተኛ ፡ ምህላው ፡ ቋሚነትን ፡ (ነባርነትን) ጠባይን ፡ ይከታል ፡ (ያመለክታል) ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚቀመጥበት ፡ እና ፡ "በነባርነት ፡ (የምንጊዜም)" — የተለያዩ ፡ ፍችዎች ፡ (ትርጒሞች) ያሉት ፡ ቃል ፡ ነው — ከዚያ ፡ ለመኖር ፡ ዐቅዶ ፡ ጥቅሞቹን ፡ ያቋቋመበትና ፡ ያሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሐሳብን ፡ ለማጠቃለል ፡ ምህላው ፡ "በነባርነት ፡ (ቋሚ ፡ በኾነ ፡ አኳኋን)" ከዚያው ፡ ለመኖር ፡ ዕቅድ፡ ጋራ ፡ የተጋባ ፡ ባንድ ፡ የተለየ ፡ ቦታ ፡ መቀመጥን ፡ ያስፈልገዋል ፡ ማለት ፡ እንችላለን ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ምህላው ፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፫ ፤ "ያንዱ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ቋሚ ፡ በኾነ ፡ አኳኋን ፡ ከዚያው፡ ለመኖር፡ በማቀድ፡ የተግባሩን [59] ፡ እና ፡ የጥቅሞቹን፡ አውራ ፡ መቀመጫ ፡ ያቋቋመበቱ ፡ ቦታ ፡ ነው" ይላል ። በዚህ ፡ ንግግር ፡ አሰካኩና ፡ አቀማመጡ ፡ "ነባርነት ፡ (ወይም ፡ ቋሚ ፡ ወይም ፡ ምንጊዜም)" የሚለውን ፡ ቃል ፡ አፍታቶ ፡ መወሰንና ፡ መተርጐም ፡ ስለሚገባን ፡ "በነባርነት" የሚለው ፡ ቃል ፡ "ያልተወሰነ ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ጊዜ" ተብሎ ፡ እንዲፈታ ፡ ተደርጓል ። "ለመመለስ ፡ ያልተረጋጋ ፡ (የሚሰፍፍ) ዕቅድ" ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ የሚችለው ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ መካኑን ፡ ከዚህ ፡ ከማድረግ ፡ ለማገድ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዲኾን ፡ አያስፈልግም ። ለምሳሌ ፡ ያኽል ፡ ቤተሰቡን ፡ እንደያዘ ፡ አንድ ፡ ግሪክ ፡ ነጋዴ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይመጣና ፡ ከበድ ፡ ያለና ፡ የጐላ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ ሀብት ፡ (ካፒታል) ባንድ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ይከታል ፡ (ያገባል) ብለን ፡ እስቲ ፡ እናስብ ። ቢቃኝ ፡ ብሎ ፡ በፈቃዱ ፡ ከሠርክ ፡ ሥራው ፡ ተለይቶ ፡ በሚያርፍበት ፡ ሰዓት ፡ (ሪታየር) ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ለመመለስ ፡ ያቅዳል ። ያቀደው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ለመቈየት ፡ ስለኾነ ፡ ምንባሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደኾነ ፡ ይገመት ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ።

---

57 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፭ ።

58 ስላንዱ ፡ ሰው ፡ ምህላው ፡ እያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ በራሱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንዲወሰን ፡ ይገባዋል ። በኮኪኖስ ፡ እና ፡ በክኪኖስ ፡ መካከል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍ. ፭፻፫፭/፶፪ ፡- "በግሪክ ፡ ሕግ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ በግሪክ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፬ ፡ መሠረት ፡ መካኑን ፡ በኢትዮጵያ፡ እንዳደረገ ፡ ሰው ፡ የመቍጠሩ ፡ ህልው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ መካኑን ፡ በዚህ ፡ እንዳደረገ ፡ ሰው ፡ መቈጠሩን ፡ የሚያመለክት ፡ አይደለም ። ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ይህን ፡ ይዘት ፡ ሊቁርጥ ፡ የሚችለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡" ሲል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አመልክቷል ። ደግሞም ፡ አኔስሌይን ፡ በሚመለከተው ፡ (፲፱፻፳፭) ፩ ፡ ቻንሴሪ ፡ ፭፻፶፮ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የፈረንሳይ ፡ ምህላው ፡ እንዳገኘ ፡ ባይገመትም ፡ ቅሉ ፡ በብሪታንያ ፡ የመካን ፡ ፅንሰ-ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የብሪታንያ ፡ (እንግሊዝ) ተገዥ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያውን ፡ በፈረንሳይ ፡ አድርጓል ፡ ሲል ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወሰነውን ፡ ይመለከታል ።

59 "ተግባር" የተባለው ፡ ቃል ፡ አገባብ ፡ ሥራ ፡ ሰምሪት ፡ ተብሎ ፡ እንዲፈታ ፡ ያስፈልጋል ።

ይህ ፡ የመካን ፡ አተረጓጐም ፡ እንደሚከተለው ፡ በተነገረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፬ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ፡-

"(፩) ያንዱ ፡ ሰው ፡ ደንበኛ ፡ መቀመጫው ፡ ባንዱ ፡ ስፍራ ፡ በሚኾንበት ፡ ላይ ፡ በዚያው ፡ ስፍራ ፡ በነባርነት ፡ ለመቀመጥ ፡ ዐቅዷል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

(፪) በቂና ፡ አጥጋቢ ፡ በኾነ ፡ ቍርጥ ፡ ባለ፡ ትክክለኛ ፡ መልክ ፡ እና፡ በተለመደው፡ ደንበኛ ፡ የነገሮች ፡ መንገድ ፡ መሠረት ፡ የነገሩ ፡ መኾን ፡ ውጤትን ፡ የሚያገኝ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ይኸው ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ የገለጠው ፡ ተቃራኒ ፡ ሐሳብ ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አይገመትም ።"

ለምሳሌ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ያምስት ፡ ዓመቱ ፡ ውል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ካገር ፡ ለመውጣት ፡ ዐቅዶ ፡ በዐምስት ፡ ዓመት ፡ ውል ፡ ለመሥራት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣ ፡ እንደኾነ ፡ መቀመጫውን ፡ በዚሁ ፡ ቢያደርግም ፡ ቅሉ ፡ ምህላውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አደረገ ፡ አይባልም ። ዕቅዱ ፡ በቂና ፡ አጥጋቢ ፡ በኾነ ፡ መልክ ፡ የተስተካከለ ፡ ስለኾነ ፡ የተረጋገጠው ፡ ኹኔታ ፡ ማለት ፡ ያምስቱ ፡ ዓመት ፡ ውል ፡ መፈጸም ፡ በሚደርስበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከናወን ፡ ነው ። በሻቶ ፡ እና ፡ በሻቶ ፡ መካከል ፡ በነበረው ፡ ነገር [60] ፡ የንጉሥ-ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አናቅጽ ፡ ፩፻፹፫ን ፡ እና ፡ ፩፻፹፬ን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አስተባብሮ ፡ በመተርጐም ፡ "በነባርነት" ማለት ፡ ላልተወሰነ ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ውሳኔውን ፡ ደመደመ ። ምህላዉ ፡ ያጠያየቀው ፡ ሰውዬ ፡ "ያደን ፡ ወይም ፡ የስፖርት ፡ ጉዞ ፡ አስተናባሪና ፡ አሰናጅ" (ሳፋሪ ፡ አውትፊቴር) በመኾን ፡ የግል ፡ ሥራውን ፡ (ተግባሩን) በዚሁ ፡ የሚያካኺድ ፡ እና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለስድስት ፡ ዓመታት ፡ የተቀመጠ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። አንድ ፡ ቀን ፡ አገሪቱን ፡ ለቅቆ ፡ ለመኼድ ፡ የሚችል ፡ (የአሜሪካ ፡ ዜጋ ፡ ስለነበረ) ነው ፡ በማለት ፡ (አንዱ ፡ አባል ፡ ዳኛ ፡ ሲለይ) የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጋብቻ ፡ ፍቺ ፡ የማጽደቅ ፡ እቤቱታውን ፡ ከለከለው ። ስለዚህ ፡ "በነባርነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመኖር ፡ አላቀደም ፡" ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ቈረጠ ። ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በመገልበጥ ፡ የንጉሠ-ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ "መጪውን ፡ ጊዜ ፡ አጥብቆና ፡ አትኵሮ ፡ አስቀድሞ ፡ በመመልከቱ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫው ፡ በርግጡ ፡ ተሳስቷል" ሲል ፡ በየነ ። በኢትዮጵያ ፡ ስለሚቀመጥና ፡ ሥራውን ፡ በዚሁ ፡ ስላደረገ ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፹፬ ፡ እምነት ፡ (ሐሳብ) ከሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል ። ተቃራኒውን ፡ ዕቅድ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጉልሕ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ ዘንዳም ፡ የታወቀው ፡ ወይም ፡ የተገለጠው ፡ እምነት ፡ ስለማይታጠፍ ፡ (ስለማይፋቅ) መካኑን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዳደረገ ፡ ሰው ፡ ይቈጠራል ። ኢትዮጵያ ፡ ለዋቂት ፡ ዘመናት ፡ ኑሮ ፡ የነበረውና ፡ ተግባሩን ፡ በዚሁ ፡ አቋቁሞ ፡ የነበረው ፡ የግሪክ ፡ ዜጋን ፡ ነክ ፡ የኾነው ፡ የዚሶስ ፡ እና፡ ዚሶስ፡ ነገርም [61] ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ ያገኘ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ወደ ፡ ምህላው ፡ አቀራረብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በፓስቶሪ ፡ እና ፡ በአስላኒዲስ ፡ መካከል ፡ በተነሣው ፡ ነገር [62] ፡ የንጉሥ-ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የበየነው ፡ እንደሚያስረዳው ፡ ቀድሞ ፡ ከነበረው ፡ አቀራረብ ፡ ጋራ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ነው ። መካኑን ፡ የተጠያየቁበት ፡ ሰውዬ ፡ በ፲፱፻፲ ፡ ዓ. ም. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ ነበረ ። ሥራውን ፡ ከዚሁ ፡ ያቋቋመና ፡ በዚሁ ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር፡

---

60 በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮሉም ፡ ፩ ፡ ቍ. ፪ ፡ ገጽ፡ ፩፻፲ ፡ የወጣው ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍ. ፩፻፹፩/፶፭ ።

61 የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍ. ፩፻፹፫/፶፭ ።

62 የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍ. ፩፻፹፭/፶፭ ።

ዐያሌ ፡ ጕብኝቶችን ፡ አድርጎና ፡ በጣም ፡ ሲታመም ፡ ወደዚያው ፡ የሼደ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ከዳነም ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሶ ፡ ነበረ ። ከመሐላ ፡ ኦዛዜው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሳይኾን ፡ በግሪክ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ስለሚኾን ፡ እና ፡ እሱ ፡ ራሱም ፡ በዐዲስ ፡ አበባው ፡ የግሪክ ፡ ቆንሲል ፡ እንዲተዳደር ፡ ስለመራ ፡ በግሪክ ፡ ሕግ ፡ እንዲዳኝ ፡ ያቀደው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ (ፍርድ ፡ ቤቱ) ጕዳዩን ፡ ቂረጠ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መካኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልነበረም ፡ ሲል ፡ ወሰነ ። እንዱ ፡ ሰው ፡ መካን ፡ ለማግኘቱ ፡ ወይም ፡ ላለማግኘቱ ፡ መመጠኛው ፡ (መፈተኛው) ‘‘ከትውልድ ፡ አገሩና ፡ ከሕጎቹ ፡ ከልማዱ ፡ ዅሉ ፡ ራሱን ፡ በፍጹም ፡ በሚገነጥል ፡ መልክ ፡ ለይቶ ፡ ዐዲሱን ፡ አገር ፡ ቋሚ ፡ ቤቱ ፡ (ሀገሩ) ለማድረግ ፡ ወቅዶ ፡ የግል ፡ ሕግ ፡ ጕዳይን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ነባር ፡ በኾነ ፡ እኳኋን ፡ ላዲሱ ፡ አገር ፡ ሕጎችና ፡ ልማዶች ፡ ራሱን ፡ ተገዥ ፡ ለማድረግ ፡ በማቀዱ ፡ ላይ ፡ ነው ፡’’ አለ ። ብሪታንያዊውን ፡ አቀራረብ ፡ በመከተል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚከተለውን ፡ አጥብቆ ፡ አረጋገጠ ፦-

(፩) የመቀመጥ ፡ ጊዜ ፡ ርዝማኔ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የማያጠርጥ ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ የምህላዉ ፡ መለወጥን ፡ (ሐሳብ) ለማምጣት ፡ (ለማስከተል ፡ ወይም ፡ ለማቋቋም) በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ፤

(፪) የምህላው ፡ ለውጡ ፡ በጦልሕ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ሲገባው ፡ እንዲሁም ፡ ከምህላው-ትውልድ ፡ በመለወጥ ፡ ጕዳይ ፡ ለማረጋገጥ ፡ (ለማሳየት) የሚያስፈልገው ፡ ማስረጃ ፡ በምርጫ ፡ (በፈቃድ) ምህላው ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ማስረጃ ፡ የላቀና ፡ የበለጠ ፡ ከብደት ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። ሰውዬው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የምርጫ ፡ (የፈቃድ) መካን ፡ ማግኘቱን ፡ የሚያሳይ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አልነበረም ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጕዳዩን ፡ ደመደመ ። በዚህም ፡ ላለ ፡ ያንኑ ፡ ‘‘የግሪክ ፡ አናዎር ፡ መንገድን’’ ሳያቋርጥ ፡ በመቀጠሉ ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለማግኘት ፡ ዐሳብ ፡ (ዕቅድ) አልነበረውም ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አጥብቆ ፡ አረጋገጠ ።

በሕጉ ፡ (ኮዱ) መሠረት ፡ ውጤቱ ፡ በጦልሕ ፡ የተለየ ፡ ይኾናል ። ሰውዬው ፡ ዅለቱንም ፡ የተግባር ፡ ስምሪቱንና ፡ የሠርክ ፡ የተለመደ ፡ ደንበኛ ፡ ምቅማጡን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እድርጎ ፡ የነበረ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የሚታመነው ፡ መካኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መኾኑ ፡ ነው ። የተባለው ፡ ቢባል ፡ (እንዲያው ፡ ዘልሎ ፡ ተስፋ ፡ ቢደረግ) እንኳ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ የመመለሱ ፡ ዕቅድ ፡ ‘‘የሚጎላፍ ፡ (የነሲብ)’’ ነበረ ፡ ዅነታው ፡ በመድረሱ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ የሚመለስበት ፡ የተቈረጠ ፡ ዅነታም ፡ አልነበረም ። እንዲያውም ፡ ከዚሁ ፡ ዐረፈ ፡ (ሞተ) ። ስለዚህ ፡ በነባርነት ፡ ከዚሁ ፡ ለመኖር ፡ የማቀዱን ፡ እምነት ፡ የሚፍቅ ፡ አንድም ፡ ማስረጃ ፡ አይኖርም ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ቢኾን ፡ ኑሮም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰው፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዳደረገ ፡ በተቈጠረ ።

የሕጉ ፡ (ኮዱ) መደቦች ፡ (ክፍሎች) ፩፤፪፪ ፡ እና ፡ ፩፤፪፬ ፡ እና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ያኖሩባቸው ፡ ትርጕሞች ፡ እንደሚያስረዱት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዚሁ ፡ በኖረና ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ መካኑን ፡ እንዲያገኝ ፡ የኢትዮጵያው ፡ መሠረተ-ሐሳብ ፡ ይመርጣል ፡ (ይፈቅዳል) ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ በዚሁ ፡ የሚቀመጡ ፡ እና ፡ የተግባር ፡ ስምሪታቸውን ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ስምሪታቸውን ፡ በዚሁ ፡ ያደረጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የጠራ ፡ እና ፡ የተስተካከለ ፡ ተቃራኒ ፡ ዕቅድ ፡[63] ከሌለ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መደበኛ ፡ ነዋሪዎች ፡ ይቈጠራሉ ።

በስተሌላ ፡ በዙል ፡ ደግሞ ፡ አስፈላጊው ፡ ዕቅድ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ በዚሁ ፡ መካንን ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ላንድ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የተቈረጠ ፡ የጊዜ ፡ ልክ ፡ ከዚህ ፡ እንዲያላ

---

63 የኢትዮጵያ ፡ ምህላው ፡ ለማግኘት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ሥነ-ሥርዐቶች ፡ አያስፈልጉም ።

ልፍ ፡ መግባትን ፡ ሕጉ ፡ (ኮዱ) አያስፈልገውም ። ምናልባት ፡ በዋይት ፡ እና ፡ በቴንአንት ፡ መካከል ፡ [64] እንደነበረው ፡ ነገር ፡ በመሰለው ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከዚ ያው ፡ ጉዳዩን ፡ ከቄሬጠው ፡ የአሜሪካ ፡ ክፍለ-ሀገር ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከደረሰበት ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ ይደርሱ ፡ ይኾናል ። ምህላዉ ፡ ያከራከረው ፡ ሰውዬ ፡ ቤቱን ፡ በ'ሀ' ግዛት ፡ (መንግሥት) ሺጦ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ 'ለ' ግዛት ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ ቤት ፡ ኼደ ። ከዚያም ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረትን ፡ ወደ ፡ 'ለ' ግዛት ፡ አስተላልፎ ፡ (አጓጉዘ) ነበረ ። ሚስቱ ፡ ስትታመም ፡ (ታምማ ፡ ስትወድቅ) በ'ለ' ግዛት ፡ የቄየው ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ነው ። ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ 'ለ' ግዛት ፡ ለመመለስ ፡ ስላቀደ ፡ ከዘመ ዶች ፡ ጋራ ፡ ወደምትቄይበት ፡ ግዛት ፡ 'ሀ' ወሰዳት ። ጤናዋ ፡ ሲሻሻል ፡ ሚስቲቱም ፡ ወደ ፡ 'ለ' ግዛት ፡ እንድትመለስ ፡ ዐስቧል ። ባልየው ፡ በ'ሀ' ግዛት ፡ እንዳለ ፡ በድንገት ፡ ዐረፈ ። በ'ሀ' ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መካኑን ፡ በ'ለ' ግዛት ፡ አማኝቷል ፡ ሲባል ፡ ተበየነ ። ምቅማጥ ፡ ከዚያው ፡ ነበረው ፡ በግዝፈተ-ሥጋው ፡ ከዚያው ፡ ነበረ ፡ በነባርነት ፡ ከዚ ያው ፡ ለመኖር ፡ ዐቅዶ ፡ ነበረ ። አንደኛው ፡ ሳይነሣ ፡ የተደረበ ፡ ተገጣጣሚ ፡ እንድላይ ፡ የኾነ ፡ ምቅማጥ ፡ እና ፡ በነባርነት ፡ ከዚያው ፡ ለመኖር ፡ ዐሳብ ፡ ነበረ ። በሕጉ ፡ (ኮዱ) መሠረት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መቀመጫውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማድረግ ፡ የሚጣልበት ፡ ማንኛቸውም ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ግዴታ ፡ ስለሌለ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ቢኾን ፡ ቅሉ ፡ ከንዚ ያው ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ ይደረስ ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ሰውየው ፡ የተወሰነና ፡ የተለየ ፡ የሠርክ ፡ መኖ ሪያ ፡ ስፍራ ፡ እንዲኖረው ፡ የሚያስፈልግበት ፡ አንዳችም ፡ ግዴታ ፡ የለም ። በሕጉ ፡ አን ቀጽ ፡ ፩፻፫፯ ፡ መሠረት ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ዐያሌ ፡ ምቅማጦች ፡ ሊኖሩት ፡ ይችላሉ ። "ባንዱ ፡ ስፍራ ፡ ደንበኛ ፡ ምቅማጥ" የተባለው ፡ የንግግር ፡ አገባብ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፫፯ ፡ እንደ ፡ ተጠቀመበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ምቅማጥን ፡ ከማመልከት ፡ ይልቅ ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ ምቅማጥን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማድረግን ፡ እንዲያመለክት ፡ ያስፈልጋል ። እንግዲህ ፡ በያንዳንዱ ፡ ስፍራ ፡ በሆቴሎች ፡ እየተቀመጠ ፡ ባንዱ ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ በሌላው ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በጉንደር ፡ እና ፡ ባንደኛው ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በጂማ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የተቀመጠ ፡ እንደኾነ ፡ በንጉሥ-ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በማንኛቸውም ፡ ክፍል ፡ [65] ቋሚ ፡ ወይም ፡ ነባር ፡ ምቅማጥ ፡ ባይኖ ረውም ፡ ቅሉ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዳደረገ ፡ ይታሰባል ።

---

64 ፴፩ ፡ ምዕራብ ፡ ቨርጂኒያ ፡ ሬፖርቴር ፡ (መግለጫ) ፭፻፲፯ ፡ ፳ ፡ ሌባዊ ፡ (ደቡብ-ምሥራቃዊ) ሬፖርቴር ፡ (መግለጫ) ፭፻፲፮ ፡ (፲፰፻፹፰) ።

65 ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚያስከትሉ ፡ ነገሮች ፡ እና ፡ በዚያው ፡ ግዛት ፡ መካንን ፡ ያገኘ ፡ ሰውን ፡ ስለመ ደገፍ ፡ በማርክስ ፡ እና ፡ በማርክስ ፡ መካከል ፡ ፸፭ ፡ የፌዴራል ፡ ሬፖርቴር ፡ (ዩ. ኤስ. ተዝዚሪ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቱኔሲ) ፻፻፳፭ ፡ (፲፰፻፹፮) የነበረውን ፡ እና ፡ በሞናንስ፡ እና፡ በሞናንስ፡ መካከል፡ ፭፻፸፭ ፡ ማሳቹሴትስ ፡ ሬፖርትስ ፡ ፻፻፱፰ ፡ ፶፭ ፡ መሰናዊ ፡ (ሰሜን-ምሥራቃዊ) ሬፖርቴር ፡ ፫፻፶፬ (፲፱፻፲፩) ይመለከቷል ።

የሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፫፯ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ የጥሪ ፡ (የባሕርይ) ሙያ ፡ ሥራውን ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሲፈጸም ፡ እና ፡ የቤተሰብ ፡ ወይም ፡ የወብሮ-ንጅሮ ፡ (ሶሺያል) ሕይወቱን ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሲያሳልፍ ፡ አጠራጣሪ ፡ ኹነታ ፡ ቢነሣ ፡ ምህላዉ ፡ በኋለኛው ፡ ስፍራ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፡ ይላል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ኹናቴ ፡ መካኑን ፡ ያከራከረው ፡ ሰው ፡ የተግባር ፡ ሥራው ፡ በ'ሀ' ግዛት ፡ ኹኖ ፡ ከነቤተሰቡ ፡ የሚኖረው ፡ በ'ለ' ግዛት ፡ የቮነበት ፡ ጉዳይ ፡ ኹሰት ፡ የአሜሪካ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ አጋጥመውዋቸው፡ ነበረ ። የ'ሀ' ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምህላዉን ፡ በዚያው ፡ ያደረገ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በዶ ራንስ ፡ መሬት ፡ ፭፻፲፩ ፡ ኒው ፡ ጀርሲ ፡ ኤዡይቲ ፡ (ርትዕ) ሬፖርትስ ። ፱፻፸፭ ፡ ፭፻፸ ፡ አትላን ቲክ ፡ ሬፖርቴር ፡ ፭፻፭ ፡ (፲፱፻፹፱) ጉዳይ ፡ ወሰነ ፤ የ'ለ' ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መካኑ ፡ በ'ለ' ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በዶራንስ ፡ መሬት ፡ ፫፻፱ ፡ ፔንሲልቬንያ ፡ ሬፖርቴር ፡ ፭፻፭፭ ፡ ፭፻፭፫ ፡ አትላ ንቲክ ፡ ሬፖርቴር ፡ ፫፻፫፡ (፲፱፻፹፱) ጉዳይ ፡ ወሰነ ። በኢትዮጵያ ፡ ጉዳዩ ፡ በጉልሕ ፡ ኹነታ ፡ በአን ቀጽ ፡ ፩፻፫፯ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተብራርቶ ፡ የተቄረጠ ፡ ነው ።

በአናቅጽ ፡ ፩፻፹፫ ፡ እና ፡ ፩፻፹፬ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ዐሳብ ፡ ምህላው ፡ ማፍራት ፡ ከመባል ፡ (ከመኾን) ይልቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመኖር ፡ ማሰብ ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ። እነዚህ ፡ መደቦች ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ በርግጡ ፡ ከሌላ ፡ ማንኛቸውም ፡ ስፍራ ፡ ሊኖር ፡ በቀላሉ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ በዚሁ ፡ በመከራዬት ፡ መካንን ፡ እንዳያገኝ ፡ ያግዱታል ፡ (ይከለክሉ ታል) ። በኪርቢ ፡ እና ፡ በቻርልስተን ፡ ከተማ ፡ መካከል ፡ እንዶተነሣው ፡ ባለንገር ፡ የቀረበውን ፡ ኹነታ ፡ ያስተውሏል ። ለሕጋዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ሲባል ፡ ወገኑ ፡ በ'ሀ' ግዛት ፡ ምህላውን ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ ። ከዚያው ፡ ያንድ ፡ ሆቴል ፡ ክፍል ፡ ይከራይ ፡ እንጂ ፡ አልተጠቀመበትም ፡ (አልኖረበትም) ፡ በ'ለ' ግዛት ፡ ባለው ፡ ቤቱ ፡ መኖሩን ፡ ቀጠለ ። በ'ሀ' ግዛት ፡ ለመኖር ፡ ምኞት ፡ (ሐሳብ ፡ ወይም ፡ ዕቅድ) ከቶ ፡ ስላልነበረው ፡ መካኑ ፡ በ'ለ' ግዛት ፡ እንደኾነ ፡ ቀርቷል ፡ ሲባል ፡ ተወሰነ ። በንደዚህ ፡ ባለው ፡ አኳኋን ፡ በነባርነት ፡ በዚሁ ፡ ለመኖር ፡ ምንም ፡ ሐሳብ ፡ ስላልነበረ ፡ በሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ ከንደዚሁ ፡ ካለው ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ ይደረሳል ።

አንቀጽ ፡ ፩፻፹፯ ፡ ላለመመለስ ፡ ዐቅዶ ፡ የቀድሞውን ፡ ምህላዉን ፡ ይልቀቅ ፡ እንጂ ፡ ዐዲስ ፡ መካኑን ፡ ገና ፡ ባላገኘ ፡ ሰው ፡ የሚነሣውን ፡ ችግር ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። አንድ ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አድርጎ ፡ የነበረ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ተመልሶ ፡ በነባርነት ፡ ከዚያው ፡ ለመኖር ፡ ይወሰን ፡ እስቲ ፡ እንበል ። ኢትዮጵያን ፡ ለቅቆ ፡ ይኼዳል ፡ ግን ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ሳይደርስ ፡ ይሙት ፡ እንበል ። እንግዲህ ፡ ጣጣው ፡ በጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያው ፡ የት ፡ መኾኑ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ መካኑን ፡ ለቅቋል ፡ ግን ፡ በግዛፈተ-ሥጋው ፡ (በባሕርይው) ከዚያ ፡ ስላልነበረ—ዕቅድ ፡ ወይም ፡ ዐሳብና ፡ በባሕርይ ፡ መገኘት ፡ አልተጋጠሙም ፡ ማለት ፡ ነው — የግሪክ ፡ ምህላውን ፡ ገና ፡ አላ ገኘም ። በንደዚህ ፡ ያለ ፡ አጋጣሚ ፡ ኹነታ ፡ ብሪታንያዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሰውየው ፡ የጥንቱን ፡ መካኑን ፡ ማለት ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ምህላው[67] ፡ እንደገና ፡ መልሶ ፡ ያገኛል ፡ ሲሉ ፡ ይበይናሉ ፡ (ያምናሉ) ። ይኸውም ፡ ብዙ ፡ ብሪታንያውያን ፡ መካናቸውን ፡ በቅኝ ፡ ግዛቶቹ ፡ አድርገው ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በርጅና ፡ ዘመናቸው ፡ ወደትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ከነበረበት ፡ ከቅኝ ፡ ዘመናት ፡ ጊዜ ፡ የቄየ ፡ ቅሬት ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ። እንደዚያ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ ምህላዉ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ኹኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደኾነ ፡ የመሬት ፡ (ርስት) ንብረቱን ፡ አከፋፈልን ፡ የሚወስነው ፡ ከቅኝ ፡ ግዛቱ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ የብሪታንያዊው ፡ ሕግ ፡ ነው ። በስተሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የአሜሪካ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዐዲሱን ፡ እስቲያገኝ ፡ ድረስ ፡[68] የቀድሞ ፡ መካኑን ፡ እንደያዘ ፡ ይቄያል ፡ ሲሉ ፡ ይወስናሉ ። ኢትዮጵያ ፡ የኋለኛውን ፡ አቀራረብ ፡ ትከተላለች ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፯ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ምህላዉን ፡ አስተሚያደርግ ፡ ድረስ ፡ ምንባሩን ፡ ባቋቋመበት ፡ ቦታ ፡ ያለውን ፡ እንደያዘ ፡ ይቄያል ።

ያገባች ፡ ሴት ፡ ጋብቻው ፡ ጸንቶ ፡ እስከቄየ ፡ ድረስ ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ውሱን ፡ በመኾን ፡[69] ያልተወሰነ ፡ (ያልተነካ) ካልኾነ ፡ በቀር ፡ የባሏ ፡ ምህላው ፡ ይኖራታል ፤ የተለየ ፡ ምቅማጥ ፡ ለማግኘት ፡[70] ብትችልም ፡ ቅሱ ፡ የተለየ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡

---

66 ሟቹ ፡ አትላንቲክ ፡ ሬፖርቴር ፡ ፩፻፸፩ ፡ (ኒው ፡ ሐምፕሼር ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፲፮) ።

67 በውድኒ ፡ እና ፡ በውድኒ ፡ መካከል ፡ (፲፩፻፷፰) ሕግ ፡ ሬፖርትስ (መግለጫዎች) ፡ ፩ ፡ ኤስሲ. እና ፡ ዲቪ. ፩፻፹፩ ።

68 በጆንስ ፡ ጉዳይ ፡ ፩፻፶፪ ፡ አይኦዋ ፡ ሬፖርትስ፡ ፭፷ ፡ ፩፻፹፪ ፡ ባሕራዊ ፡ (ሰሜን-ምዕራባዊ) ሬፖርቴር ፡ ፪፻፴፯ ፡ (፲፱፻፴፭) ።

69 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፱ ።

70 በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ እና ፡ በሌላ ፡ ጥቂት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ ዝንባሌ ፡ ጋብቻው ፡ በሚቆየልበት ፡ ጊዜም ፡ እንኳ ፡ ሚስቲቱ ፡ የተለየ ፡ መካን ፡ እንድታገኝ ፡ መፍቀዱ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ምህላው ፡ አቀራረቢ ፡ እንደዚያው ፡ ወደ ፡ ዘግነት ፡ አቀራረቢ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ለማግኘት ፣ [71] አይቻላትም ። ራሱን ፣ ገና ፣ ነጻ ፣ ያላወጣ ፣ ኢአኪል ፣ የጠባቂው ፣ ምህ ላው ፣ [72] ይኖረዋል ። እሱም ፣ ቢኾን ፣ ቅሉ ፣ የተለየ ፣ ምቅማጥ ፣ ሊኖረው ፣ (ሊያገኝ) [73] ይችላል ። አንድ ፣ እክብ (በፍርድ ፣ የተወሰነ ፣ ሰው) በታከበበት ፣ (በተወሰነበት) ጊዜ ፣ [74] የነበረውን ፣ መክን ፣ ይይዛል ፤ ምንም ፣ እንኳ ፣ እሱም ፣ ቢኾን ፣ የራሱን ፣ ግል ፣ ምቅማጥ ፣ [75] ሊያገኝ ፣ (ሊኖረው) ቢችል ፣ ቅሉ ።

ለማጠቃለል ፣ ያኸል ፣ የኢትዮጵያ ፣ ምንባርን ፣ ስለማግኘት ፣ ሕጉ ፣ በጣም ፣ ጕልሕ ፣ ነው ። ግልጥ ፣ በኾነ ፣ ማስረጃ ፣ በተቃራኒ ፣ ዕቅድ ፣ እምነቱ ፣ ካልተ ሻረ ፣ እና ፣ ከኢትዮጵያ ፣ መልቀቃቸውም ፣ ሊደርስ ፣ በሚችል ፣ ዅነታ ፣ የታጀበ ፣ ካልኾነ ፣ በቀር ፣ ደንበኛ ፣ ምቅማጣቸውን ፣ በዚሁ ፣ ያደረጉ ፣ ሰዎች ፣ ምንባራቸውን ፣ በዚሁ ፣ ያደረጉ ፣ ናቸው ፣ ተብሎ ፣ ይታመናል ። ይህም ፣ ማለት ፣ ላልተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ከዚሁ ፣ የሚኖሩና ፣ የሚሠሩ ፣ ሰዎች ፣ በኢትዮጵያ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ዘንድ ፣ ምንባራቸውን ፣ ከዚሁ ፣ እንዳደረጉ ፣ ይቁጠራሉ ፣ ነው ። ሕጉ ፣ ግልጥ ፣ የሚኾንበት ፣ ህል ው ፣ (ርግጠኛ ፣ ጕዳይ) ፣ እኹን ፣ እስተውሎአችኁን ፣ ወደምንመልስበት ፣ ነገር ፣ ወደ ሚዳኘው ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ ጕዳዮችን ፣ በሚወስኑት ፣ ነገሮች ፣ ላይ ፣ ትልቅ ፣ የኾነ ፣ ተገቢ ፣ ትርጕም ፣ አለው ።

የተለይ ፣ ግላዊው ፣ ሕግ ፣

<u>የችግሩ ፣ (የፐሮብሌሙ) ጠባይ ፣</u>

በሕጋዊ ፣ ዝግጅቶች ፣ ዅሉ ፣ አንዳንድ ፣ ጕዳዮች ፣ በግል ፣ የተለይ ፣ ሕግነት ፣ ይከለ ላሉ ፣ (ይወሰናሉ) ። የግል ፣ የተለይ ፣ ሕግ ፣ ስንል ፣ ያንዱ ፣ አገር ፣ (መንግሥት) ነጠላው ፣ ግላዊ ፣ ሰው ፣ አንዳንድ ፣ ግንኙነቶችን ፣ በመምሥረት ፣ የተሳሰራቸው ፣ ግለታችን ፣ ነው ። የሰውን ፣ እቋም ፣ ጕዳዮችን — ግለት ፣ ለማግባት ፣ የችሎታ ፣ መብት ፣ አለውን ፣ የልጆቹ ፣ መብቶች ፣ እነየቱ ፣ ናቸውን ፣ እና ፣ መሰል ፣ ጕዳዮች ፣ የኾኑትን — ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዲወሰን ፣ ይገባዋል ። እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ ነገሮችን ፣ የሚወስነው ፣ ሕግ ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕጉ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። በብዙ ፣ አገሮች ፣ የተለይ ፣ የኾነው ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ የተንቀሳቃሽ ፣ ሀብት ፣ (ንብረት) ውርሻ ፣ ጕዳዮችን ፣ ዅሉ ፣ ይወስናል ። በግላዊ ፣ የተ ለይ ፣ ሕግ ፣ የሚወሰኑት ፣ ጕዳዮች ፣ በያንዳንዱ ፣ አገር ፣ (መንግሥት) የግል ፣ ኢንቴርና ሺናላዊ ፣ ሕግ ፣ ደንቦች ፣ ወይም ፣ እንዳንዴ ፣ የሕጎች ፣ ግጭቶች ፣ ተብለው ፣ በሚጠ ሩት ፣[76] ውስጥ ፣ ይገኛሉ ። ለተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ ለምሳሌ ፣ ያኸል ፣ ያገሩ ፣ ዜጋ ፣ የኾ ነው ፣ ሰው ፣ ያገሩ ፣ ሕግ ፣ ወይም ፣ ሰውየው ፣ መደበኛ ፣ ኑዋሪ ፣ ለኾነበቱ ፣ አገር ፣ ሕግ ፣ የሚመለከቱትን ፣ የሚወስነው ፣ ሕግ ፣ ነው ።

ባለንበት ፣ ባኹኑ ፣ ጊዜ ፣ የግል ፣ ኢንቴርናሺናል ፣ ሕግ ፣ ያልተዘጋጀ ፣ በመኾኑ ፣ ህልው ፣ ችግሩ ፣ በኢትዮጵያ ፣ የተጠናጠነ ፣ ዅኗል ። ስለግላዊ ፣ ኢንቴርናሺናላዊ ፣ ሕግ ፣

---

71 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፫፰ ።

72 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፯።

83 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፫፰ ።

74 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፯።

75 የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፫፰ ።

76 <u>ኢንፍራ</u> ፡ (ዝቅ ፣ ብሎ) እንደምናየው ፣ በኢትዮጵያ ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ ያጽምንና ፣ የተንቀሳ ቃሽ ፣ ሀብት ፣ ውርስ ፣ ጕዳዮችን ፣ ይዳኛል ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ተዘጋጅተው ፡ የነበሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ በመጨረሻ ፡ ሕጉ ፡ ተሠርቶ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡[77] አልተጨመሩም ፡ ነበረ ። እነዚህ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶች ፡ (ኮዲፊኬሺን) እስቲዘጋጁ ፡ ድረስ ፡ ጐዳዩ ፡ በተቋረጠ ፡ ነገር ፡ ሕግ ፡ (የቀደመ ፡ ውሳኔ) መሠረት ፡ መወሰን ፡ ይኖርበታል ። በጐዳዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሮኑን ፡ ከመገምገማችን ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ ጐዳይ ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፡ የያዙዋቸውን ፡ አቀራረቦች ፡ እስቲ ፡ እንመርምር ።

ወደሚዳኘው ፡ (ወደሚገዛው) የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ አቀራረቦች ፡

እንዲቀና ፡ (እንዲያመች) ሲባል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አቀራረብ ፡ የጋራ ፡ ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ (ኮሞን ፡ ሎው) አቀራረብና ፡ የላቲን ፡ አመሪካዊው ፡ አቀራረብ ፡ ተብለው ፡ ሊጠሩ ፡ ወደሚችሉ ፡ ሦስት ፡ ኮለል ፡ ብለው ፡ ተለይተው ፡ የተመደቡ ፡ ዳኜ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ ጐዳይ ፡ አቀራረቦች ፡ ተይዘዋል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ አንዳንዱ ፡ ወደምህላው ፡ ፈታቸውን ፡ ቢያዞሩም ፡ የብሔራዊ ፡ (ፍትሐ)ሕግ ፡ አገሮች ፡ የኾኑት ፡ በትንሹም ፡ ኾነ ፡ በትልቁ ፡ ተወላጅነትን ፡ የሚዳኘው ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግን ፡ እድርገው ፡ ተቀብለውታል ። ለምሳሌ ፡ ያኸል ፡ የፈረንሳይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ "ስለ ፡ ሰዎች ፡ ኹኔታና ፡ መብቶች ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚቀመጡ ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሰዎችን ፡ (ኹሉ) ይዳኛሉ ፡" ሲል ። እንዲሁም ፡ የፈረንሳይ ፡ ግላዊ ፡ ኢንቴርናሺናል ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የሚቀመጡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ የተወላጅነታቸው ፡ ሕግ ፡ ነው ፡[78] ሲል ፡ ያጸናል ። የኢጣልያው ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ "የሰዎች ፡ አቋምና ፡ የችሎታ ፡ መብት ፡ እንዲሁም ፡ የቤተሰብ ፡ ግንኙነታቸው ፡ (ጉዳያቸው) የሚዳኜው ፡ በሰዎቹ ፡ (በራሳቸው) ሕግ ፡ ነው ፡[79]" ሲል ፡ ያትታል ። የግሪክም ፡ ሕግ [80]፡ የሑንጌሪያ ፡ ሕግ [81]፡ የባልጌሪያ ፡ ሕግ [82]፡ እንዲሁም ፡ የብዙ ፡ ሌሎች ፡ ኤውሮጳዊ ፡ አገሮች ፡ እና ፡ የብሔራዊውን ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔር) ሕግ ፡[83] የሚጠቀሙበት ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ ያው ፡ ነው ።

በተወላጅነት ፡ የመጠቀምን ፡ ምክንያቶች ፡ ስንመረምር ፡ ምክንያቶቹ ፡ ታሪካዊ ፡ ማለት ፡ የዝግጅቱን ፡ ንድፈ-ሐሳባዊ ፡ (ቴዎሬቲካል) ጠባይ ፡ ሊከተሉ ፡ የሚችሉ ፡

---

77 ዴቪድ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ፴፮ ፡ ቱሌይን ፡ ሎው ፡ ሬቪው ፡ (የቱሌይን ፡ ሕግ ፡ መጽሔት) ፩፻፹፮ (፲፱፻፷፫) ።

78 ፕላኒዮል ፡ ትራቲስ ፡ እን ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ (በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ምርምር ፡ ቅንጅት ፡ ፩፻፹፩ ፡ (፲፱፻፵፱ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡) ምርምርን ፡ ይመለከቷል ።

79 ምክካስኬር ፡ የኢጣልያኑ ፡ የሕጎች ፡ ግጭት ፡ ደንቦች ፡ ፭፭ ፡ ቱሌይን ፡ ሎው ፡ ሬቪው ፡ (ቱሌይን ፡ የሕግ ፡ መጽሔት) ፫ ፡ ፫፭ (፲፱፻፶) ምርምርን ፡ ይመለከቷል ።

80 ኒኮሌፖውሎስ ፡ የግል ፡ ኢንቱርናሺናሳዊ ፡ ሕግ ፡ ባዲው ፡ የግሪክ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ፳፫ ፡ ቱሌይን ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፳፻፶፱ ፡ ፳፻፶፭ (፲፱፻፵፱) ምርምርን ፡ ይመለከቷል ።

81 ድሮቢንግ ፡ ኮንፍሊክት ፡ አፍ ፡ ሎውስ ፡ ኢን ፡ ሪሰንት ፡ ኢስት ፡ ዩሮፒያን ፡ ትሪቲስ ፡ (የሕጎች ፡ ግጭቶች ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ የምሥራቅ ፡ ኤውሮጳውያን ፡ ስምምነቶች)፡ ፭፡ አሜሪካን ፡ ጆርናል፡ አፍ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡ (የሕግ ፡ ማስተያያ ፡ አሜሪካዊ ፡ መጽሔት) ፲፻፹፮ ፡ ፲፻፹፱ ፡ (፲፱፻፶፯) ምርምርን ፡ ይመለከቷል ።

82 ኢቢድ ፡ (ከዚያው) ።

83 ፩ ፡ ራቤል ፡ የሕጎች ፡ ግጭት ፡- (አነጣጣሪ/አመጣጣኝ ፡ ጥናት) ኮምፓራቲቭ ፡ ስቱዲ ፡ ፩፻፲፫-፩፻፲፩፡ (ጀኖ ፡ አትም ፡ ፲፱፻፶፯) ይመለከቷል ። ደግሞም፡ ምክካስኬር፡ ሱፕራ ፡ (ከላይ) ማሳሰቢያ ፡ ቁ. ፭፱፡ ይመለከቷል ።

ወይም ፡ እንዲያው ፡ የሚዳሰስና ፡ የሚጨበጥ ፡ ፍሬን ፡ የሚሰጡ ፡ (ፐራክቲካል ፡) ምክን ያቶች ፡ ሊኾኑ ፡ ይችላሉ ። በኢጣልያው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ አስተውሎውን ፡ በመጣል ፡ ባ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተወላጅነትን ፡ መሠረተ-ሐሳብ ፡ ይዞ ፡ መቈየት ፡ ከኹለት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ታሪካዊ ፡ ሲኾን ፡ ሌላው ፡ ፖሊቲካዊ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አንዱ ፡ ጸሐፊ ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጠ [84] ። የተወላጅነቱ ፡ ልም ፡ እጅግ ፡ በበለጥ ፡ የዳበረው ፡ (የለማው) በኢጣልያ ፡ የመተባበር ፡ እንቅስቃሴ ፡ ዘመን ፡ ማንቺኒ ፡ በተባለው ፡ አንድ ፡ ኢጣልያናዊ ፡ እጅ ፡ እንደኾነ ፡ ያ መለክታል ። የማንቺኒ ፡ ዐይነተኛ ፡ የሐሳብ ፡ ምርምር ፡ ሕግ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ እንጂ ፡ ግዘአታዊ ፡ (የምድር ፡ ግዛት ፡ ስፋት) አይደለም ፡ ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ የተሠራ ፡ እንጂ ፡ ለተወሰነ ፡ የምድር ፡ ግዛት ፡ አይደለም ። [85] ነበረ ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሲመለከቱት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የትም ፡ ቢቀመጥ ፡ (ቢኖር) [86] ብሔራዊ ፡ ሕጉን ፡ እንደያዘ ፡ ይዞራል ፡ ነው ። ይኸውና ፡ በተለይ ፡ ግል ፡ ጕዳዮች ፡ የሚዳኘው ፡ ከምህላዌ ፡ ይልቅ ፡ ብሔራዊዉ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ደራሲው ፡ (ሐሳቡን ፡ አመንጪው) እንዳመለከተው ፡ የፖሊቲካ ፡ ምክን ያቱ ፡ "በሙሶሊኒ ፡ ግርጌ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ፈን ድቆ ፡ በነበረው ፡ ብሔራዊ ፡ (ናሺናሊስቲክ) ስሜት ፡ አብነት ፡ እምነቶች ፡ (ዶክትሪ ንስ) ፡" ላይ ፡ የቆመ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ አብነታዊ ፡ እምነቶችም ፡ እንደሚከተለው ፡ ከረ ዥም ፡ በትንሹ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ አድርጎ ፡ ያጠቃልላቸዋል ፤-

> "የወጣውን ፡ (ውጭ ፡ አገር ፡ የኼደውን) ተወላጁን ፡ ለመዳኘት ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የተወ ፡ (የለቀቀ) እንደኾነ ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ ፈላጭ-ቈራጭ ፡ ሥልጣኑን ፡ (ሶቬሬይኒቲ) አውልቆ ፡ መጣል ፡ ይኾንበታል ፤ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ (ኹነታ) ቢገለበጥ ፡ ወይም ፡ ቢዘዘር ፡ ተቀባዩ ፡ አገር ፡ ለሱ ፡ ያልተሠሩትን ፡ ሕጎች ፡ የፈጸመበት ፡ እንደኾነ ፡ አገሩን ፡ ትቶ ፡ የወጣ ውን ፡ ሰው ፡ (ኤሚግሬ) መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ ፈላጭ-ቈራጭ ፡ ሥል ጣኑን ፡ መጣስ ፡ ይኾንበታል ፤ ለመደምደሚያም ፡ አገሩን ፡ ለቅቆ ፡ የወጣው ፡ ሰው ፡ ካባት ፡ (ከናት) አገሩ ፡ ጋራ ፡ የሚኖረው ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰሪያ ፡ ለብሔ ራዊ ፡ ወግና ፡ ሥርዐቶች ፡ (ኢኒስቲቱይሺንስ) ታማኝነቱን ፡ ማዳበሪያ ፡ ይ ኾን ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ የሚጨምር ፡ ነው ።"

እንግዲህ ፡ በስተሌላ ፡ መንገድ ፡ ሲመለከቱት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ ኢጣልያ ውያንን ፡ በኢጣልያኑ ፡ ሕጎች ፡ ማሰሩ ፡ (ተጠያቂ ፡ ማድረጉ) ለኢጣልያ ፡ በጣም ፡ የሚ ጠቅማት ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ። በጣልያን ፡ አገር ፡ ለሚቀመጡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎ ችም — መቸም ፡ ቍጥራቸው ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነበረ — እንደዚሁ ፡ የመሰለ ፡ አያያዝ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ወጸፋው ፡ ጠየቀ ።

አንዱ ፡ ሌላ ፡ ደራሲ ፡ በግሪክ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ምርምሩን ፡ ሲጥል [87] ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ያለም ፡ ክፍለ-ሀገሮች ፡ የሚወጡ ፡ (በኢትዮጵያም ፡ ቅሉ ፡ ቍጥራቸው ፡ በቂ ፡ ጉላት ፡ ያለው ፡ አሉ) ቍጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጆች ፡ ስላሉ ፡ እና ፡ "በዚ

---

84 ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ (ማሳሰቢያ) ቍ. ፰፱ ፡ በምክክስኬር ፡ ገጽ ፡ ፰፪ ።

85 በስታምቡርግ ፡ ኬሲስ ፡ አን ፡ ኮንፍሊክትስ ፡ (በግጭቶች ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ነገሮች) ፭ ፡ (የ፲፱፻፶፯) ፡ የማንቺኒን ፡ ንድፈ-ሐሳብ ፡ ምርምር ፡ ይመለከቷል ።

86 ከዚህ ፡ ወጣ ፡ ያለው ፡ ልማድ ፡ ሰውየው ፡ በሚቀመጥበት ፡ አገር ፡ (መንግሥት) የሕዝብ ፡ ሰላማዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (የሕዝብ ፡ ጸጥታ) የመንግሥቱ ፡ ሕግ ፡ እንዲፈጸም ፡ በሚያስፈልግበት ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ነው ። እነሆ ፡ የፈረንሳይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ "የፖሊስና ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ሕጎቹ" በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ኑዋሪዎች ፡ ኹሉ ፡ ይዳኛሉ ፡ ሲል ፡ ያትታል ።

87 ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ቍ. ፹ ፡ በኢኮሌቶፖውሎስ ፡ ገጽ ፡ ፻፲፭ ።

ያው ፡ መቀጠሉ ፡ ራስን-ማትረፊያ ፡ (ማዳኛ ፡ ወይም ፡ መጠበቂያ) የተባለውን ፡ የተወላጅነቱን ፡ ዝግጅት ፡ (ሲስቱም) ወደ ፡ መተው ፡ ለመምራት ፡ (ለመውሰድ) ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ በቂ ፡ ጎይል ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሊኖር ፡ ” አይችልም ፡ ሲል ፡ ያትታል ። ይህ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ ተወላጆችን ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ እቋምን ፡ ለመቈጣጠር ፡ የመሻቱ ፡ ጕዳይ ፡ ፖሊቲካዊ ፡ ፍልስፍና ፡ እምነትን ፡ (አይዲዮሎጂ ፡ ወይም ፡ ሐሳብ ፡ ቅንጅትን) ሳያወላውሉ ፡ አጥብቆ ፡ ከመከተሉ ፡ እንኳ ፡ ተቀዳሚነት ፡ አለው ። ለምሳሌ ፡ ያኽል ፡ ሓንግሪንና ፡ ባልጌሪያን ፡ በመሰሉ ፡ የሶቪያሊስት ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ስምምነቶች ፡ ተወላጅነትን ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መነሻ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ይዘውታል ። አንዱ ፡ ጸሐፊ ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲጥል [88] ፡ የተወላጅነቱን ፡ ልም ፡ እንደገና ፡ ማጽደቁ ፡ “የሚያስደንቅ ፡” እና ፡ ከሶቪያሊስት ፡ ንድፈ-ሓሳብ ፡ ጋራ ፡ የማይሰማማ ፡ ነው ፡ ይላል ። “በዚህኛው ፡ ወይም ፡ በዚያኛው ፡ ሶቪያሊስት ፡ አገር ፡ ኮምሬድ ፡ (በሶቪያሊስት ፡ ወይም ፡ በኮሚኒስት ፡ አገሮች ፡ የነፍስ-ወከፍ ፡ ርስ-በርስ ፡ መጠራሪያ ፡ ‘ጓድዬ ፡’ እንደማለት ፡ ቅጽል ፡ ነው) ላይ ፡ የዚህን ፡ ወይም ፡ የዚያኛውን ፡ ሕግ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ ማድረጉ ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ የሌለው ፡ የማያስፈልግ ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ አይኾንምን ፡” ሲል ፡ ይጠይቃል ። ውጤቱን ፡ “ከቶ ፡ በማይጣሰው ፡ የያንዳንዱ ፡ ሶቪያሊስት ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ ፌላሞ-ቈራጭ ፡ ሥልጣን ፡” መሠረት ፡ ለመግለጥ ፡ ሲቻል ፡ የሚቀመጡባቸው ፡ በሌላ ፡ የሶቪያሊስት ፡ አገሮች ፡ ቢኾንም ፡ እንኳ ፡ ቅሉ ፡ ካገር ፡ ውጭ ፡ (ከውሰን ፡ ድንበር ፡ ወዲያ) የሚቀመጡ ፡ ተወላጆችን ፡ ለመቈጣጠር ፡ መሻቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ።

ለመጨረሻ ፡ ካገር ፡ ውጭ ፡ የሚቀመጡ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ተወላጆች ፡ ያሏቸው ፡ አገሮች ፡ የዜጎቻቸውን ፡ ግላዊ ፡ እቋም ፡ በተለየም ፡ ቢጋብቻ ፡ እና ፡ በቤተሰቡ ፡ ረገድ ፡ በባዕድ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ከነባዕድ ፡ ሐሳቡ ፡ ይዳኙብናል ፡ ብለው ፡ ሊፈሩ ፡ ይችላሉ ። አንዱ ፡ ጸሐፊ ፡ ቤልጂግ ፡ ሆላንድና ፡ ሉክሳንቡርግ ፡ የተወላጅነት ፡ ቅንጅትን ፡ (ሲስተም) [89] የተከተሉበትን ፡ ምክንያት ፡ ለይቶ ፡ ሲያወጣ ፡ “ብዙ ፡ ምሥራቃዊ ፡ አገሮች ፡ በፍጹም ፡ የተለየ ፡ የጋብቻ ፡ እና ፡ የወላጅ-የልጅ ፡ ዝምድናዎች ፡ አስተያየቶች ፡” ስላሏቸው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ያስተውላል ። ምህላውን ፡ በነዚያ ፡ አገሮች ፡ ላደረጉት ፡ ዜጎቻቸው ፡ ጥንድ ፡ (ድርብ) ጋብቻ ፡ (ቢጋሚ) ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጕዳይን ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የምዕራብ ፡ አገሮች ፡ እንዲቀበሉ ፡ አያስፈልግም ፤ ስለዚህም ፡ ለተለይ ፡ ግላዊው ፡ ሕግ ፡ የሚኾነው ፡ ከምህላዉ ፡ ይልቅ ፡ የተወላጅነቱ ፡ ሕግ ፡ ሊኾን ፡ ማስፈለጉ ፡ እንዲጸና ፡ ሲል ፡ ይተቻል ።

ብዙ ፡ አገሮች ፡ ተወላጅነትን ፡ እንደየተለይ ፡ ግል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ የተቀበሉበት ፡ እንደዚህ ፡ ለመሰሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ሲሉ ፡ ነው ።

እንግሊዝንና ፡ የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታትን ፡ ምህላውን ፡ እንደየተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ እንዲቀበሉት ፡ ያደረጉዋቸው ፡ ወይም ፡ የመሩዋቸው ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ግምግሞች ፡ ናቸው ። የአንግሎ-አሜሪካ ፡ ሕግ ፡ ግጭቶች ፡ በመገሥገሪያ ፡ ቢሑቤር ፡ ይዘጋጂ ፡ (ይውጡ) እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ባሉት ፡ ጊዜያቶች ፡ በአሜሪካው ፡ የሕግ ፡ ምሁር ፡ ጀሴፍ ፡ ስቶሪ [90] ፡ ጽሑፎች ፡ እጅግ ፡ የላቀውን ፡ የመንቀ

---

88 ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ቍ. ፰፩ ፡ በድሮቢንግ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፸፮ ።

89 ሜይጂርስ ፡ በግል ፡ ኢንቴርናሽናሎ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የቤኔሉክሱ ፡ (ቤልጅግ ፡ ሆላንድና ፡ ሉክሳንቡርግ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ የሚጠሩበት፡ ነው ፡) ቃል-ኪዳን ፡ ፮ ፡ ሕግን ፡ የማስተያያው ፡ (ማነጣጠሪያው) አሜሪካዊ ፡ መጽሔት ፡ ፩-፪ ፡ (፲፱፻፶፫) ።

90 ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ቍ. ፰፭ ፡ በስታምበርግ ፡ ገጽ ፡ ፫ ፡ ያለውን ፡ ምርምር ፡ ይመለከቷል ።

ሳቀሻ ፡ ጎይሉን ፡ ያገኘው ፡ የግዘአታዊነትን ፡ ንድፈ-ሐሳብ ፡ ተከትሏል ። የግዘአታዊነ ት ፡ ንድፈ-ሐሳብ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ የያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ ሕጎቹ ፡ በአገሩ ፡ ወሰን ፡ ክል ሎች ፡ ውስጥ ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ ውጭ ፡ አይጸኑም ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጋቸውን ፡ ተሸክመው ፡ አይንከራተቱም ፤ ይልቁንስ ፡ የሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ ተገዥ ፡ ናቸው፡ እንጂ ። ስለዚህም ፡ ዳኟው ፡ የተለይ ፡ ግላዊው ፡ ሕግ ፡ ከተወላጅነቱ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ የሰውየው ፡ ምህላው — ከዚያው ፡ ለመቅረት ፡ ወቅዶ ፡ የነበረበቱ ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ ነው — ሕግ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ በቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ሲመ ጣጠን ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ውጭ ፡ የሚቀመጡ ፡ እንግሊዛውያን ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ። በቅኝ ፡ ግዛቶችም ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቱን ፡ የጨበጠችው ፡ ወይም ፡ የምትቈጣጠ ረው ፡ እንግሊዝ ፡ ነበረች ፤ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በሚታያት ፡ ላይ ፡ የብሪታንያውን ፡ ሕግ ፡ በብሪታንያ ፡ ተወላጆች ፡ ላይ ፡ መፈጸሙን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ትችል ፡ ነበረ ። እንደዚሁም ፡ ምህላውን ፡ እንደገዥ ፡ የተለይ ፡ ግላዊው ፡ ሕግ ፡ በማድረግ ፡ የአሜሪካ ፡ ግዛቶች ፡ (አገ ሮች ፡ ወይም ፡ መንግሥቶች) ቍጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ከውጭ ፡ አገር-መጦች ፡ ላይ ፡ የቍጥጥር ፡ ክንዳቸውን ፡ ለማሳረፍ ፡ ቻሉ ፤ መቸም ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ ቅሉ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ከአገር ፡ ውጭ ፡ ያደረጉ ፡ አሜሪካውያን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

ጥቂቱ ፡ የላቲን ፡ አሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ የተቀላቀለ ፡ ቅንጅትን ፡ ይከተላሉ ። ምህላዋቸውን ፡ በዚያው ፡ ባደረጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የዚያው ፡ ያገሩ ፡ ሕግ ፡ ይፈጸምባቸዋል — እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ የጋራ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ (ኮሞን ፡ ሎው ፡) አቀ ራረብን ፡ ይከተላሉ ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አገሮች ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ያደ ረጉ ፡ ተወላጆቻቸውን ፡ ግላዊ ፡ ግንኙነቶቻቸውን ፡ ለመዳኘት ፡ የሚጠቀሙበት ፡ ብሔ ራዊ ፡ ሕግን ፡ ነው ። በቺሌ ፡ በኮሎምቢያ ፡ በኤኩዋዶር ፡ በኮስታሪካ ፡ በኤልሳልቫዶር ፡ በፔሩ ፡ በቬኔዙዊላ ፡ እና ፡ በሜክሲኮ ፡[91] የተያዘው ፡ አቀራረብ ፡ ጥቂት ፡ በመለዋወጥ፡ ይኸው ፡ ነው ። ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ አገሮችን ፡ ዐላማ ፡ (ምንባራቸውን ፡ በ ውጭ ፡ አገር ፡ ያደረጉ ፡ ተወላጆቻቸውን ፡ መቈጣጠሩን ፡ ማለት ፡ ነው ፡) ያከናውናል ።

በግል ፡ ኢንቴርናሺናላዊ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በንድፍ ፡ የቀረበው ፡ ረቂቅ ፡ ከዐምስት ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ያደረጉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አቋማቸውና ፡ የችሎታ ፡ መብታቸው ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖኝ ፡ በማድረግ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ አቀራረብ ፡ የሚያሻሽል ፡ ነው ። በሌላ ፡ ማንኛቸውም ፡ ስፍራ ፡ ምህላዋቸውን ፡ ያደረጉ ፡ ፈረንሳውያን ፡ በፈረንሳይ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡[92] ተጠያቂ ፡ ወይም ፡ ተገዢ ፡ መኾናቸውን ፡ ይቀጥላሉ ።

ቍጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዜጎቿ ፡ ምንባራቸውን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ላደረጉባት ፡ አገር ፡ እና ፡ ቍጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ላቋቋሙባት ፡ አገር ፡ ምናልባት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አቀራረብ ፡ የሚበጃት ፡ ይኾናል ። ቢኾንም ፡ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ክፉ-ፈቃድን ፡ (-ስሜትን) የሚፈጥር ፡ እንጂ ፡ የሚረዳ ፡ አይደለም ፤ አንድ ፡ መንግሥት ፡ መካናቸውን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ላደረጉ ፡ ዜ ጎቹ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ እንዲኾን ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ካመነ በት ፡ እንኪያውስ ፡ በራሱ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ሊፈጽመው ፡ የገለጠውን ፡ ቍጥጥር ፡ በዜጎቻ ቸው ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ያንኑ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ መንፈግ ፡ አይገባውም ።

---

91 ናዬልማን ፡ ዘ ፡ ኩየትሺን ፡ እና ፡ ሬሺዝን ፡ እና ፡ ዘ ፡ ባስትማንተ ፡ ኮድ ፡ (የባስትማንተን ፡ ሕግ፡ ሰለ ማሻሻል ፡ ያለው ፡ ጣጣ) ፡ ፶፮ ፡ የአሜሪካ ፡ የኢንቴርናሺናል ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፲፱፻፹ ፡ (፲፱፻፵፫) ።

92 አንቀጽ ፡ ፭፮ ።

ዳኛ ፡ የኾነው ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተነገረው ፡ ለተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ የሚኾኑ ፡ ሕጉጋዊ ፡ (በዐዋጅ ፡ የተነገሩ) ውሳኔዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሉም ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ፍርዳዊ ፡ ውሳኔዎች ፡ ማለት ፡ እንዳንዱ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረቱ ፡ ተወላጅነት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲበይኑ ፡ ሌሎቹም ፡ ምህላው ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲወስኑና ፡ በኹለቱም ፡ መንገዶች ፡ ሲጓዙ ፡ ቈይተዋል ። የዚህ ፡ እንቀጽ ፡ ደራሲ ፡ ላወቃቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ከሚኾኑት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ኹለት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ዳኛ ፡ የኾነው ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ የተወላጅነቱ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ወሰኑ ። በቬርጂኔላ ፡ እና ፡ በአንቶኒያኒ ፡ መካከል [93]፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ኢጣልያዊ ፡ ተገዥ ፡ ኹኖ ፡ ምህላዉ ፡ መቸም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኾነው ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ፍርዳዊ ፡ መለያየት ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያገኝ ፡ ጠየቀ ፡ (ፈለገ) ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳተተው ፡ ፍርዳዊ ፡ መለያየት ፡ የተባለው ፡ ወግና ፡ ሥርዐት ፡ ኢኢስቲቱይሺን) ለኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ የታወቀ ፡ እይደለም ። ኢጣልያዊው ፡ ሕግ ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በየነና ፡ ፍርዳዊ ፡ መለያየቱን ፡ አዘዘ ። ኢጣልያዊውን ፡ ሕግ ፡ የፈጸመበት ፡ ምክንያቶች ፡ እንደሚከተሉት ፡ ነበረ ፡-

(፩) አቤት ፡ ባዩ ፡ ኢጣልያዊ ፡ ተገዥ ፡ ስለነበረ ፤

(፪) መልስ ፡ ሰጪዋም ፡ ኢጣልያዊት ፡ ተገዥ ፡ ስለነበረች ፤

(፫) ጋብቻው ፡ የተከበረውና ፡ የተፈጸመው ፡ ኢጣልያዊው ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ስለነበረ ፤

(፬) ለፍርዳዊ ፡ መለያየት ፡ የሚኾን ፡ ውሳኔ ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስላልነበረ ፤ እና ፡

(፭) ኢትዮጵያዊ ፡ ሕግ ፡ ለጉዳዩ ፡ የሚያገለግል ፡ አንዳች ፡ ውሳኔ ፡ ባላደረገበት ፡ ላይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በሚነሡት ፡ ነገሮች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ልሞችን ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ማዋሉ ፡ የኢትዮጵያው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ልማድ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምርምር ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አድርጎ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ህልው ፡ ችሳ ፡ ይለዋል ፤ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የውሳኔው ፡ ውጤት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ የማይገኘው ፡ መድነንን ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አገኘ ፡ ነው ።

ሌላ ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ውጤት ፡ ያገኘው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ባለጉዳይ ፡ ወገኖቹ ፡ ምህላዋቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እድርገው ፡ በነበሩት ፡ የግሪክ ፡ ዜጎች ፡ ካትሶውሊስ ፡ ከካትሶውሊስ ፡ ጋራ ፡[94] ተነሥቶ ፡ በነበረው ፡ ላይ ፡ ነው ። ከድታው ፡ ከመኼዷ ፡ የተነሣ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ፍቺን ፡ ፈለገ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊወሰን ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ በየነና ፡ በግሪኩ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተመሠረተ ፡ ፍቺን ፡ አዘዘ ። እንድሪያምፓናና ፡ ከእንድሪያምፓናና ፡ ጋራ [95]፡ እና ፡ ዜርቮስ ፡ ከዜርቮስ ፡ ጋራ [96] በነበሩት ፡ ነገሮች ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ (ባለጉዳይ ፡ ወገኖች ፡ ምህላዋቸውን ፡ ከዚሁ ፡ ያደረጉ ፡ ነበሩ ፡)እና ፡ በተወላጅነታቸው ፡ ሕጉ ፡

---

93 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍ. ፩፻፭/፶ ።

94 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍ. ፩፻፶/፶፭ ።

95 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍ. ፩፻፶፭/፶፱ ።

96 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍ. ፩፻፶፭/፶፱ ።

መካከል ፣ ግጭት ፣ ስላልነበረ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጉዳዩን ፣ አላብላላውም ፣ ከውሳኔም ፣ አልዶ ረሰበትም ፤ በዚህኛው ፣ ኾነ ፣ በዚያኛው ፣ መንግሥት ፣ በኹለቱም ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ቢ ኾን ፣ እቤት ፣ ባዩ ፣ ፍቺን ፣ ለማግኘት ፣ ባለመብት ፣ ነበረና ። እነዚህ ፣ ነገሮች ፣ የፍትሐ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ከጸናበት ፣ ቀን ፣ በፊት ፣ የተወሰኑ ፣ ነገሮች ፣ መኾናቸውን ፣ እንዲገነዘ ቡት ፣ ያስፈልጋል ፤ ከዚህ ፣ ግርጌ ፣ እንደምናየው ፣ በሕጉ ፣ (ኮዱ) መሠረት ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ፍቺን ፣ ለመወሰን ፣ ሲባል ፣ ፍርዳዊ ፣ ሥልጣንን ፣ አያጠልቁም ፣ (አይዙም) ።

በስተሌላ ፣ በሱል ፣ ደግሞ ፣ የንጉሥ-ነገሥት ፣ ጠቅላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በኹለት ፣ ነገሮች ፣ ላይ ፣ ምህላው ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ይኾን ፣ ዘንድ ፣ ወስኗል ። በዮሐንስ ፣ ፕራታ ፣ እና ፣ በወ/ት. ጸጋይነሽ ፣ መኰንን ፣ መካከል ፣[97] በተነሣው ፣ ነገር፣ ፍርድ ፣ ቤቱን ፣ ያጋጠመው ፣ ኹነታ ፣ ምህላዉን ፣ በኢትዮጵያ ፣ እንዳደረገ ፣ የሞተ ፣ የኢጣልያ ፣ ዜጋ ፣ ጉዳይን ፣ ነበረ ። በኢጣልያ ፣ አገር ፣ ሚስት ፣ እግብቶ ፣ ከሷ ፣ የተወለ ጱ ፣ ልጆችን ፣ የተወ ፣ ሰው ፣ ነበረ ። ካንዲት ፣ ኢትዮጵያዊት ፣ ጋራም ፣ ዐብሮ ፣ ኑሮ ፣ ከሷ ፣ ደግሞ ፣ በኢጣልያዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ከሕግ ፣ ውጭ ፣ (ዲቃላ) የሚቈጠሩ ፣ ልጆ ችን ፣ ተወ ። በኢጣልያዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ዲቃሎች ፣ (ከማእሰረ-ጋብቻ ፣ ውጭ ፣ የተወ ለዱ ፣) ካባታቸው ፣ ለመውረስ ፣ አይችሉም ። በኢትዮጵያ ፣ ሕግ፣ መሠረት፣ የሕግ-ውጭ ፣ ልጅነት ፣ ፅንሰ-ሓሳብ ፣ (ኮንሴፕት) ከቶ ፣ ያልታወቀ ፣ ነው ። አባትነት ፣ እስከታወቀ ፣ ድረስ ፣ በዚህ ፣ ጉዳይም ፣ ላይ ፣ አባትነት ፣ ታውቆላቸው ፣ ነበረ ፣ ልጆች ፣ ኹሉ ፣ ካባታ ቸው ፣ እኵል ፣ ይካፈላሉ ። ኢጣልያዊው ፣ ሕግ—የተወላጅነቱ ፣ ሕግ ፣ ማለት ፣ ነው— ከሥራ ፣ ላይ ፣ ቢውል ፣ ኑሮ ፣ ኢጣልያናዊ ፣ ልጅቱ፣ ብቻ ፣ ይወርሱ፣ ነበረ ። ኢትዮጵያዊው ፣ ሕግ — የምህላዉ ፣ ሕግ ፣ ማለት ፣ ነው — ከሥራ ፣ ላይ ፣ ሲውል ፣ ልጆቹ ፣ የኾኑት ፣ ኹሉ ፣ ኢጣልያውያንና ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ እኵል ፣ ይካፈላሉ ። የንጉሥ-ነገሥት ፣ ጠ ቅላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ምህላው ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ነው ፣ ሲል ፣ ወሰኖ ፣ ኢትዮጵያዊው ፣ ሕግ ፣ እንዲፈጸም ፣ እደረገ ። የፍርዱ ፣ እንግሊዝኛው ፣ ብሂል ፣ የሚከተለ ውን ፣ ይገልጣል ፦-

> ‘‘እነሆ ፣ የተለይ ፣ ግላዊ ፣ ሕጉ ፣ የሻቹ ፣ የተወላጅነት ፣ ሕጉ ፣ ወይም ፣ በ ሞተበት ፣ ጊዜ ፣ የነበረው ፣ የምህላዉ ፣ ሕግ ፣ ሊኾን ፣ ይችላል ። ከነዚህ ፣ ኹለቱ ፣ ሕጎች ፣ የትኛውን ፣ እንደሚከተሉ ፣ የሚነድቅ ፣ ሥሩዕ ፣ (በፓርላ ሜንት ፣ የወጣ ፣ ሕግ) በኢትዮጵያ ፣ ካለመኖሩም ፣ በላይ ፣ (ከዚህ ፣ ቀደ ም) የተቈረጡት ፣ ነገሮች ፣ አንደኛውን ፣ ሕግ ፣ ወይም ፣ ሌላውን ፣ በመከተ ል ፣ የጸኑ ፣ አልበነረም ። ይኹን ፣ እንጂ ፣ የቅርቡ፣ ጊዜ ፣ የሰው ፣ ልጅ፣ ሕግ ፣ ፍልስፍና ፣ አዝማሚያ ፣ ወደ ፣ ምህላው ፣ ሕጉ ፣ እጋድሏል ። በኛ ፣ አስተያየ ት ፣ የምህላው ፣ ሕጉ ፣ የቀድሞ ፣ ተወላጅነቱን፣ ሳይለቅ፣ ምንባሩን ፣ በተለየ ፣ አገር ፣ ባቋቋመ ፣ ሰው ፣ የተቀሰቀሰ ፣ ፍርዳዊ ፣ ኹነታዎችንና ፣ ግንኙነቶችን ፣ ለመዳኘት ፣ በይበልጥ ፣ በቂና ፣ ተገቢ ፣ ነው ፤ ስለዚህም ፣ የምህላው ፣ ሕጉ ፣ የ ግል ፣ አቋም ፣ ጉዳዮችን ፣ ኹሉ ፣ የሚዳኝ ፣ ሕግ ፣ እንዲኾን ፣ ይገባል፣ ስንል፣ እናስባለን ።’’

ይህን ፣ ነገር ፣ ተከትለው ፣ አልፍሬዶ ፣ ፓስቶሪ ፣ ከሚለስ ፣ አስላኒዲስና ፣ ጀርጅ ፣ አስላኒዲስ ፣ ጋራ ፣[98] በነበረው ፣ ነገር ፣ ላይ ፣ ይኸው ፣ ተፈጽሞበት ፣ በባልና ፣ ሚስት ፣

---

97 ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ይግባኝ ፣ ቍ. ፮፻፴፮/፶፪ ።

98 ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ይግባኝ ፣ ቍ. ፫፻፵፰/፶፯ ።

መካከል ፡ የንብረት ፡ መብቶች ፡ ጉዳይ ፡ በተወላጅነቱ ፡ ሕግ ፡[99] ከመዳኘቱ ፡ ይልቅ ፡ ቢጋብቻው ፡ ምህላው ፡ ሕግ ፡ ይዳኛል ፡ ሊባል ፡ ተበየነ ።

በተለየም ፡ የፕራታ ፡ ነገር ፡ ውጤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምህላውን ፡ እንደተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማድረጉን ፡ ለጎሊና ፡ ሚዛን ፡ ተሰማሚነቱንና ፡ ተገቢነቱን ፡ ከለል ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ። ምህላዋቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደረጉ ፡ ቊጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እሱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ በጣም ፡ ደጎና ፡ አድርጋ ፡ ስለምታስተናብርም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ሊያገኙ ፡ ከሚችሉት ፡ ዕድሎች ፡ የሚበልጥ ፡ በሚቀርቡላቸው ፡ በዚህች ፡ አገር ፡ ብዙ ዎቹ ፡ ዘመን-ኑሮዋቸውን ፡ (ሕይወታቸውን) በዚሁ ፡ ለማሳለፍ ፡ መምረጥ ፡ ችለዋል ። ቀደም ፡ ብሰን ፡ እንዳየነው ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ሕጋዊ ፡ ልዩነቶቹ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ምህላዋቸውን ፡ በሌላ ፡ አገሮች ፡ ያደረጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ቊጥር ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ምህላዋቸውን ፡ በዚሁ ፡ ያደረጉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎቹ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በዚሁ ፡ ይኖራሉ ፡ በሙያ ፡ ተግባራቸው ፡ ይሰ ማራሉ ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ አግብተው ፡ ይወልዳሉ ፡ ይከብዳሉም ። የንዚህን ፡ ሰዎች ፡ አቋ ምና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብታቸውን ፡ ውርስ ፡ በማደላደል ፡ (በመመጠን) እና ፡ በመቊጣ ጠር ፡ ኢትዮጵያ ፡ አውራ ፡ (ብርቱ) ጥቅም ፡ አላት ። አህጉራዊው ፡ ኤውሮጳ ፡ ተወላ ነትን ፡ እንደግል ፡ የተለይ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የቊጠሪበት ፡ አውራ ፡ ምክንያት ፡ በዚያው ፡ ምህላዋቸውን ፡ ካደረጉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ቊጥር ፡ ይልቅ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚቀመጡ ፡ ቊጥራቸው ፡ በጣም ፡ የበዛ ፡ የራሳቸው ፡ ዜጎች ፡ ስላሏቸው ፡ የዜጎቻቸ ውን ፡ አቋም ፡ ለመቊጣጠር ፡ ስለፈለጉ ፡ ነው ። በሌላ ፡ አንጋገር ፡ የሚዳኘው ፡ ሕግ ፡ ደንብ ፡ ተቀርፆ ፡ የሚወጣው ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ ባላነሰ ፡ እኳኋን ፡ ያንኑ ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚያውለው ፡ አገር ፡ ጥቅም ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ኢትዮጵ ያ ፡ ጥቅሙዋን ፡ ልትጠብቅ ፡ ያስፈልጋል ፡ ስለዚህም ፡ ምህላውን ፡ እንደተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ልታደርገው ፡ ይገባል ። ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተገለጠው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ምህላው ፡ በቀላሉ ፡ ይለያል ። እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ዘንዳም ፡ ከምህ ላው ፡ ይልቅ ፡ ተወላጅነትን ፡ መለየቱ ፡ ይቀላል ፡ በማለት ፡ ተወላጅነት ፡ እዲመረጥ ፡ አይገባም ። ከረዥሙ ፡ በትንሹ ፡ ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ለማጠቃለል ፡ የተ ለይ ፡ ግላዊው ፡ ሕግ ፡ ሰውየው ፡ ተወላጅ ፡ ከኾነበቱ ፡ ይልቅ ፡ ምህላዉን ፡ ያደረገበቱ ፡ ቦታ ፡ ሕግ ፡ እንዲኾን ፡ ማስፈለጉን ፡ የኢትዮጵያው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዲያጸኑ ፡ እነሆ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቧል ።

እንደፍቺ ፡ የመሰለውን ፡ የቤተ-ሰብ ፡ አቋም ፡ ጉዳዮችን ፡ ለመወሰን ፡ የኢትዮጵያው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍርድ ፡ ሥልጣንን ፡ ስለሚያገኙበት ፡ እኳኋን ፡ የሚናገር ፡ ዐብሮ ፡ የሚዘምት ፡ እሡል ፡ የኾነ ፡ ተጫፋሪ ፡ ጉዳይ ፡ አለ ። ከተከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ ምህ ላዉን ፡ ከዚሁ ፡ ያደረገ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የፍርድ ፡ ሥልጣንን ፡ እንደማ ያገኙ ፡ ተወሰኗል ። ሐሎክ ፡ ከሐሎክ ፡ ጋራ[100] ፡ በተነሣው ፡ ነገር ፡ ፍቺን ፡ ፈሊጉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ የተቀጠረ ፡ አሜሪካዊ ፡ ነበረ ። ከዚህ ፡ የነበረው ፡ ለተወ ሰነ ፡ የውል ፡ ዘመን ፡ ጉዳ ፡ ምህላዉ ፡ በተባበረው ፡ (አ.) መንግሥታት ፡ አላባማ ፡

---

99 በዚያ ፡ ነገር ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ ምህላዋቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አድርገው ፡ እንዳልነበረ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማሣኘቱን ፡ ይገንዘቧል ። ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ቊ. ፩፪ ፡ ያለውን ፡ ምርምርና ፡ ዐሻሺ ፡ ጽሑ ፉን ፡ ይመለከቷል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ አኹን ፡ ምህላዋቸውን ፡ ከዚሁ ፡ ያደረጉ ፡ ኾነው ፡ ይገኛሉ ።

100 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቊ. ፹፻፵፮/፺ ።

ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ። በአላባማ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የፍቺ ፡ ውሳኔን ፡ ለማግኘት ፡ ቢያንስ ፡ ያንድ ፡ ዓመት ፡ ባንዱ ፡ አገር ፡ መቀመጡ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ፍርዳዊ ፡ ሥልጣንን ፡ ለማስጠለቅ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ተከራከረ ። የንጉሥ-ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በፍጹም ፡ ተገቢና ፡ ትክክለኛ ፡ በኾነ ፡ አኳኋን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአላባማ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለጉዳዩ ፡ አስፈላጊ ፡ ያይደሉ ፡ ትርፍ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ በየነ ። መቀመጥን ፡ እንደፍቺ ፡ ፍርዳዊ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚያደርግ ፡ በፓርላሜንት ፡ የወጣ ፡ ሕጉ ፡ ከሌለ ፡ ዘንዳ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲባል ፡ ቢያንስ ፡ ከተከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ ምህላ ዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደረገ ፡ እንዲኾን ፡ ያስፈልገዋል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በየነ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አቤቱታውን ፡ ሳይቀበሉ ፡ እንዲዘጋ ፡ ተደረገ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤት ፡ ባዩን ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አድርጎ ፡ ባላገኘበት ፡ በኮኪኖስ ፡ እና ፡ በኮኪኖስ ፡ መካከል ፡[101] በተነሣው ፡ ነገርም ፡ እንደዚሁ ፡ ካለ ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ ተደረሰ ። ባያሌ ፡ ሴላ ፡ ነገሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዳዊ ፡ ሥልጣንን ፡ ለማያዝ ፡ ቢያንስ ፡ ከተከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ ምህላዉን ፡ በዚህ ፡ ያደረገ ፡ መኾን ፡[102] አለበት ፡ ሲል ፡ ደጋግሞ ፡ አረጋግጧል ። በሕጉ (ኮዱ) መሠረት ፡ ጋብቻው ፡ እስተቋየበት ፡ ድረስ ፡[103] የሚስቲቱ ፡ ምህላው ፡ የባልየውን ፡ ስለሚከተል ፡ እኹን ፡ ባልየው ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደ ረገ ፡ ሰው ፡ እንዲኾን ፡ የሚገባ ፡ መኾኑ ፡ መገለጥ ፡ ያስፈልገዋል ። ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ፍርዳዊ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚያገኙት ፡ በምህላው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ እና ፡ ምህ ላው ፡ የተሰይ ፡ ግላዊ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሚኾን ፡ ስለሚመስል ፡ በፍቺ ፡ ክሶች ፡ የሚያ ገለግለው ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ከዚሁ ፡ ይከተላል ።

ደግሞም ፡ ይህ ፡ እንደዚህ ፡ እንዲኾን ፡ ያስፈለገበቱ ፡ የሥነ-ሥርዐት ፡ (ፕሮሴዱራል) ምክንያት ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ የፍቺ ፡ ነገሮች ፡ ገና ፡ ሲነሡ ፡ (ሲወጠኑ) በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከመሰማታቸው ፡ ይልቅ ፡ በመዝመሪያ ፡ በቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ (በቤተ-ዘመዱ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች) እንዲታዩ ፡ ይገባል ። ከጋብቻ ፡ የሚነሡ ፡ ችግሮች ፡ መዝመሪያ ፡ ለቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ሊቀርቡ ፡ ሲገባ [104] ፡ እንግ ዲህ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተግባር ፡ ፍቺ ፡ ተነግሮ ፡ (ተወስኖ) ወይም ፡ አልተነገረ ፡ መኾኑን ፡[105] መወሰን ፡ ነው ። በወ/ሮ ዝማነሽ ፡ አማረ ፡ እና ፡ በአቶ ፡ ተፈራ ፡ ወልደ-ፀማኑኤል ፡ መካከል ፡[106] በተነሣው ፡ ነገር ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ-ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደገለጠው ፡-

> "ፍቺውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ረገድ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሊፈጽ ሙዋቸው ፡ የሚገቡን ፡ አንዳንድ ፡ ደንቦችን ፡ መሥርቷል ። ከኹሉ ፡ አስቀ ድሞ ፡ በጋብቻ ፡ ኑሮዋቸው ፡ ባበሮቹ ፡ (በተጋቡት ፡ ሰዎች) መካከል ፡ የሚነ ሡትን ፡ ችግሮች ፡ ኹሉ ፡ የሚያቀርቡባቸው ፡ የቤተ-ሰብ ፡ ገላጋዮች ፡ ተብ ለው ፡ የሚጠሩ ፡ የሰዎች ፡ እከባ ፡ እካልን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አጭቁ ሙዋል ። . . . የፍቺ ፡ ጥያቄ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ለቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ነው ፤ የፍቺው ፡ ጥያቄ ፡ ለቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ እስተቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ድረ ስና ፡ እነሱም ፡ ውሳኔያቸውን ፡ እስተሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለፍቺ ፡ የሚ

---

101 ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁ. ፩፻፫፯/፻፱ ።

102 ከላይ ፡ ግስጥንዘቢያ ፡ ቁ. ፶፫ ፡ ቬርጂኔላ ፡ ከአንቶኒያኒ ፡ ጋራ ። ከላይ ፡ ግስጥንዘቢያ ፡ ቁ. ፶፬ ፡ ካት ሶውሲስ ፡ ከካትሶውሲስ ፡ ጋራ ፤ ከላይ ፡ ግስጥንዘቢያ ፡ ቁ. ፶፭ ፡ አንድሪያምፓናና ፡ ከአንድሪያምፓ ናና ፡ ጋራ ፤ ከላይ ፡ ግስጥንዘቢያ ፡ ቁ. ፶፯ ፡ ዜርቮስ ፡ ከዜርቮስ ፡ ጋራ ።

103 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፱ ።

104 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አናቅጽ ፡ ፭፻፭፭ — ፭፻፭፰ ።

105 የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፭፱ ።

106 ፍትሐ ፡ ነሐር ፡ ይግባኝ ፡ ቁ. ፩፻፭/፻፯ ።

ኾን ፡ ምንም ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የለውም ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ በገላጋዮቹ ፡ ፍቺ ፡ መነገሩን ፡ ወይም ፡ አለመነገሩን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ። ”

ሕጉ ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔሩ) ምህላዋቸውን ፡ በዚሁ ፡ ላላደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ልዩ ፡ እያያዝ ፡ እንዲያገኙ ፡ ምንም ፡ ወይነት ፡ ውሳኔ ፡ አልሠራም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ለነሱ ፡ ሲል ፡ ከተ ለመደው ፡ ተለይቶ ፡ የወጣ ፡ ነገርን ፡ (ልዩ ፡ አስተያየትን) በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ሰክቶ ፡ (ከትቶ) ሊያነብ ፡ አይገባውም ። የቤተ-ሰብ ፡ ገላጋዮችን ፡ መመደብ ፡ (መሾም) ወይም ፡ የቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ በሌሉበት ፡[107] ነገሩን ፡ መስማት ፡ መቀጠል ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ የራቀ ፡ ጉዳይ ፡ ይኾንበታል ። በኮኪኖስ ፡ ከኮኖስ ፡ ጋራ ፡[108] በተነ ሣው ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደገለጠው ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የፍቺ ፡ ጥያቄያ ቸውን ፡ ለምህላዋቸው ፡ (ለቀበሌዎቻቸው) ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማቅረቡ ፡ ለአእምሮ ፡ ሚ ዛን ፡ የሚሰማማ ፡ ነው ።

ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ ከረዥሙ ፡ በትንሹ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ለማጠቃለል ፡ ባልየው ፡ ምህላዉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደረገ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የፍቺ ፡ አቤቱታ ፡ አይሰሙም ፤ ባልየው ፡ ምህላዉን ፡ ከዚሁ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ሚስቲቱም ፡ በዚሁ ፡ እንደኾነች ፡ ይገነዘባል ። በኢትዮጵያ ፡ ፍቺ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከመታየት ፡ ይልቅ ፡ በቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ሊታይ ፡ ይገባዋል ። ዕርግጥ ፡ ነው ፡ የቤተሰቡ ፡ ገላጋ ዮች ፡ ነባሩን ፡ (ቋሚውን) ኢትዮጵያዊ ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉት ፡ ይገባል ። በፍቺ ፡ ከስ ፡ ጉዳዮች ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ በዚሁ ፡ ባደረጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ተወላጅነትን ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ የተቀበሉት ፡ እንደኾነ ፡ የቤተ-ሰቡን ፡ ገላጋዮች ፡ ማለፍ ፡ ይኖርባቸዋል ። ፍርድ ፡ ቤቶቹም ፡ እንደዚያ ፡ እንዲያደርጉ ፡ የሚያስፈልግበትን ፡ ምክንያት ፡ ማየትም ፡ አዳጋች ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለተገለጡት ፡ ምክንያቶች ፡ ሲባል ፡ ምህላዋቸውን ፡ በዚሁ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ለተወላጅነታቸው ፡ ሕግ ፡ ተዳኚ ፡ ከመኾናቸው ፡ ይልቅ ፡ ለኢትዮጵያው ፡ ሕግ ፡ ተገዥ ፡ እንዲኾኑ ፡ ያስፈልጋል ። ይህን ፡ አቀራረብ ፡ የተከተሉት ፡ እንደኾነ ፡ በፍቺ ፡ ክስ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕግን ፡ የመፈጸሙ ፡ ጣጣ ፡ አይኖ ርም ። እንግዲህ ፡ ለፍቺ ፡ ጉዳይ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖር ፡ የሚችለው ፡ በምህላው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በሕጉ ፡ (ኩዱ) መሠረትም ፡ ፍቺ ፡ ሊነገር ፡ ወይም ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ከመኾኑ ፡ ይልቅ ፡ በቤተ-ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ነው ።

---

107 ይኹን ፡ እንጂ ፡ ባንዳንድ ፡ ኹኔታዎች ፡ የቤተ-ሰብ ፡ ገላጋዮችን ፡ መሾም ፡ የሚጨበጥ ፡ ፍሬን ፡ የማይ ሰጥ ፡ መስሎ ፡ በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍቺውን ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። ፎርቲ ፡ ከፎርቲ ፡ ጋራ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁ. ፩፻፵፬/፺፩ ። በዚያ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከታከራካሪ ፡ ወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ አድራሻው ፡ ጠፍቶ ፡ ነበረ ። ጠቅላይ ፡ የንጉሥነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገላጋዮቹ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ፍቺውን ፡ በመንፈጋቸው ፡ ተሳስተው ፡ ነበረ ፡ ሲል ፡ የበየነበትን ፡ ዜቪ ፡ ከዜቪ ፡ ጋራ ፡ የነበረውን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁ. ፭፻ሕ፭፻፱/፺፭ ፡ ይመለከቷል ። ስለዚህ ፡ ፍቺውን ፡ የፈቀደውን ፡ ያነሰ ፡ ድምፅ ፡ መግለጫ ፡ አደደቀ ።

108 ከላይ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ቁ. ፭፻፭ ።

መደምደሚያ ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ተወላጅነትን ፡ ምህላውን ፡ (ምንባርን/መደበኛ ፡ መኖሪያን/መካንን)እና ፡ ዳኚ ፡ የኾኑ ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከቱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ለመመራመር ፡ ተሞክሯል ። ያ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. ተወላጅነት ፡ ሕጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅነትን ፡ የሚያስገኙትንና ፡ የሚያሰጡትን ፡ ግዴታዎችንና ፡ ኹነታዎችን ፡ ይነድቃል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የምህላውን ፡ ፍች ፡ አወሳሰን ፡ (ትርጒም) በጕልሕ ፡ ከልሎ ፡ (ወስኖ) ፡ ከዚሁ ፡ የሚቀመጡና ፡ የተግባር ፡ ስምሪታቸውን ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ስምሪታቸውን ፡ በዚሁ ፡ ያደረጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በመጪው ፡ ሰዓት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለቅቆ ፡ ለመኼድ ፡ ጕልሕ ፡ የኾነ ፡ ዐሳብ ፡ ከሌላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነባሮች ፡ (መደበኛ ፡ ኑዋሪዎች) ኹነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ የመኾናቸውን ፡ ሕጉጋዊው ፡ ዕቅድ ፡ ከለል ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ። ምንባራቸውን ፡ በዚሁ ፡ ያደረጉትን ፡ ቊጥር ፡ ከፍ ፡ ከማለቱ ፡ ጋራ ፡ ሲያስተያዩት ፡ ለአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ በጣም ፡ ተገቢና ፡ ማለፊያ ፡ የኾነው ፡ የቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔዎች ፡ አዝማሚያ ፡ ምህላውን ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ወደሚደረግበት ፡ መንገድ ፡ መኾኑን ፡ ያመለክታል ። የተለይ ፡ ግል ፡ ኢንቴርናሺናላዊ ፡ ሕግ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ (ኮዲፋይድ) ሰዓት ፡ ምንባር ፡ የተለይ ፡ ግላዊ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ መኾኑን ፡ የሚያሳይ ፡ ውሳኔ ፡ በሕግ ፡ መሰናዶው ፡ (ኮዲፊኬሺን) ውስጥ ፡ እንዲጨመርበት ፡ ያስፈልጋል ።

NATIONALITY, DOMICILE AND THE PERSONAL LAW IN ETHIOPIA

by Robert Allen Sedler, Faculty of Law
Haile Sellassie I University

INTRODUCTION

In this article the writer hopes to explore the Ethiopian law of nationality and domicile and the law applicable to determine matters of personal status. In Ethiopia the foreigner has always been welcome. Many foreigners live and work here, often for many years, but do not become Ethiopian nationals. A country with a large foreign population is thus faced with questions of nationality law, questions of who is domiciled there, and questions of what law shall govern the personal status and relations of individuals. In this paper I propose to present the existing provisions of law relating to Ethiopian nationality, review such legal distinctions as exist between Ethiopians and foreigners, discuss the provisions of the Civil Code that cover the domicile of natural persons and to deal with the question of the governing personal law.

NATIONALITY

Acquisition and Loss of Ethiopian Nationality

It is provided in Article 39 of the Revised Constitution that "the law shall determine the conditions of acquisition and loss of Ethiopian nationality and of Ethiopian citizenship.[1]" The existing law on the subject is the Ethiopian Nationality Law of 1930,[2] which is still in effect. The Civil Code of 1960, it should be noted, contains no provisions with respect to the acquisition or loss of nationality, though it does contain provisions relating to domicile.

There are two basic approaches to determination of nationality and citizenship,[3] that of *jus sanguinis* (nationality by blood) and *jus soli* (nationality by birth). Under the principle of *jus sanguinis*, a child takes the nationality of his parents (where the parents are of different nationality, it is usually the nationality of the father) irrespective of where the child was born. Germany, for example, has adopted parentage as the decisive factor; children born of German parents are German whether born in Germany or abroad while

1. The same provision is contained in Article 18 of the Constitution of 1931.
2. Law of July 24, 1930. Throughout the article the Gregorian calendar will be used unless otherwise indicated. However, Ethiopian cases are cited to the Ethiopian Calendar.
3. Of these two terms, "nationality" is used more in an international context and "citizenship" in a local context. Distinctions between citizens and nationals are frequently made in countries that have colonial possessions. For example, a person born in a possession of the United States is called a national rather than a citizen. United States Code, Title 8, Section 1408. For purposes of international law, there is no distinction between citizens and nationals. See generally, Silving, Nationality in Comparative Law, 5 *American Journal of Comparative Law* 410-415 (1956). Nationals of a country having a monarchial form a government such as Ethiopia are sometimes called subjects. As used in this article, "nationality" and "citizenship" have the same meaning.

children of foreigners born in Germany are not German nationales but take the nationality of their parents.[4]

Under the principle of *jus soli*, children born in a nation, whether the parents be nationals or foreigners, become nationals; conversely, children born to its nationals residing abroad, are not nationals.[5] Argentina is classified as a nation in which the territory on which the birth occurs is the exclusive determining factor.[6]

Many nations recognize elements of both principles in their nationality law, with one or the other usually predominating.[7] The United States is primarily a *jus soli* nation. The Fourteenth Amendment to the Constitution provides that "all persons born or naturalized in the United States, and subject to the jurisdiction thereof, are citizens of the United States,..." This provision insured that all the newly emancipated Negroes and their children would be American citizens. This provision also proved of great value during the large wave of immigration to the United States in the late nineteenth century, as all the children born in the United States of newly arrived immigrant parents would be American citizens.[8] Children born abroad are considered citizens of the United States in certain circumstances.[9] Where both parents are American citizens, the child, though born abroad, is considered an American citizen by birth[10] so long as one parent had a residence in the United States or its possessions prior to the birth of the child. If only one parent is a citizen, that parent must have been a resident in the United States or its possessions for a continuous period of at least one year prior to the birth of the child.[11] Where one parent is a citizen who did not reside in the United States for a continuous period of one year prior to the birth of the child, but was present in the United States or its possessions or served in the military services for periods totaling 10 years, at least 5 of which were after attaining the age of 14, a child born abroad is considered a citizen. But such a child must, prior to attaining the age of 23 and after the age of 14, spend at least 5 years continuously in the United States. It is clear that these provisions are very restrictive, and that the prime basis of citizenship in the United States is birth there.

France originally followed the *jus sanguinis* principle very strictly. Under Article 10 of the French Civil Code "every child born of a Frenchman in a foreign country was French." A child born in France of a foreigner was not French, though under the provisions of Article 9 of the Code a child born in France of a foreigner could upon attaining

---

4. Reich and State Nationality Law of July 27, 1913, paragraph 4. Under Article 116 of the Constitution of the Federal Republic (West Germany) all persons who possessed German nationality or who were accepted as refugees of German stock as of 31 December 1937 are Germans. Persons who lost German nationality by the acts of the Nazi regime are regranted this nationality upon application. In the absence of other provisions, the Law of 1913 is the basic nationality law. Under that law the legitimate child of a German father is German, as is the illegitimate child of a German mother. See the discussion in Oppenheim, *International Law* (8th ed., Lauterpacht). Vol. 1, p. 651.
5. Oppenheim, *ibid.* This would not, of course, include children of foreign diplomatic representatives.
6. Oppenheim, *ibid.*
7. For a listing of the different approaches toward nationality based on a 1935 study see Bishop, *International Law* 415 (2d ed. 1962). The original study will be found in 29 *American Journal of International Law* 248, 256 (1935). Although some changes no doubt have been made, the study gives a general idea as to the distribution of the different approaches.
8. In the case of *United States v. Wong Kim Ark*, 169 *U.S.* 649 (1898), the Supreme Court held that the child born in the United States of Chinese parents was a citizen of the United States, though at the time the parents were not eligible to become naturalized citizens. Under the *jus soli* approach the status or condition of the parents is irrelevant as long as they are subject to the jurisdiction of the state in which the child was born, *i.e.*, they are not diplomatic officials.
9. This is set forth in United States Code, Title 8, Section 1401.
10. Only American citizens by birth are eligible to become President. Constitution of the United States, Article II, Section 1(5).
11. See United States Code, Title 8, Section 1401 (5).

majority claim French nationality. The French approach fluctuated over the years as different nationality laws were enacted, but the French Nationality Law of 1945 extensively employed both principles in an effort to increase the number of French nationals. The provisions are interesting, as they demonstrate an effort by a nation to obtain as many nationals as possible.

Under Article 17 and 18, the legitimate child born of a French father is French irrespective of where he was born, as is the legitimate child of a French mother where the father's nationality is unknown. Unlike the United States, there are no residence requirements imposed on the parents. Where a child first establishes filiation[12] against a French parent, whether the father or mother, that child is French. So too, if one parent is French and the nationality of the parent against whom the first filiation action is brought is unknown, the child becomes French upon successfully maintaining an action of filiation against the French parent. Under Article 19, subject to an option to repudiate, the legitimate child of a French mother and foreign father is French, as is the natural child recognized by or successfully filiated against parents, one of whom is French. The above provisions are essentially based on *jus sanguinis*, as the country of birth is irrelevant.

The French law also contains many elements of *jus soli*.[13] Where a child is born in France of a father who was born in France, though not necessarily a French national, that child is French. The same is true when the parent against whom filiation was first established was born in France. The legitimate child born in France of a mother also born in France is French, subject to his right of repudiation; so is the child of a parent born in France when that parent is the one against whom filiation was established the second time. Under Article 21, the child born in France of parents whose nationality is unknown is French unless he is filiated and takes the nationality of the filiated parent.

Where the child was born in France of foreign parents, neither of whom was born in France, the child is considered French upon attaining majority if he is then residing in France and has been residing there since the age of 16.[14] He may decline French nationality in certain circumstances, and in certain circumstances the government may oppose the petition. Under the Law of 22 December 1961, military service can be substituted for the five year residence. Such a child can also claim French nationality prior to reaching majority if he has resided in France for five years. If he is under the age of 18, the claim can be made by his guardian. There are special provisions relating to children who were raised in France, though not born there; under certain circumstances they can acquire French nationality as well.[15] It is clear that France, while retaining the basic principle of *jus sanguinis*, has adopted many elements of *jus soli* in an effort to increase the number of French nationals.

